አቃቤ ሕግ ቁጥሩን ለማክበድና ጊዜ ለማራዘም ብቻ ሲል ያን ሁሉ ምስክር የቆጠረው እኛንም ከፍርድ በፊት የሚበቃውን ያህል በእስር እንድንታሽ በማሰብ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል:: የምስክሮች ቁጥር መብዛት፣ የቪዲዮው ማስረጃ መከመር፤ የተጠቀሰው አንቀጽ ብዛቱ፣ ይህ ሁሉ በሌለ ወንጀል ለማስፈረድ ባደረባቸው ጉጉትና ፍላጎት ነው::

ቀጣዩ ቀጠሮ ለጥቅምት 30/99 በመሆኑ እንደተለመደው ተጭነን፣ በመንገድም ላይ ታጅበን፤ ወደ ፍርድ ቤት ሄድን:: ዛሬም ባለፈው እንደተጀመረው የነዳንኤል ምስክሮች ናቸው የሚሰሙት:: 11ኛው ምስክር ነው:: ወንድ ወሰን ሥዩም፣ እድሜው 29 ቁራ የሚኖር ሥራ ግን የሌለው ነው::

ሲመሰክር:- "በሰኔ ወር ኢዴአፓ መድሕን ቢሮ አጠገብ ተገናኘን ከዳንኤል ጋር:: በ1996 ነው የቅንጅት አባል የሆንኩት:: በአጋጣሚ ነው ሻይ ስንጠጣ የተገናኘ ነው፤ ተዋወቅንና ስለ ቅንጅት አወራን:: በርታ አለኝና የስልክ ቁጥሩን ሰጠኝ:: ከዚያ በኋላ ሁለት ጊዜ ተገናኝተናል:: ኢህአዴግን ለመጣል ወጣቱን ማደራጀት እንዳለብኝ ነግሮኝ 200 ብር ሰጠኝ:: መንግሥት መሣሪያ እጠቀማለሁ ካለ አድማ በመምታት መቃወም ያስፈልጋል ብሎኝ ሰው በማስተባበር እና ፓምፍሌት በመበተን ስሰራ ቆየሁና ሰዎች ሲያዙ ተሰወርኩ:: በኋላ እስከመቼ መሰወር እችላለሁ ብዬ እጄን ሰጠሁ:: ወረዳ 21 በፈቃዴ ሄጄ ቃሌን ከሰጠሁ በኋላ ሂድ ስንፈልግህ ትመጣለህ ተብዬ ሄድኩ» አለ::

ይህን ከቀባጠረ በኋላ መስቀልኛ ጥያቄ ዳንኤል ማቅረብ ጀመረ:: ዳንኤልና ነጻነት መስቀልኛ ጥያቄ ለመጠየቅም ይሁን በአንዳንድ ሂደት ላይ ለመናገር ሲነሱ አቃብያነ ሕጎች በሙሉ ይጨንቃቸዋል ይቁነጠነጣሉ:: የሚባለውን ሳይሰሙ «ተቃውሞ» ማለት ያምራቸዋል:: የሚይዙት የሚጨብጡት ነው የሚጠፋቸው:: አሁንም ዳንኤል ሲነሳ መቁነጥነጥ መንሾካሾክ ጀመሩ::



"አቶ ወንድወሰን! አለዛሬ አይቼህ ስለማለውቅ መታወቂያህን ልታሳይ ትችላለህ? " አለው፣ ዳንኤል:: ላድርግ አላድርግ በሚል የተማጽኖ ጥያቄ ምስክሩ ፊቱን ወደ አቃቤ ሕጎች በማዞሩ ዳንኤል፣ "ምስክሩ ጥያቄ ሲጠየቁ በቀጥታ በመመለስ ፈንታ ፊቱን ወደ አቃቤ ሕግ እያዞረ ነውና ፊት ለፊት ችሎቱን እያየ ይመልስ" ብሎ ፍርድ ቤቱን ሲያሳስብ አቃቤ ሕግ ብድግ ብሎ፣ "እኛ በእንዲህ ዓይነት ርካሽ ተግባር አንሰማራም፣ ክሱ በቀላል አይታለፍብን::" አለ:: ዳንኤልን ይቀጣልን ማለት ነው:: ዳኛ አዲል «ምስክር (Eye contact) አያድርግ የሚለው ተቀባይነት የለውም» ካሉ በኋላ በመታወቂያው ላይ ያለውን በማንበብ «ሌጆ አሉሚኒዩም 29/05/89 ይላል» አሉ::

ዳንኤል፤ "አድራሻህ ባሁኑና በድሮው ላይ ልዩነት አለው" ሲለው ምስክሩ "ከ92 ጀምሮ ለቅቄያለሁ" አለ:: አንድ ጊዜ የተገናኛንበትን ገልጸው ሁለተኛውን አልተናገሩም፣ የት ነበር የተገናኘነው?

እዚያው አካባቢ ነው፣ ለ2 ደቂቃ ያህል የተገናኘ ነው:: ከኛ ቤተሰቦች ዘንድ ሂደህ 'በነዳንኤል ላይ አቃቤ ሕግ መስክር ብሎኝ ልመሰክር ነውና ገንዘብ ስጡኝ እንድተወው' ብለህ ቤተሰቤን አላነጋገርክም? ለተባለው ጥያቄ ሲመልስ "አላነጋገርኩም" ብሎ ደመደመ::

"ሻይ ቤት ተገናኘን ለመጀመርያ ጊዜ፤ ተዋወቅን ተግባባን በዚያው ቅጽበት መለመልኩህ፤ ገንዘብ ሰጠሁህ በቃ ይሄው ነው?

ይሄው ነው በቃ:: "

የጉድ ሀገር ሆነ:: እንዲህ አድርጎ ምልመላም የለ! ማንነቱ ሳይታወቅ ያውም ዳንኤልን የሚያህል ሕግን አብጠርጥሮ የሚያውቅ እንዲህ አይነቱን ተግባር በዚህ መልክ ፈጸመ ተብሎ ቢወራ ማመን አይቻልም::

ስለሕግና ፖለቲካ ምንነት ምንም የማያውቅ ሰው እንኳን ቢሆን እንዲህ አይነቱን የድብቅ ሥራ በዚህ መልኩ አያከናውንም። ፍርድ ቤቱም ይህን እውነት ብሎ ይቀበለዋል የሚል እምነት ቀርቶ ጥርጣሬ ባይኖረኝም ከሂደቱ እንደተረዳሁት በዚህ ፍርድ ቤት የማይቻል ምንም ነገር የለም። ከአቃቢያኑ አንድ ለታዛቢነት የተቀመጠ አለ፤ ከዳኞችም እንዲሁ ለታዛቢነት የተመደበው የግራ ዳኛው ይመስላል። አንዳንድ ጊዜ የመሃልና የቀኝ ዳኞች ጭርሱን የግራውን እርግፍ አድርገው እስከመኖሩም ይረሱታል። አልፎ አልፎ ትዝ ሲላቸው ድንገት ዳኛ አዲል ዘወር ብለው ያወሩታል።

የግራ ዳኛው ጆሮ ግንዱን ደግፎ ሲቀመጥ ሁለቱ የቅንጅት የምርጫ ጣቶች ቅርጻቸውን ሰርተው ስለሚታዩ በምልክት ክልክል መሆኑን ለመንገር እንሞክራለን እሱም አንዳንድ ጊዜ ያየናል መሰለኝ፣ ቶሎ ብድግ አድርጎ አቀማመጡን ይለውጣል። ችሎቱ ለምሳ እረፍት ካደረገ በኋላ ከቀትር በኋላ ቀጥሎ ተከታዩ ምስክር በአቶ በድሩ አደም ላይ የሚመሰክረው ቀረበ።

መስካሪው ተከሳሾች የተያዝንበትን ቀን ጨርሶ የሚያውቅ አይደለም፤ መስክር ያሉትም ይህንን ያውቀዋል በሚል እምነት አላስጠኑትም። ሲመሰክር፣ "መርካቶ በሚገኘው ቀበሌ ስብሰባ ተጠርተን ሄደን ነበር፣ እኔም እዚያ ነበርኩ። አቶ በድሩ አደም አዳራሹ በድንጋይ እንዲደበደብ ሲያነሳሱ ነበር፤ መስታወቱ ሲሰበር ሁሉ እዚያው ነበሩ" በማለት የምስክርነት ቃል ሰጠ።

የመስቀልኛ ጥያቄ እድሉ ሲገኝ አቶ በድሩ ምስክሩን "ይህ ሁኔታ የተከናወነው መቼ ነበር?" አሉት፣ መስካሪውም "ጥቅምት 23 ነው አለ። " አቶ በድሩ "እኔንስ እዚያ ያየኸኝ "መቼ ነው?" አሉት "ያው ጥቅምት 23 ነዋ " ብሎ አረጋገጠ።



አቶ በድሩም «የተከበረው ፍርድ ቤት በጥቅምት 23 ቀን እኔ ተይዤ ማእከላዊ እንደነበርኩ ይታወቅልኝ።» በማለት ይህን ጥናቱን በደንብ ያላጣጣመውን ምስክር ፋርሽነት አጋለጡት። በዚህም የእለቱ ችሎት ተከናውኖ የሚቀጥለው ቀጠሮ ለ 5/3/99 ከሰአት በኋላ ተቀጠረ።

ከፍርድ ቤት ወደ ወህኒ ቤታችን ተመለስን። ገረመው የሚባል ታሣሪ በዞን 5 እኛ ያለንበት ማለት ነው በቁጥር 1 ቤት ውስጥ ይኖራል። ገረመው ነጋዴ የነበረ ግን ከባለቤቱ ጋር በተፈጠረ ግጭት ለመፋታት ይደርሳል። ወዲያው የጭነት ማርቼዲስ መኪናውን ቤንዚን ማደያ አቁሞ ሳለ ጠላቶች /እሱ እንደሚለው የቀድሞው ሚስቱ ወዳጆች/ ያቃጥሉበታል። ማደያው ዳነ፤ መኪናው ጋየ። በዚህም የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ሞክሮ ነው የ7 ዓመታት ፍርድ ተጥሎበት የታሰረው። ገረመው ዘመድ አይጠይቀውም፤ ስንቅ የሚያቀብለው የለም፤ የወሕኒ ቤቱ የሚያቀርበውን ምግብ ነው የሚበላው። እንደሌሎቹ እንኳን አልፎ አልፎ የሚጠይቀውም ስንቅ የሚያቀብለውም የለውም።

በፊት የነበረው በዞን አንድ ነበር። ከዚያ ሲመጣ በትንሹ 3 ማዳበሪያ ይዞ ነበር የመጣው። ሶስቱም የማዳበሪያ ጆንያ በአሮጌ ልብስ የተሞላ ነበር። ሲያወራ እንደሰማሁት ከዞን አንድ ወደ አምስት ሲዛወር ሶስቱን ማዳበሪያ ጨርቅ ብቻ ሲፈቅዱለት በትንሹ ሌላ ሶስት አስቀርተውበታል። በዚህ ባመጣው ማዳበሪያ ጆንያ ውስጥ ያለው ጨርቅ ወጥቶ ተሰቅሏል ገበያው ቀልጧል ገረመው ቆሞ ገንዘቡን ይሰበስባል ገዢዎች የሚፈልጉትንና የሚሆናቸውን ይመርጣሉ። "ምን መጣ?" ስል ገረመው ሊወጣ ስለሆነ እቃውን ለትራንስፖርት እየሸጠ ነው ተባለ። እውነት ሊወጣ ነው? ምነው አልተወራ? ሌሎች ሲወጡ በትንሹ ሳምንት ሲቀራቸው የመውጣታቸው ነገር ይወራል። የስንብት ትንሽ ትንሽ ገንዘብ ይዋጣላቸው ነበር አሁን ገረመው ግን ወሬውም የለም መዋጮም የለም።እንዴት ለገረመው መዋጮ አልተሰበሰበም?» አልኩ ባሳቤ።

ገረመው ልብስ ከመሸጥ ባሻገር አንዳንድ ስራዎች ለሰዎች እየሰራ ገንዘብ ያገኛል::ምናልባት ገንዘብ ያለተሰበሰበለት ለዚህ ይሆናል:: ሁል ጊዜ ከመጣበት ቀን ጀምሮ እኔ የምወጣው እናንተ ከወጣችሁ በኋላ ነው" ይል ነበር:: ለምን? ስንለው እናንተ የማትፈልጉትን ልብስና ሌላም የማትወስዱትን ሰብስቤ ነው የምወጣው ይል ነበርና ዛሬ ቀድሞን ሊወጣ እየተዘጋጀ ነው:: ማታ ገረመው እንዲወጣ አልተጠራም:: እርግጥ ይህ አዲስ ነገር አይደለም:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች የእስራት ጊዜያቸውን ከጨረሱና ሊወጡ ነው ከተባለ በኋላ ሳምንት ሁለት ሳምንት ቆይተው በስንት ጩኸት እንደሚወጡ እናውቃለን:: የገረመውም እንደዚሁ ሊሆን ይችላል::

ተፈቺዎች የሚቆዩበት ምክንያት፣ በዞኑ ባሉ ሰዎች እንደሚነገረው፣ ምን ያህል እውነት እንደሆነ አላውቅም እንጂ የመውጫ ቀናቸው የሚተላለፈው የመውጫ ወይም የመፈቻ ወረቀት የሚያመጣው ሰው ትንሽ ካላቀመሱት ማዘግየት የተለመደ መቅጫው ነው ይባላል:: ገረመው ደሞ ይቺን ሊያደርግ ቀርቶ የሚያስበውም አይደለም:: ትልቅ ሃሳብ የሆነበት ከቃሊቲ ወህኒ ቤት ከወጣ በኋላ የሚሄደው ወደ ጂማ በመሆኑ ጅማ እስኪሄድ ድረስ የት እንደሚቆይ አለማወቁ ነው:: ሆኖም፣ አርፈህ በማግስቱ ቲኬት ቆርጠህ መሄድ ነው ስንለው፤ ጅማ ከመሄዱ በፊት እዚያ ያለውን ሁኔታ ማጣራት አለብኝ:: የት እገባለሁ ዝም ብዬ ብሄድ? ችግር ነው እያለ ነገሩን ሁሉ ችግር በችግር ያደርገዋል:: ስለዚህ ልውጣ ብሎ ገንዘብ መክፈሉን አያስበውም::

በጣም የሚገርመው ነገር፣ ገረመው የተከሰሰበትን ወንጀል በፍጹም ሃሰት ነው ይላል:: እንዲያውም መኪናውን ካቃጠሉብኝ በኋላ ሊገሉኝ ሲሉ ተሸሸግሁ፤ ፖሊስ ፈልጎ ያዘኝ:: ያው ጉቦ ተቀብሎ እኔን ጥፋተኛ እነሱን ነጻ ብሎ ወህኒ ላከኝ ይላል:: ለነገሩ በቃሊቲ ወህኒ ቤት ሁሉም ስለራሱ ሲያወራ እኔ ንጹህ ነኝ ፍርድ ተዛብቶብኝ ነው የሚለው:: ለኛም ቢሆን ሁሉም እንዲሁ አለወንጀላቸው የታሰሩ



መሆናቸውን ይነገሩን ነበር:: እየቆየ ጉዳያቸውን ለአንተነህ እየነገሩ የክስ ሰነዳቸውን ሲያየው አንዳቸውም እንዳሉት ሳይሆን፣ በተቃራኒው እየሆነ ስላገኘውና ለኛም ይህንኑ ስለነገረን ማመን ተውን::

አንድ ተስፋዬ የሚሉት የአንድ ድርጅት ገንዘብ ቤት የነበረ ሲያወራልን የነበረው፣ በ7 ሚሊዮን ብር እንደተከሰሰና በሃሰት እንደታሰረ ነበር:: በኋላ የክስ ቻርጁ ሲታይ የተከሰሰበት 4000 ብር ጎድሎበት መሆኑን አወቅን:: ተስፋዬ በዚያ ግቢ ካሉት እስረኞች ሁሉ አክራሪው ፀሎተኛ ነው:: የሚፀልይበት ጊዜ ማታ ቆጠራና እራትም የቴሌቪዥንም ፕሮግራም አልቆ ሁሉም ወደ እንቅልፍ በሚሄድበት ጊዜ ሲሆን የፀሎት ሥርዓቱ ትንሽ ለየት ያለ እንደሆነ ይነገራል:: በዚህም የተለየ ፀሎቱ በተደጋጋሚ ተከሶ ቅጣት ተጥሎበታል::

አንድ እስረኛ ጥፋት አጥፍቶ አቤቱታ ሲቀርብበት ወይም የሌሎቹን መብት ተጋፋ ከተባለ፣ አለያም የግቢውን መተዳደሪያ ከጣሰ ይቀጣል:: ቅጣቱ በገንዘብ ወይም በምግብ አይደለም፤ ያንን አያደርጉም:: ቅጣቱ ቆሻሻ ተሸክሞ ማፍሰስ ወይም ውጪ ያለውን መጸዳጃ ማጠብ ነው:: ተስፋዬም ለአንድ ሳምንት ቆሻሻ ተሸክሞ እንዲያፈስ ቅጣት ተጥሎበት ነበር:: ምክንያቱ በሚጸልይበት ጊዜ ሰዉ ሁሉ ተኝቶ እያለ እሱ ራሱ በሰራው ረጂም መቁጠሪያ ጀርባውን እየገረፈ፣ ይቅር በለን! ይቅር በላቸው! እያለ ድምጹንም የግርፋቱንም ጩኸት ከፍ እያደረገ ሌሎቹን እንቅልፍ በመንሳቱ ሲሆን፣ ይህንኑ ለማጽናናት አይዞህ ለሚሉት የሚሰጠው መልስ «የሚያደርጉትን አያውቁትምና ይቅር ይበላቸው» በማለት ነበር::

የሚቀጥለው የቀጠሮ ቀን በ5/3/99 ነበር:: መቼም ቢሆን የማይሻሻለው የግርግርና የፍተሻው፤ የመቆጣጠሩ፤ የፖሊሱ መብዛት፤ የግቡ ጠጋ በሉ፤ መስኮቱ ይዘጋ፤ ከኋላ ሁኑ፤ ሥነስርአት የሚሉት የተለመዱ ትእዛዛት ናቸው:: ትላንት ጥቁር አትልበሱ ብለው እንደሆነ፣ ያ ሲፈርስባቸው ደሞ ኮፍያ አታድርጉ ይላሉ ያም ሲቀር መጽሐፍ አትያዙ፤ ደብተር ክልክል

ነው" ወዘተ...... ሁል ጊዜ ትእዛዛቸው ቅጥ ያጣ ነው:: ለሚሰጠው ትእዛዝ ሁሉ አንዱ ያዘዘውን ሌላው መጥቶ ይሽረውና እርስ በርሳቸውም የሚፈጥሩትን አለመግባባት እስኪፈቱ ድረስ እኛ በታዛቢነት መመልከት ነው::

በዛሬው እለት አቃቤ ህግ ያቀረባቸው ምስክሮች 1ኛ፣ 2ኛ፣ 7ኛ ክሶች ሆኖ የመንግሥት ደጋፊዎች ናቸው በተባሉ ላይ "በአመፁ" ምክንያት የደረሰባቸውን አካላዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት ያስረዱልኛል ያላቸውን ነው::

መቅረብ ከሚገባቸው ምሥክሮች ፃኙ ቀርበዋል አንዱ እየመጣ መሆኑን አቃቤ ሕግ ለችሎቱ አስረድቶ የምስክር መስማቱ ሂደት ቀጠለ:: የመጀመሪያው ምስክር "7ኛ አካባቢ የተነሳ ግርግር ነው ያየሁት:: ከአብነት አካባቢ ድንጋይና ገጀራ የያዙ ወደ ላይ ይመጣሉ:: የፌዴራል ፖሊሶች ነበሩ:: ድንጋይና ገጀራ የያዙት አመጣጣቸው የቀበሌውን ክበብ ለማቃጠል ነው:: ሁሉም የቅንጅት አርማና መፈክር ይዘዋል:: በተፈጠረው ረብሻ እኔ ራሴ እንኳን ከ8 ያላነሱ የፌዴራል ፖሊሶች ሆስፒታል አድርሻለሁ:: ሰልፈኞቹ ንብረት ሰባብረዋል የተማረ ይግዛን መለስ ይውረድ፤ ፌዴራል መሄይም፤ ወያኔ ዘረኛ እያሉ ይጮሁ ነበር" በማለት መሰከረ::

ሁለተኛው ምስክርም በመቀጠል:- "ተማሪዎች በማስ ወጡ፤ መለስ ሌባ! ኢህአዴግ ሌባ! በማለት ይጮሁ ነበር:: ቀበሌ ጽ/ቤት ቆየሁ:: ወደ ማታ ገደማ ቀበሌውን የማቃጠል ሙከራ ተደረገ:: ድንጋይ ከኋላና ከፊት እንደመአት ይወርዳል:: በተለይ በ24 ምሽት 2 ሰአት ላይ በሬን ጥሰው ገቡ::ቤንዚንና ጋዝ ይዘዋል:: እኛ ቴሌቪዥን ስናይ ነበር:: የድንጋይ ናዳ ቤታችን ላይ አወረዱብን:: ነዳጅም ወርውረው ነበር ግን አልተቀጣጠለም:: ከውጭ ግን አጥሩን አነደዱት የሰፈር ሰው ተረባርቦ አጠፋው፤ በዚህ ድንጋጤ እቤት ያሉት



ሽማግሌ እግርና እጃቸው ፓራላይዝድ ሆነ በማለት የማይመስል ምስክርነት አስመዘገበ::

ሌላዋ መስካሪ የቀበሌ ሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት ናቸው:: ገና ወደ መመስከሪያው ቦታ ሲመጡ እኛን በግልምጫ አነሱን፤ ጥላቻቸው ይታይ ነበር:: ሲጀምሩም በንዴት ነው::«የቅንጅት ደጋፊዎች ወደ ቀበሌው መጥተው 'ይለያል ዘንድሮ የወያኔ ኑሮ' እያሉ ቢሮው ላይ ድንጋይ ይወረውሩ ነበር:: የቀበሌውን አጥር ደምስሰው ገቡ፤ ባንዲራውን አውርደው በላዩ ላይ የተለጠፈውን ኮከብ ቀደዱት:: የቀበሌውን መስኮት ሰባበሩት:: ሠራተኞቹ በሙሉ በፍርሃት ጠረጴዛ ሥር ተደብቀው ዋሉ:: በመጨረሻ ፖሊስ መጥቶ በጥበቃ ተወሰድን:: የኔን ቤት በሬን ሰብረው ዘረፉት፣ ልጆቼን አስፈራርተው በሽታ ላይ ጣሏቸው:: ይህ ሁሉ እንግዲህ የቀበሌ ሥራ አመራር በመሆኔና የኢህአዴግ አባል በመሆኔ ነው:: እኔ ደሞ አምኜበት ነው፣ ለምን ይህ ይደርስብኛል? ቤተሰቤ ምን አደረገ? በማለት አስመዘገቡ፣ የቀበሌዋ ሥራ አስፈጻሚና የኢህአዴግ አባል የሆኑት መስካሪ:: ከሳቸው ሌላ ምን ይጠበቃል?

የምስክር ማስማቱ በተለያዩ ቀጠሮዎች ሲካሄድ ከቆየ በኋላ አቃቤ ሕግ፣ "የምስክሮቹን ቁጥር ቀንሻለሁ፣ ነገር ግን አዲስ 15 ምስክሮች ለክሱ በጣም አስፈላጊና ዋና ሊባሉ የሚችሉ ምስክሮች ስለሆኑ ይፈቀድልኝ" አለ:: ተከሳሾች፣ ክቡር ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርቤ ጨርሻለሁ ያለው አቃቤ ሕግ አሁን 'አዲስ ላቅርብ' ማለቱ አግባብነት የሌለው ስለሆነ አይፈቀድብን በማለት ብናመለክትም፣ ዳኛው "አብዛኛዎቹን ምስክሮች አስቀርቶ 15 መጠየቁ ለፍርድ ሂደቱ መፋጠን ያለውን ፈቃደኝነት ስለሚያሳይ አቃቤ ሕግ የጠየቀው ተፈቅዶለታል" አሉ:: በዚህም መሰረት በ20/3/99 4 ሰአት ላይ በዋለው ችሎት በጣም ልዩ የሆነውንና እውነትን የመሰከረውን የአቃቤ ሕግ ምስክር እንመልከት::

ምስክሩ፣ ቀደም ባሉት በተለይ ሽሮ ሜዳን በተመለከት በቀረቡት የአቃቤ ሕግ ምስክሮች፣ ሽጉጡን ተቀምቶ በገጀራ ጭንቅላቱን ተመቶ፣ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበታል፤ ደሙ እንደጎርፍ ይፈስ ነበር በአናቱ ደሙ ሲንተከተክ ይታይ ነበር" የተባለው ምስክር ነው:: ኑር ሁሴን ከሞት ተነስቶ እንደመጣ ነው የተቀበልነው:: አንዱ ምስክር "ሞተ" ካለ በኋላ ትዝ ብሎት ነው "አልሞተም" ያለው፣ ያውም በመስቀልኛ ጥያቄ ላይ::

ኑር ሁሴን እድሪስ፤ ልብስ ሰፊ፤ የሽሬ ተወላጅ፤ ለ13 ዓመታት ሽሮ ሜዳ ነዋሪ ነኝ:: በ23/8/98 ሽሬ ሄድኩ ካለ በኋላ ጭንቅላቴን ያመኛል ብሎ ማልቀስ ጀመረ:: ፍርድ ቤቱም አይዞህ ተረጋጋ ብሎ ማባባል ያዘ:: ትግሬ በመሆኔ ብቻ ቅንጅት ነው የደበደበኝ:: እኔ የፖለቲካ አባል አይደለሁም ታዲያ መላኩ፤ ታዬ፤ መሐመድ ፍቃዱ ናቸው የደበደቡኝ:: የልጆች አባት ነኝ፣ ሰዎቹን አውቃቸዋለሁ መማርያዬን ወሰዱብኝ ኢዮብ ድብደባ ፈጸመብኝ ድንጋይ ውርወራ ነበር፤ በሥጋ መከትከቻ እራሴን መቱኝ ገደልነው ገደልነው ሲሉ እሰማቸው ነበር:: 4 ወር ጥቁር አንበሳ ተኝሁ ከዛ ትንሽ ብረሳው ቢሻለኝ ብዬ ወደ ሽሬ ሄድኩ አሁን ነው የመጣሁት::" አለ::

በኋላ ከተከሳሽና "ደበደበኝ" ካለው ከፍቃዱ መስቀልኛ ጥያቄውን ማቅረብ ጀመረ:: ረጋ ብሎ በአክብሮት ዓይን አይኑን እያየው «ጋሼ ኑር እንደምን ነህ? እኔን ታውቀኛለህ አይደል?»

ኑር፣ "አዎን አውቅሃለሁ"

ፈቃደ፣ "አንድ ሰፈር ነን አይደል?"

ኑር፣ "እንዴ በደንብ አውቅሃለሁ እንጂ"

ፈቃደ፣ "ታዲያ እኔ ምን አድርጌሃለሁ?"



ኑር፣ "አንተ"

ፈቃደ፣ "እኔ ምን አደረግኩህ?"

ኑር፣ "ምንም"

ፈቃደ፣ "ታዲያ ለምን ከሰስከኝ?"

ኑር፣ "እነሱ ክሰሰው አሉኛ"

ፈቃደ፣ "እነማን ?"

ኑር፣ "መንግሥት"

ፈቃደ፣ "መንግሥት የቱ?"

ኑር፣ (ወደ አቃቤ ሕግ እያሳየ) "እነሱ ናቸዋ"

ፈቃደ፣ "እነሱ እነማን ናቸው?"

ኑር፣ "እነዚህ አቃቤ ሕጎቹ ናቸው እንዲህ ብለህ ክሰስ ያሉኝ አንተ ምንም አላደረግኸኝም:: "

አቃቤ ሕግ፣ (ድንገት ብድግ ብሎ) "የተከበረው ፍርድ ቤት በደረሰበት ድብደባ የተነሳ አእምሮው ትክክል አለመሆኑ ይመዝገብልን:: በማለት ዋነኛ ማስረጃዬ ያለውን ምስክር እብድ ነው ብሎ ከሰሰው::"

ክችሎቱ የማጣርያ ጥያቄ ተብሎ በ«ዳኛ» ልዑል ጥያቄው ለኑር ሁሴን ቀረበ::የጥያቄው አቀራረብ

ግን ለማጣሪያነት ሳይሆን ለኛ ለተከሳሾች እንደገባን ኑር ሁሴን የተናገረውን በማፍረስ አቃቤ ሕግ ይመሰክርልኛል ወዳለው ቃል ለመመለስ የተሞከረ እንደሆነ ነው የጠረጠርነው::

ዳኛ ልኡል፣ "ማን እንደመታዎት አይተዋል?"

ኑር፣ "አላየሁም ግን መላኩ ነበረበት፣ እሱ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ"

ዳኛ፣ "የመታወትን አላየሁም ካሉ ማን ነገረዎት የመታዎትን ሰው?"

ኑር፣ "መንግሥት"

ዳኛ፣ "ማን? "

ኑር፣ "አላውቅም" ከዚህ በኋላ ጥያቄው አካሄዱ ስላላማረ አልቀጠለም:: በቃው:: የተፈለገውን ግብ አልመታም!!

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቀነ ቀጠሮዎች የቀረቡት ምስክሮች በየጎዳናው ላይ ተሰማርተው የነበሩ ፖሊሶች ነበሩ:: ከፖሊሶቹ የቃል ምስክርነት ጋር ተዳምሮ የወንጀል ማጠናከሪያ የሚሆን ፖሊስ በእለቱ ያስነሳውን ፊልምም አቅርቦ ነበር:: በዚህ በቀረበው ፊልም ግን ለአቃቤ ሕግም ለፖሊስ አስረጂ ባለስልጣንም ያልታያቸው ቀደም ብለው በቀረቡ ምስክሮች ወንጀሉ ሰላማዊ እንዳልሆነና በተለይም በትግራይ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ጉዳት ያዘለ እንቅስቃሴ ነበር የሚለውን ክስ ሊያጠናክር ይችላል የተባለው ጉዳይ የከሸፈ መሆኑን የሚያሳይ ነበር::

አቃቤ ሕግ ማጠናከርያ ማስረጃ ያለው ሁሉ መፍረስ የጀመረው ገና ከጅምሩ ነው:: የምስክርነት



ቃላቸውን የሰጡት የአቃቤ ሕግ የፈጠራ ምስክሮች በሙሉ ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ገጀራ፤ ስለት፤ በነዳጅ የተሞላ ጠርሙስ፤ ሌላም ሌላም ይዘዋል በማለት ነበር ቃላቸውን የሰጡት:: ፊልሙ በሚታይበት ጊዜ ግን አንድም ቦታ ይህ የተባለው ቁሳቁስ ጨርሶ አይታይም:: ታዲያ ይዘዋል የተባለውን ስለት ምን በላው? ፊልሙ እሱን እያስጣለ ነበር የሚነሳው ወይስ ፊልም አንሺው የቅንጅት አባል ስለነበረ ያልያዙትን እየመረጠ ነበር ያነሳው? ይህ ነው እንግዲህ የማያወላውል ማስረጃ ተብሎ በአቃቤ ሕግ የቀረበው ማስረጃ:: የእያንዳንዱን ምስክር ሀቀኛነት ለማወቅ ተብሎ የምስክሮች ማንነት አስቀድሞ ይገለጽ ሲባል ተቃውሞ ቀርቦ አቃቤ ሕግ በጠየቀው መሰረት ቢፈቀድለትም «ዕውነት ይዘገያል እንጂ ማሸነፉ አይቀሬ ነው» የተባለውን በጣም በፈጠነ መልኩ አስመሰከረ::

## የግለሰቦች ለአስተያየት በክሱ ላይ

ጋሼ መስፍን በአጠቃላዩ የፍርድ ሂደትና እኛ ስለምናቀርበው አቤቱታ፣ ስለሚሰጠው ውሳኔ በጣም ተናዷል:: «ወንጀል እንደሊሻን» የሚሰጥ ፍርድ ቤት እያለ ምሳ ከበላን በኋላ ብዙ ተነጋገርን:: በማግስቱ ጠዋት ላይ ቁርስ በልተን አቅም ያላቸው ለጤንነታቸው ልምምድ ሲሰሩ እያየን ቡና ስንጠጣ «እስቲ አንብባት» ብሎ ሰጠኝ:: ወረቀቷ በትንሳኤ ሬዲዮ ቀርባለች፤ ግን ብዙ ያላዳመጣት ሊኖር ስለሚችል ይቺው:

### «ወንጀል እንደሊሻን»
ከመስፍን ወ/ማርያም (T/C)
ቃሊቲ

በመጀመሪያ ድሮ በአንድ ፍርድ ቤት ውስጥ ክርክር ለማዳመጥ ገብቼ የሰማሁትን ልናገር:: አንድ

ሰው ሌላውን በአንድ ሺህ ብር ከሶታል። ተከሳሹ ደሞ "ሳንቲም የለብኝም" ይላል። ከሳሹ ከጠበቃው ጋር በመሆን ላቀረበው ክስ ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው፤ ከሳሹ ራሱ ለአንድ ጓደኛው የጻፈውን ደብዳቤ ነው። ተከሳሹ በመደነቅ "ይህ የእኔ ከሳሽ፤ ደግ ሰው በመሆኑ በ1000 ብር ወሰነው እንጂ አንድ ሚሊዮን አለብህ ቢለኝ ማን ይከለክለዋል?" በማለት በፌዝ ተናገረ። እኔ ዳኛው ፋይሉን ዘግተው ለተከሳሹ ኪሳራ ቆርጠው ያሰናብቱታል ብዬ ስጠብቅ ዳኛው ሌላ ማስረጃ አቅርብ ብለው በቀጠሮ አሳደሩት።

በዚህ ክስ ላይ የህግ ስርአቱን ያበላሹት በመጀመሪያ ከሳሹና ጠበቃው ናቸው። ከዚያ በኋላ ፍርድ ቤቱ ከማረም ይልቅ ነገሩን በማጓተት የፍርድ ስርአቱን በተጨማሪ ግድፈት አበላሸው።ይህንን ይዘን አሁን በቅንጅት መሪችምና አባሎች፤ በጋዜጠኞችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መሪዎች ላይ የቀረቡትን ክሶችና የፍርዱን ሂደት እንመልከት። ክሶቹን ሰው ሁሉ ስለሚያውቃቸው አልዘረዝራቸውም፤ ነገር ግን ክሶቹ ከላይ በፍትሐ ብሔር ችሎት እንደገለጽሁት የከሳሽ ዓላማ በትንሹ የተመጠነ ሳይሆን፣ ተከሳሾችን ለመደፍጠጥና ለመጨፍለቅ የታለመ ነው። ይረሳል እንጂ መደፍጠጥና መጨፍለቁ እርቃኑን በወጣ ጭካኔ በተለይ በወጣቶች ላይ ተፈጽሟል። የታሰሩት የተሻለ ዕድል የገጠማቸው ናቸው። የተገደሉት በሕገ አራዊት ተጨፍጭፈዋል። ከሳሽ ገና ከመጀመሪያው የክሱን ዓይነትና የቅጣቱንም ክብደት በአደባባይ አሳውቋል። አቃቤ ሕግ የሚባሉት የከሳሽ ጠበቆችም የከሳሹን ትዕዛዝ ተቀብለው የክስ ክምር አቅርበዋል። የክሱን ክምር በህጋዊ ስርአት ለማጣራት ችሎታ ያነሳቸውን ያህል ተከሳሾችንም ለማበጠር ስለተሳናቸው በያለበት ያገኙትን ስም ሁሉ ከአውሮፓ፤ ከአሜሪካ፤ ጭምር በመጨመር የተከሳሾቹን ዝርዝር አሳብጠውታል። ለከሳሾቹ ጠበቆች ትልቁ ነገር ክሱንና ተከሳሾቹን መጨመር ብቻ ነው። አሜሪካ ተቆጣና የተከሳሾቹ ክምር ትንሽ ተናደ። እንዲሁም አንዱ ክስ ትንሽ ተቀረፈለት።

የከሳሽ ጠበቆች በፍርድ ቤቱ ውስጥ ያሳዩትን ስነ ምግባር ለእኔ የሚያሳፍረኝ ነበር። ፍርድ ቤቱ ከተሰየመ በኋላ በግርማ ሞገስ ይገባሉ። በተከሳሾች ላይ አስቀድመው ወስነው አድመኞች አንዳንዱም ወንጀለኞች እያሉ ሲናገሩ ቆይተዋል። የሶስቱ ተከሳሾች ጠበቆች ተቃውሞ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጊዜ ወስዶ የከሳሽ ጠበቆችን አረማቸው። እነሱን የሚያካክሉ ልጆች ያሏቸውን ሽማግሌዎች ተራ ጨዋነት በጎደለው አነጋገር ሲዘረጥጧቸው ኩራት ይሰማቸው ነበር። የተዋረዱት እነሱ መሆናቸውን ሳያውቁት አዋረድናቸው ብለው ያብጡ ነበር።እራሳቸው ለምስክርነት ያቀረቡት ሰው ስላጋለጣቸው «የአዕምሮ ሕመምተኛ ነው» በማለት ስሙን አጠፉት።የከሳሽ ጠበቆች እንዲህ ያሉ ናቸው።

ከክሶቹ ሁሉ የሚያቅለሸልሸውና የሚከረፋው « የትግሬን ዘር ለማጥፋት» የሚለው ነው።ተከሳሾቹን ለዐመታት አስሮ ለማቆየትም ሆነ ለመግደል ይህ ክስ በፍጹም አስፈላጊ አይደለም።

የተፈለገው የትግራይ ተወላጆችን በማስፈራራትና በስጋት ውስጥ በመጣል ወደ ወያኔ እንዲጠጉ ለማድረግ ነው።ይህ እኩይ ክስ ተከሳሾችን ጭራቅ በማስመሰል የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት የታቀደ ነው።

የከሳሾች ጠበቃ ለክሶቹ ያቀረባቸው «የአድማ» ማስረጃዎች በምርጫ ውድድሩ ጊዜ በቪዲዮ የተነሱ ስብሰባዎች፤ በኢቲቪ የተላለፉ ክርክሮች፣ በጋዜጣ የወጡ ጸሁፎች ናቸው። እንኳን የሕግ ጠበቃና ማንም መሐይም ቢሆን አድማ በእንዲህ ዓይነት ዘዴ በአደባባይ ይደረጋል ብሎ አያስብም። ከዚያም በላይ «አድመኞቹ» በኢትዮጵያ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩና ብዙዎቹም በጭራሽ የማይተዋወቁ ናቸው።

የአድማ ወንጀል ተከሳሾቹን ለመፈረጅ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት አለ። የከሳሽ ጠበቃዎች በእያንዳንዱ ተከሳሽ ላይ የወንጀለኛነት ማስረጃ ለማግኘትም ሆነ ለመከራከር ባለመቻላቸው ነው። የሕግ አዋቂዎች እንደሚሉት ወንጀል የግል ነው። ለከሳሽ ጠበቃዎች ግን ፍጹም የማይተዋወቁና የማይገናኙ ሰዎችን በአንድ ከረጢት ውስጥ ከቶ በጅምላ «አድመኞች» ማለት የቀለለ ነበር።

ተከሳሾች በመጀመሪያው ላይ በጣም የታወቁ የሕግ ምሁራን ጠበቆች ነበሯቸው። የዋስ መብትን

ለማስከበር የቀረቡት በሕገ መንግሥቱና በዓለም አቀፍ ሕጎች ላይ የተመሰረተ ክርክር ሰሚ አላገኘም። የከሳሽ ጠበቆች ያሉት ሁሉ የሚፈጸም እየመሰለ ሄደ። በዚህ ጊዜ ሌላ ምርጫ አልነበረም፤ ስለዚህም ከቅዱስ ዳዊት ጋር በሚከተለው ፀሎት ክርክሩን መዝጋት አስፈላጊ ሆነ።

«ፍታህ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ
እምሕዝበ ውጹአን እምጽድቅ»
«አምላኬ ሆይ ከእውነት ከታቀቡን፤
ከራቁ ሰዎች ጋር ተከራክረህ ፍረድልኝ»

ሁሉንም ነገር ለፍርድ ቤቱ ትተን ተከሳሾች፣ ተመልካቾችና አድማጮች ሆንን። ምንም እንኳን የከሳሽ ጠበቆች የሥነ ምግባር ጉድለትና በፍርድ ቤቱም ውስጥ ዙሪያችንን ጠበንጃ በያዙ ወታደሮች መከበባችን የፍርድ ቤቱን ግርማና ሞገስ ቢፈታተኑም፤ ለፍርድ ቤቱ በበኩሌ ትልቅ ክብር አለኝ።ፍርድ ቤቱ የአንድ ሃገር ሕዝብ በአንድነትና በሠላም እንዲኖር የሚያደርገው መሠረት ነው።ከዚህም አልፎ ለዚህ ፍርድ ቤት ያለኝ ክብር በዓይነ ሕሊናዬ በግልጽ የማያቸውን በማካተት ነው።

1ኛ- ከዳኞች ወንበሮች በጣም ከፍ ብሎ እግዚአብሔር የሁላችንንም ልብና አእምሮ ያያል፤ ይፈርዳል፣ ለፍርዱም ፍርዱን ይሰጣል።

2ኛ- የኢትዮጵያ ሕዝብ የህግ መጽሐፍ ከፍ አድርጎ ተሸክሞ «የሕግ ያለህ » ይላል።

3ኛ- የአጼ ሰርጸ ድንግል ሠራዊት ከደቡብ ኢትዮጵያ ገስግሶ ከቱርክ ወራሪዎች ጋር ሲፋለም ተቀላቅሎ የፈሰሰው ደምና ተቃቅፎ አፈር የሆነው አጥንት የማን ዘር ነው?እነዚህ አፈር የሆኑ ኢትዮጵያውያን «አፈር ብንሆንም በሁላችሁም ውስጥ አለን» ሲሉ ይሰማኛል። በአድዋ፣ በማይጨውና በባድመም የፈሰሰው ደምና የተከሰከሰው አጥንት የማን ዘር ነው?

4ኛ- አክሱም ጽዮን፣ ደብረ ዳሞና ደብረ ቢዘን በያሬድ ዝማሬ ይጸልዩልናል።

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ስደዶሙ ለአጋንንት፣
ስደዶሙ እግዚኦ እምየማንነ ወእምዳግም



ወእምዛቲ መካንነ ይርሃቁ እም ለአለ
ይፀልእዋ ለነፍስየ
«አጋንንትን የምታባርሩ አብወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከቀኛችንም ከግራችንም ከዚች ከቤታችንም (ኢትዮጵያ) ነፍሳችንን የሚጠሉትን ሁሉ አርቅልን።"

5ኛ የእውነት መዝገቧን በግራ እጇ፣ የነጻነት ብእሩን በቀኝ እጁ ይዞ ታሪክ ይመዘግባል።

የከሳሽና የከሳሽ ጠበቃን ዓላማ የሃሰት ድር፣ የእስረኞችንና የቤተሰቦቻቸውንም መጉላላት የዳኞቹን ጭንቀትና ፍርድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃዘንና ጸሎት የዓለም አቀፉን ኡኡታና ተቃውሞ በመልክ በመልኩ እያነጠረ ለሚቀጥሉት ትውልዶች ለማስተላለፍ ይመዘግባል። እያንዳንዳችን በታሪክ ፍርድ ነጻ የምንወጣውና ወይም የሚፈረድብን የልጅ ልጆቻችንን አክብሮት የምናገኘው ወይም የምናጣው በዛሬው ሥራችን ነው።

እንግዲህ ለፍርድ ቤቱ ያለኝ ክብር እነዚህን በአጭሩ የገለጽኳቸውን ሃይሎች ሁሉ በአንድ ላይ በማጠቃለል ነው።

ፍርድ ቤቱ ውስጥ ከሳሾችን ከበው የሚታዩ ጠመንጃ የያዙ ወታደሮች ለፍርድ ቤቱ ያለኝን ክብር እንደሚፈታተኑት አይካድም። ከዚያ በላይ የከሳሽ ጠበቃ ያቀረበውን የክስ ድሪቶ በመቀበል የዋስትና መብት ለተከሳሾች መነፈጉ ያሳዝናል። በዚህ ምክንያት እያንዳንዱ ተከሳሽ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ከሥራ ውጭ ሆኗል። ቤተሰቦቹ ብቻ ሳይሆኑ አገሪቱም ተጎድታለች። አንድ ሺህ ያህል ሰዎች ለአንድ ዓመት ተኩል ከሥራ ውጪ ሲሆኑ አገሪቱ አንድ ሺህ አምስት መቶ የሥራ አመታት አጣች ማለት ነው። ሁለተኛውን ሺህ የክርስትና ዘመን (ሚሌኒየም) እናከብራለን ብሎ በሰፊው በመደገስ ላይ ላላ ደሃ ሀገር አንድ ሺህ አምስት መቶ የሥራ ዓመታት ማጣት የሚያሳዝን ባይሆን ኖሮ ያስቃል።

ከ1997 ምርጫ ጋር በተያያዘ የታሰርንበት የአንድ ዓመት ተኩል የግፍ እስር ከሌሎች እስረኞች ጋር ሲነጻጸር ኢምንት ነው። ወጣቶችና ሽማግሌዎች

ከአምስት አመታት እስከ አስር ዓመታት ያለፍርድ በቀጠሮ የሚመላለሱ ሞልተዋል።እንደዚህ ያለው ግፍ በብዙ ሺህ ሰዎች ላይ የሚፈጸም ነው። ይባስ ብሎም የተፈረደባቸው ጊዜያቸውን ሲጨርሱና አንዳንዶቹንም ፍርድ ቤት ነጻ ሲላቸው ለሳምንታትና ለወራት እንደታሰሩ የሚቆዩ ሞልተዋል።

በእኛ አንድ ዓመት ተኩል ከእስር ቤት ወደ ፍርድ ቤት መመላለስ የታዘብሁት የከሳሽ ጠበቃ ምን ያህል በሕግ የመጫወት ሥልጣን እንዳለው ነው።የቪድዮ ክምር በማስረጃነት ያቀርባል፤ቅንጣት ታህል እውነት ያለባቸው ቢሆን በጣም ጥቂቶች ይሆኑ ነበር።ከዚያም በላይ እያንዳንዱ ቪዲዮ ከመታየቱ በፊት የከሳሽ ጠበቃ የምታዩትን አትመኑ እኔ የምነግራችሁን ተቀበሉ የሚል አሰልቺ፤ሐሰት፤ ጊዜ ከመፍጀት በቀር ምንም ዋጋ አልነበረውም።ማስረጃ ተብሎ የቀረበው የሚለውና የከሳሽ ጠበቃ የሚናገረው የሰማይና የመሬት ያህል የተራራቁና ተቃራኒዎች ናቸው።ከዚያም በላይ የቪዲዮውና የምስክሮቹ ብዛት የሚያስገርም ነው።ሁሉም ፍሬ የሌለውና መሳቂያ በመሆኑ ያስመዘገበውን ቁጥር በጣም ለመቀነስ ተገደደ። አብዛኛው የሰነድ ማስረጃ የተባለው የሚያስቅ ነው።በበኩሌ እንኳን ማስረጃዎች የተባሉትን ክሶቹንም አላነበብኋቸውም።

የከሳሽ ጠበቃ ክሶቹን ሲያነብ ስሰማው «የትግሬን ዘር ማጥፋትን» ሲያነሳ ደንግጬ ደነዘዝሁ። ይህንን ጽሁፍ የምደመድመውም በዚህ የሚያቅለሸልሸኝ ክስ ነው። የትግሬ ዘር ጭራቅ እንደተነሳበት ለመገመት አያዳግትም። _(እስካሁን ያልገባኝ የትግሬ ዘር ኤርትራውያንንም መጨመር አለመጨመሩ ነው፡)_ ይህ ጭራቅ ግን ከተከሰሱት መሃል እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ።እንኳን በገቢር በኀልዮም ሆነ በነቢብ የትግሬን ዘር በማጥፋት ወንጀል የሚጠረጠር የለም። ቢኖር እኔ በከሳሽ ጎራ እንደምቆም አውቃለሁ።

ኤርትራውያን እብዶች ከዚያም ጠላቶች ተብለው ሲባረሩም ዝም ብዬ አላየሁም፤በዚያን ጊዜ ለዝምድናችን



ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ክብርና መብት ብንቆም ኖሮ ዛሬ የትግሬን ዘር ማጥፋት ብሎ ነገር አይታሰብም ነበር።አንድ ጥፋትን በዝምታ ማሳለፍ ሌላ ጥፋት ያስከትላል።

የወያኔ መሪዎች በሻቢያና በኤርትራ ሕዝብ መሀከል ትልቅ ልዩነት መኖሩን ያለመታከት ይናገራሉ፤ በአንፃሩ በወያኔና በትግራይ ሕዝብ መሃከል ምንም ልዩነት አለ ብለው አያምኑም። ወያኔ ሁሉ ትግሬ ነው፤ ትግሬ ሁሉ ወያኔ ነው የሚል ሰንካላ አስተሳሰብ አለ። ፈረስ ሁሉ እንስሳ ነው እንስሳ ሁሉ ፈረስ ነው እንደማለት ነው።

የቀረበብን ክስ የትግሬን ዘር ለማጥፋት መሆኑ ቀርቶ ወያኔን ለማጥፋት ቢሆንም የሚያቅለሸልሽ እኩይ ወንጀል ከመሆን አያልፍም። ነገር ግን ሌላው ቢቀር ከተከሳሾች ውስጥ ያሉትን ትግሬዎች በማስወጣት የትግሬ ዘር በማለት ውስጥ ያለውን መርዛማ ዓላማ አያጋልጥም ነበር።

የትግሬ ዘር (ኤርትራውያንን ጨምሮ) የኢትዮጵያ መሰረት ነው፤የትግሬ ዘር የኢትዮጵያን ታሪክ ተሸካሚ ነው፤ እንኳን በኢትዮጵያዊነታቸው ያሉትን ትግሬዎች የተገነጠሉትን ለማጥፋት ማሰብ በምድርም በሰማይም ይቅርታ የማያስገኝ ወንጀል ነው። ከኤርትራውያን ጋር የተደረገውንም የወንድማማቾች ጦርነት አጥበቄ የተቃወምሁት በዚህ ምክንያት ነበር። በሰሜን ያሉትን ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ከመቅጽበት ወደባእድነትና ወደጠላትነት ለውጠን አሁን ደግሞ የተረፍነውን አጥፊና ጠፊ አድርጎ መፈረጁ ለማንም የሚበጅ አይሆንም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ ነው ብዬ ከልቤ ስለ-ማምን እንዲህ ያለውን የጥፋት መርዝ ይቀበላል ብዬ አላስብም።ራሱ ሃሳቡ መጸነሱ ብቻ ያሳምማል።

የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ወደጠላትነት ሊለወጥ አይገባም። ምንም እንኳን ፖለቲካ ነበር

ባይባልም ከአለፉት ሁለት ስርአቶች ጋር የፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነት ነበረኝ። ሆኖም እኔ ለመቀበል አልፈለግሁም እንጂ ሁለቱም ሊሻን ሊሸልሙኝ ፈልገው ነበር። በዛሬው ሶስተኛው ሥርአት የፖለቲካ መብቶችን ሁሉ በሕገ መንግሥት ባወጀ ሥርአት ቅንጣት ታህል ማስረጃ ሳይኖረው ልዩ የወንጀል ሊሻን በግድ ለጠፈብኝ፤ ለጠፈብን። ይዋል ይደር እንጂ የወንጀል ሊሻን ለሰኔ አንድ 1997 እና ለጥቅምት 22 1997 ሰማዕታት ገዳዮች ያለበቀል ይተላለፋል።

ክፉውን መልካም፤ መልካሙን ክፉ ለሚሉ ጨለማውን ብርሃን፣ ብርሃኑን ጨለማ ለሚያደርጉ፤ ጣፋጩን መራራ መራራውን ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው!።

ኢሳይያስ 5/30

እግዚአብሔር አእምሮአችንንና ህሊናችንን አጽድቶልን እውነትን ለማየት፤ ፍቅርን ለመቀበልና ተስፋን ለማየት አብቅቶን እንድንተማመን ያድርገን።

ኢትዮጵያውያንና ሌሎችም ጉዳዩ ያሳሰባቸው ሁሉ ከመጮህ አልተቆጠቡም። ሁሉም ከያለበት ይህን ግፍ በተመለከተ ይበጃል የሚለውን ሁሉ እያደረገ ነው። ወያኔ/ኢህአዴግም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የምን ፍትሕ የምን ዕውነት የምን ዴሞክራሲ የምን ሰብአዊ መብት በማለት የሚመቸውን ብቻ እያደረገ ነው።

የቅንጅት አመራሮች አባላትና ደጋፊዎች የሲቪክ ማህበራት አባላት ወንጀለኞች ተብለው ክሱ እንዲመሰረትባቸው ከተወሰነና ከየቤታቸው እየተለቀሙ ወደ ማእከላዊ ሲወሰዱ ምናልባት ለማስፈራራትና አንገተ ሰባራ ለማድረግ ይሆናል የሚል ግምት ነበር። ያ እንዳልሆነና ነገሩ ሌላ መልክ እንደያዘ ሲታወቅ ሁሉም ነገሩ እንዲያበቃ መጠየቁን ተያያዘ። ከነዚህ ይህ ነገር ለሃገርም ለወገንም ለመንግሥትም ከሚጠቅም ይልቅ ሃገሪቱን ወደ ባሰ አዘቅት የሚጨምር፤ የከረረ



ቂም የሚያስቋጥር ስለሚሆን መንገድ ተፈልጎ ስህተቱ ቢታረም ይበጃል ካሉት አንዱ ብርሃነ መዋ ናቸው።

አቶ ብርሃነ ይህን ሃሳብ ሲያቀርቡ መፍቻው ቁልፍ የት እንደሆነ በመለየት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በላኩት ግልፅ ደብዳቤ

«ኢትዮጵያዊ ጨዋነት»ምን እንደሆነ በሚገባ ያስመሰከሩበትን ደብዳቤያቸውን የማንበብ እድል ያላገኙትም እንዲያነቡት ከዚህ በታች አካትቼዋለሁ።

# ግልጽ ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ

## በረከተ መርገም

### የኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

ብርሃነ መዋ
( e-mail- breemewa@gmail.com )

በጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብና በተለይም ደግሞ ልጆችና የልጅ ልጆችም ይሆናሉ።

ይህችን መልእክት ለመጻፍ ስነሳ በቅድሚያ የገጠመኝ ፈተና መልእክቴን ከስሜት ውጭ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለማስቀመጥ እራሴን ለማዘጋጀት ማውጠንጠን ነበር። ምን መልእክት ማስተላለፍ እንደሚገባኝ ከወሰንኩ በኋላ፣ ብእሬን ከወረቀት ጋር ለማገናኘት ብዙ ተጨነቅሁ። ጭንቀቴ የመነጨው እርስዎ ልልዎት ወይንም አንተ ልልህ ለመወሰን ያለመቻሌ ነበር። ምክንያቱም ይህ ደብዳቤ የጠቅላይ ሚኒስተሩ ጠረጴዛ ቆርጥሞት እንዲቀር ሳይሆን፣

በአደባባይ እንዲወጣ በመወሰኔ፣ ሶስተኛ ወገንና ታሪክ በአገላለጼ እንዳይታዘቡኝ በመፍራት ነበር።

እርስዎ ለማለት ኢትዮጵዊነት ጨዋነቴ እና የተቀመጡበት ወንበር ክብር ጫና አሳደሩብኝ። ውስጣዊ ስሜቴ ግን የሰራኸውን ተግባራት አመዛዝኖ፣ በተለይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያሳየኸውን ንቀት ከግምት ውስጥ በማስገባት አንተ እንድልህ አዘዘኝ። ይህ በእኔና-በእኔ መካከል የተፈጠረው የስሜት ትግል አንዱ አሸንፎ እስኪወጣ ረዘም ያለ ጊዜ ወሰደብኝ። ኋላ ግን የስልጡን ፖለቲካ መርህ ከዳመናው በላይ እንዳስብ፣ በቅንጅት መንፈስ ተከስቶ ውሳኔየን ከስሜት ነጻ አድርጎ ቢያንስ ባደባባይ ለአገሬ ክብር ስል እርስዎ እንድል ስሜቴ ተሸነፈ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፤-

የማምንባቸው ጉዳዮች ውስጤን ሲወጥሩኝ እንደአብዛኛው ሰው ከመብከንከን ይልቅ፣ መተንፈስና ላመንኩበት መቆሜ፣ እርስዎንና ድርጅትዎን ቢያስከፋችሁም፣ ውድ አገሬን ለጊዜውም ቢሆን ትቸ እንድሰደድ ቢያስገድደኝም፣ የስብዕናዬ መገለጫ ነውና አንገቴን አልደፋሁም። በዚህ ጽሁፍ ላይ የማሰፍረው ሃሳብ በስሜትና በወገንተኝነት የተበከለ እንዳይሆንብኝ አምላኬን ለምኘዋለሁ። እርስዎንም በክፋትና በንቀት፣ በእልህና በቸልታ ጽሁፉን እንዳያዩብኝ አምላክን እለምናለሁ።

ከጉልበትም ይሁን ከሹመት የመነጨ ስልጣን ከክብርና ከሃይል ጋር መምጣቱን ሁሉም ይገነዘበዋል። ብዙውን ጊዜ የሚረሳው ስልጣን፣አዛዥነትን ብቻ ሳይሆን ሃላፊነትንና ተጠያቂነትንም ያካተተ መሆኑ ነው። በስልጣን ላይ ከተቀመጡበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ጉዳይ፣ የኢትዮጵያውያን እጣ ፈንታ፣ ከርስዎ ስልጣን ጋር እየተጠላለፉ መሄዳቸውን ማንም የሚያስተውለው ነው። እናም የኢትዮጵያ ታሪክ ሲወሳ የርስዎ ስም እየተለጠፈ መገኘቱ አይቀሬ ይሆናል። በአካባቢዎ ያሉት እንደሚያሞካሹዎት ብቻ ሳይሆን



በህሊና የፍርድ ሚዛን ላይ ተቀምጠው፣ በሃሰት ምስክር አማካኝነት ሳይሆን በተጨባጭ መረጃ ይዳኛሉ። ዳኞቹ ተጽእኖ ሊደረግባቸው የማይችሉ የታሪክ ተመራማሪ-ዎች፣ የማውቀውንና የማምንበትን ያህል በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የርስዎ ስልጣንና የስልጣን ተዋረድ፣ በህግና በፍትህ ስርአቱ ላይ ያለዎት የበላይነት፣ በድንጋጌ ሳይሆን በተግባር የሚያስፈራራ ደረጃ ላይ ደርሶአል። ይህ አገላለጽ የስሜቴ ነጸብራቅ ሳይሆን ባንደኛ ደረጃ ያየሁትና ያጋጠመኝ የታዘብኩትና ያረጋገጥኩት ስለሆነ በልበሙሉነት የምገልጸው ይሆናል። ምንም እንኳን ባስተዳደር መረብ ውስጥ ተሸንቁሬ ባልፍተለተልም፣ ያገዛዝ ስርአት ነበልባል ከሚአንገበግባቸው ወገኖች መሃል ሆኘ በወላፈኑ ተገርፌያለሁ። ስለሆነም እርስዎንና አገዛዝዎን በሚገባ አውቄያለሁ ብየ አምናለሁ። የምሰነዝረው ሃሳብ ለኢትዮጵያ መንግስት ሳይሆን በቀጥታ ለእርስዎ እንዲሆን ማድረጌ ያገዛዝዎን ስርአት በመረዳቴና ለማፍረስም ይሁን ለመገንባት ስልጣኑ ያለዎት እርስዎ ብቻ መሆንዎን በመገንዘቤ ነው። ለመፍለጥና ለመቁረጥ ብቻ ሳይሆን ለመቀጠልና ለመገንባትም የርስዎ ይሁንታ ብቸኛ ወሳኝ ነው። ባካባቢዎ ያሉት ሹማምንት የርስዎን ስሜት አይተው፣ ግንባርዎን አንበው የሚያስተጋቡ እንጅ በራሳቸው ለመቆም የሚያስችል ችሎታ ቢኖራቸውም ስርአቱ በራሳቸው እንዳይተማመኑ ተጽእኖ አድርጎባቸዋል። እንደመሳሪያ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን ሹማምንት፣ ዳኞችን፣ የስራ ሃላፊዎችን ከመሰግሰግ ባሻገር፣ ሊያፈነግጡ እንዳይችሉ በጸረ-ሙስና ህግ በመጠቀም ህጉን የሚያስፈጽመውን አካል በግል ለርስዎ ተጠሪ በማድረግ ልጓም አስገብተውላቸዋል። ስለሆነም ከርስዎ ስሜትና ፍላጎት ውጭ፣ የርስዎን ዜማ ከማቀንቀን ባሻገር ሊያስኬድ የሚያስችል ወኔ እንዳይኖራቸው ተቀፍድደዋል። ለዚህ ነው ፍርድ ቤቶችና የፍትህ ስርአቱ ለርስዎ የፖለቲካ መሳሪያ ከመሆን ያለፈ ነጻነት የሌላቸው። ይህንን ስደመድም ከይሆናል በመነሳት ሳይሆን እንደሆነ ስለማውቅ ነው። በስራ አጋጣሚ የታዘብኩት ቱባ ቱባ ባለስልጣናት ሳይቀር ቀላል ጉዳዮችን እንኳን ለመፈጸም

ከተስማሙ በኋላ፣ እርስዎን እያማከሩ ቃላቸውን ሲያጥፉ በመደጋገም ታዝቤያለሁ::

ጥሩ የሰሯቸውን ነገሮች ከሚገባው በላይ አጋነው የሚያጮሁልዎት፣ ደጀ ጠኝዎች፣ ወይም አድርባዮች፣ ወይም ደግሞ እውነተኞች በርካታ መሆናቸውን አምናለሁ:: በአንጻሩ ደግሞ ሲሳሳቱ እርስ-ዎን ቅር እንዳይልዎት ወይም እንዳይቀየሙ በማለት የሚያጨበጭቡልዎት ጥቂቶች እንዳልሆኑ እገነዘባለሁ:: ስለሆነም፣ ሁሌም ትክክል እኔ ብቻ ነኝ ብለው እንዲያምኑ የተገደዱ ይመስለኛል:: ይህን መሰል ስነልቦና በርስዎ ብቻ የተከሰተ ሳይሆን በታሪክ ተደጋግሟል:: እሩቅ ሳንሄድ እርስዎ ከወንበራቸው ያፈናቀሏቸው ኮሎኔል መንግስቱ በብዙ ጉዳዮች ከርስዎ የተለዩ ቢሆኑም በዚህ ረገድ የአንድ ስነ-ስሜት ተጋሪዎ-ች ሆናችኋል:: እነዚህን ጉዳዮች ስዘረዝር የርስዎን ክህግና ክሁሉም በላይ መሆን ለማስረገጥ እንጂ ሰብእናን ለመንካት ወይም ታሪክን ጥላሸት ለመቀባት እንዳልሆነ ይረዱልኝ:: ምክንያቱም ይህን ላደርግ ብዳዳ አበላሸው ይሆናል እንጅ ታሪክ እየመዘገበ ካለው የተለየ ምንም ልጨምር አልችልም::

ወደ ተነሳሁበት ቁምነገር ልመለስና በማንኛውም ስራ ውስጥ ስህተት ሊፈጠር ይችላል:: ስህተት ደግሞ ዋጋ ይከፈልበታል በንግድም ሆነ በፖለቲካ ይህ ዋጋ ኪሳራ ይባላል:: ይህን ለማካካስ ብዙ ማሰብንና ቆራጥነትን ይጠይቃል ::

እርስዎ በተሰማሩበት የፖለቲካ ስራ ባለፉት የስልጣን ዘመን ያጋጠሙዎትን ክስተቶች በሚመለከት የወሰዱአቸው እርምጃዎች የፖለቲካ ኪሳራን አስከትሎብወታል:: እነዚህ በርካታ ክስተቶች ታሪክ ጸኃፊዎች የሚዘረዝሩአቸው ስለሚሆኑ ሁሉንም ለመጥቀስ አልዳዳም:: ነገር ግን ግዙፍ የሆኑና ሊያስተካክሉ ሲገባዎት ያበላሹአቸውን ጉዳዮች እጠቁማለሁ::



1. ከኢትዮጵዊነት በላይ የህወሓት አባልነት እያየለብዎ ባደባባይ የሰነዘሩአቸው ቃላት፤አገራዊ ብሄረተኝነትን በዘረኝነት ለመተካት ያካሄዱአቸው የፖለቲካ እርምጃዎች፤ የኢትጵያን ዘላቂ ጥቅም የሚጎዱ ስምምነቶችና ተግባራት፤ ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አቃቅሮዎት ቆይቶአል:: ስለሆነም ህዝብ በርስዎ ላይ ያለው ስሜት ጎምዛዛ እንደሆነ ይታወቃል:: ይህ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ጦርነት ሊኖር አይችልም ብለው በፓርላማ በይፋ በማረጋገጥ የፖለቲካ ግምትዎን ለትዝብት የዳረጉት ቢሆንም ጦርነቱ ተቀሰቀሰ:: ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ የውስጥ ጉዳዩን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ አድርጎ ለዳር ድንበሩና ለኢትዮጵያዊነት ክብሩ ዘብ ቆመ:: በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የብሄረሰብ አባላት የሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶች አጥንታቸውን ከስክሰው፣ በደማቸው ለውሰው፣ የእርስዎ ፖሊሲ ሊበታትነው ያሰበውን ኢትዮጵያዊነት አጠናክረው ገነቡት:: ይህ እርስዎ ያራመዱት ፖሊሲ የተሳሳተ መሆኑን ብቻ ሳይሆን እራስዎንም እንዲመረምሩ ከኢትዮጵያ ህዝብ የተላለፈ መልክት ነበር:: ፖሊሲ ምልከታዎን እንዲያስተካክሉ ከታሪክና ከኢትዮጵያ ህዝብ የተሰጠ ስጦታ ነበር:: በወቅቱ ከኤርትራ ጦርነት ጋር በተያዘ በትግራይ አካባቢ ያጋጠመትን ቀውስ፣ መንግስታዊ ስልጣንን በመጠቀም የትግል ጓዶች የነበሩትን ግማሹን በመጥለፍ ከፊሉን በማጥመድ አገለሉአቸው:: ለዚህም ምርኩዝ አድርገው የተጠቀሙት ሲንቁአቸው የነበሩትን ብአዴን እና ኦህዴድን ነበር:: የህዝብን አመኔታ ለማግኘት ሊረዳ ይችላል ብለው ያሰቡትን መጠነኛ ለውጥ ለማምጣት ምለው ተገዘቱ:: የመሃል አገር አጋሮች ደጋግፈው ቀና ሲያደርጉዎት እንደገና የኢትዮጵያን ህዝብ ረሱ፣ ንቀትን ቀጠሉ:: ይህ እንግዲህ አንዱ ያጋጠመ የፖለቲካ ኪሳራ ነው::

2. የኢትዮጵያ ህዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈለገውን ፓርቲ የመምረጥ እድል በማግኘቱ ተጠቀመበት፤ እናም የርስዎን ፓርቲ እንደማይጠቀመውና እንደማይፈልገው በድምጹ ጮክ

ብሎ አስመዘገበ፡፡ ዱብ እዳ ሆኖብዎት የተሸፈኑበትን ጭምብል አወለቁ፡፡ የህዝብ ድምጽ ያለበትን ኮሮጆ አስመዘበሩ፣ ድምጽ በጠራራ ፀሃይ እንዲሰረቅ አደረጉ፡፡ የጠበቁት ውጤት ያለመገኘቱን ሲያረጋግጡ አፈናና ጭፍጨፋ አካሄዱ፡፡ ሁሉም የኃይል እዝ በርስዎና በርስዎ ብቻ እንደሚታዘዝ ይፋ አደረጉ፡፡ አስራለሁ አሉ አሰሩ፣ እገላለሁ አሉ ገደሉ ጣት እቆርጣለሁ አሉ ቆረጡ፡፡ እናም የኢትዮጵን ህዝብ የዲሞክራሲ ተስፋ አጨለሙ፡፡ የሰላማዊ ለውጥ ፈላጊዎችን፣ ህዝብ እምነቱን የጣለባቸውን፣ እርስዎ ያሳጡትን ተስፋ ለህዝብ ያሳዩትን የቅንጅት መሪዎች አሰሩ፡፡ ጥፋተኞች መሆናቸውን ባደባባይ ይፋ አደረጉ፡፡ በዚህም ፍርድ ቤቶች አሰራር ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ አደረጉ፡፡ ይህ እንግዲህ አብይ የሆነ የፖለቲካ ክስረት ነው፣ ሊወገድ ይችል የነበረ ክስረት፡፡

3. የሃሰት ምስክር አስመሰከሩ፡፡ ምስክሮቹ ተጋለጡ፡፡ በታሳሪዎች ላይ አስተዳደራዊና ስነልቦናዊ ተጽእኖ አደረጉ፣ አንገላቱ፡፡ የፍትህ ስርአቱን የፖለቲካ መሳሪያነት ለሃፍረት፣ ለትዝብት አጋለጡት፡፡ ጥፋት ፈጥረው፣ ማስረጃ ጠፍጥፈው፣ የታሳሪዎችን መረጃ የማግኘት መብት ረግጠው፣ የጥፋተኛነት ውሳኔ አስወሰኑ፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ፍትህ ስርአት እርቃኑን ቀረ፣ አለም ጉድ እስኪል፡፡ ይህም ሊወገድ ይችል የነበረ የፖለቲካ ክስረት ነበር፡፡

4. ከላይ የተጠቀሰውን ሁሉ ሊሽር የሚችል የፖለቲካና ሰላማዊ መፍትሄ ማግኘት በእጅጉ ቀላል ነበር፡፡ የታሪክ ጠባሳን ማጥፋት ባይቻልም እንዳይሰፋ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡ ይህን ከማድረግ ይልቅ ቀዳዳዎችን የሚያሰፋ፣ የጎመዘዘውን የህዝብ ስሜት እንዲመር የሚያደርግ፣ ሰላምን የሚፈታተን እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀትዎ ተሰማ፡፡ በቅንጅት፣ በጋዜጠኞችና በንጹሃን ተቀናቃኞች፣ በዲሞክራሲያዊ ምሁራን፣ በሰላማዊ ትግል ሊቃውንት፣ በህዝብ ተስፋ ላይ ሊፈርዱ ተዘጋጁ፡፡ እናም በጠቅላላው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሊፈርዱ አንገቱን ሊያስደፉ፣ ስሜቱን



ሊያኮላሹ ተዘጋጅተናል አሉ ባለሚሎችም፡፡ ይህ ደግሞ ለከባድ ፖለቲካ ኪሳራ መዘጋጀት ነው፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር!

*ሥጋቴን ልግለጽልዎ*፣ ይህ የመጨረሻው ኪሳራ፣ በግፍ በታሰሩ የቅንጅት መሪዎች ላይ ቅጣት መወሰን፣የፖለቲካ ኪሳራ ብቻ ሆኖ የሚቀር ጉዳይ አይሆንም፡፡ የአገርም፣ የሰላምም፣ የሰላማዊ ለውጥ ፍላጎትም፣ የህዝብም ተስፋ ኪሳራ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡ መዘዙ እንደቆላ ቁስል ያመረቅዝና፣ እንደ ነቀርሳ ይራባና፣ እንደሰደድ እሳት ይቀጣጠልና፣ ሁላችንንም ይለበልበናል፣ ያሰቃየናል፡፡ እናም ይህችን ሃገር ይታደጓት፣ የልጆችዎን አንገት አያስደፉ፡፡ ፍርድ ቤት-ም፣ ፍትህን፣ አገርን እኛ ሁላችንን አያሳፍር፡፡ መሰላል ላይ ለመውጣት ብዙ እርከኖችን መሻገር ያስፈልጋል፣ ከመሰላል ለመውደቅ ግን አንድ መጥፎ እርምጃ በቂ ነው፡፡ ይህን መጥፎ እርምጃ አይሞክሩት፣ እናም ፋይሉን ዘግተው ምንም ምን ይሁን ምክንያት ፈጥረው ተከሳሾችን ያሰናብቱ፡፡በዚህም ለዚህች አገር አንድ ቁምነገር ሰርተው የኢትዮጵያን ህዝብ ከሰቆቃ ያውጡ፡፡

አምላክ ሆይ ኢትዮጵያን ጠብቃት !

በዚህ ዓይነት በርካታ ደብዳቤዎች፣ የኢንተርኔት መልእክቶች፣ ፋክሶች፣ የተወካይ መልእክተኞች፣ ከየሃገሩ እየመጡ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ተፋጠጡ፡፡

## የፍርድ ሂደቱ.........

የተለያዩ የውጭ ሀገር መልዕክተኞችና ተወካዮች፣ «ጉዳዩ የፍርድ ቤት ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ጉዳይ ነውና የፖለቲካ መፍትሔ ይሰጠው ለዚህ በርዎ-ን ይክፈቱ፣ ካልሆነ አመራርዎ በዓለም ሕብረተሰብ ዘንድ ጥላቻን እያተረፈ ነው፡፡ በኛም በኩል የሕዝቡን መብት ለማያከብርና ሕዝቡን በጭቆና ውስጥ ለሚገዛ መንግሥት እርዳታ ለመስጠት በጣም የሚያስቸግረን

ሆኗል» የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥተው ሲሄዱ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የሚቀርበው ዘገባ ግን ሌላ ነው።

«ከ.. .. .. .. .. ቦታ የመጡት የከፍተኛ ባለስልጣን ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ተገናኝተው ባካሄዱት ውይይት ለጠ/ሚኒስትሩ ያላቸውን አክብሮት፤በሃገሪቱ ላይ የሚታየው የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት አከባበር በአፍሪካ ቀደምት ሥፍራ የሚሰጠው ነው። ሃገሪቱ በጥቂት ጊዜ አድጋና ለምታ ለሌላው ዓለም የምትተርፍ ትሆናለች ብለው እንደሚያምኑ የአበባ እርሻ ከጎበኙ በኋላ ሃገራቸው የሚሰጠውን እርዳታ አጠናክሮ እንደሚቀጥልበት ገልጸዋል» የሚል ሆኖ ይደመጣል፤ ይነበባል። ያም ሆኖ ይህ ሁሉ የሚነገረው በጋዜጠኛው አንደበት እንጂ አሉ የተባሉት እንግዳ ድምጻቸው አይሰማም። አማርኛ ስለማይችሉ እንዳይባል በእንግሊዝኛውም ዜና ላይ ሲናገሩ አይሰማም። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በየቀኑ የምንሰማውና እንደመዝናኛ አድርገን የምናየው ነበር።

በቀይ ሽብር ተፋራጆች ዞን ከገባንበት እለት ጀምሮ ስፖርት ከመሥራትና መጻሕፍት ከማንበብ ባሻገር በአጋጣሚው ሁሉ ከደርግ ባለስልጣናት ጋር እንነጋገር ነበር። ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ያለፈውን ሁሉ ትተው ፊታቸውን ወደ እግዚአብሔር መልሰዋል፣ ይጸልያሉ። በግል ከሚያደርጉት ባሻገር በአንድነት ሆነው በየእለቱ በሚውሉት መላእክትና ቅዱሳን ቀናት ጸሎታቸውን በሚገባ ያካሂዳሉ፤ እኛም የዚሁ አካል ሆነን ነበር። ፀሎቱን በየተራ ይመራሉ፣ በየተራ ያስተምራሉ። እነዚህ የቀድሞ ባለስልጣናት በዚያን ጊዜ ያደረጉት ሁሉ "ልክ ነው" ባይሉም ያደረጉትን ሁሉም ስህተት ነው አይሉም። ይህ ነበር የውይይታችን ርእስ። በብዙ ነጥብ ላይ መተማመን ደረጃ ደርሰናል።

የእነዚህ ተከሳሾች የፍርድ ሂደት እየተጓተተ ቀጠሮ መስጠት የማይቸግረው ፍርድ ቤት ቀጠሮውን እያራዘመ ያሻግረዋል። ይህን ስንሰማና ስንት ቀጠሮ እንደተሰጠ በምን ያህል የጊዜ እርዝመት እንደተቀጠረ



ስንሰማ የኛም እንደዚያው ሊሆን እንደሚችል ሁኔታው አስገንዝቦናልና ዝግጁ ነበርን።ምንም ቢመጣ የቆምንለት ዓላማ ሕዝባዊና ትክክለኛ በመሆኑ ምንም ቁጭት የለንም።ወደ ኋላ ተመልሰን ምነው ባላደረግነው የምንለው አንዳችም ነገር የለም። በሰላማዊ መንገድ የሄድንበት አቀጣጫና የተከተልነው የሰለጠነ ፖለቲካ አካሄድ ትክክለኛ ነው፤ ስህተት የሠራው ተቀናቃኞችን ገዢው ፓርቲ ይህን መንገድና አካሄድ አለማወቁ ነው። ልዩነታችን ይህ ነው።

እኛ ታሥረናል፤ ሕዝቡ ታፍኗል፣ ያውም በጦር መሳሪያ፤ ትግሉ ግን ቀጥሏል። አሁን በሃገራችን መቼም ታይቶ የማይታወቅ የዴሞክራሲ ፍላጎትና ለዚህም የሚያስፈልገውን ለማድረግ ዝግጁና የዴሞክራሲ ታጋይ የሆነ ሕዝብ ተፈጥሯል። ይህን ማጥፋት ሳይሆን በማስፈራራት ማቆም ጨርሶ አይቻልም ያ ጊዜ አሁን አልፏል። ኢትዮጵያዊ ሁሉ፤ በዴሞክራሲ የሚያምን ሁሉ በአንድነት ቆሞ በመታገል ላይ ነው። በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን በሃገራቸው ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ እስከዛሬ ከነበረው እጅጉን በጠነከረ መልኩ እየታገሉ ነው። ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውን፣ ሃብታቸውን፣ እውቀታቸውን ሁሉ ለዚህ ሕዝባዊ ዓላማ እየከፈሉ ነው። በሃገር ውስጥ ለሚደረገው እንቅስቃሴና ለሚታገለው ሕዝብ ጋሻና መከታ እየሆኑ ነው። ስለዚህ ፍርዱ ይጓተት፣ ይዋል ይክረምም የተጀመረው ሒደት ውጤት ያመጣልና በዚህ እንበረታታለን።

በቃሊቲ ማረሚያ ቤት አሁን እኛም ባለንበት ሆነ በሌሎች ዞኖች ሁሉም ለጊዜ ማሳለፊያም ለገቢ ማግኛም እንዲሆናቸው አንዳንድ ሥራዎችን ይሰራሉ። ጥሪት ያላቸው ወይም ባላቸው ቤተሰቦቻቸው የሚደገፉ ከነሱ የባሱትን ታሳሪዎች በመቅጠር አንዳንድ ሥራዎች በማሰራት ሥራ ፈጥረውላቸዋል። ልብስ ማጠብ፤ የምግብ ሰሃን ማጠብ፣ ምግብ ማሞቅ፣ ጠዋት ሻይና ዳቦ ተቀብሎ ማምጣት።

ከዚህ በተለየ ደግሞ የራሳቸውን ሥራ እየሠሩ ገቢ የሚያገኙም አሉ:: ጸጉር ማስተካከል፤ ልብስ መተኮስ፤ መቋሚያና መስቀል፣ ከዘራ፣ ረከቦት፣ መቁጠሪያ፣ የአንገት ጌጥ፣ የፎቶግራፍ ፍሬም፣ ትናንሽ ጠረጴዛ፣ ጉትቻ፣ የባህል እቃዎች፣ መሶብ፣ አገልግል፣ ጀበና.. .. .. የሚሰሩ አሉ::

የቆዳ ውጤቶች እንደ የሴት ቦርሳ፤ የወንድ ቦርሳ፤ ከሸራ የሚሰራ የልብስ መስቀያ ቦርሳ፤ የጉዞ ቦርሳ /ከሸራም ከቆዳም እንደምርጫ/፤ ለተለያየ ጉዳይ የሚውሉ የቆዳ ስራዎች፤ አዲስ ሙሉ ልብስ ካኪ፤ ሱፍና ሌላም፤ በያይነቱ የሥራ ዘርፍ ፈጥረው እራሳቸውም ተጠቅመው አገልግሎትም ይሰጣሉ::

እኛ በነዚህ ሥራች ውስጥ ለመሳተፍ ገና ስልጠና ያስፈልገናል አሁን ያለነው በአገልግሎት ተቀባይነት ነው:: ቀጥታ የምንሳተፍበት ነገር ቢኖር በቀይ ሽብር ተፋራጆች ዘንድ እያለን በጸሎቱና በክበቡ ተገልጋይነት፣ በካርታ ጨዋታ፣ በቢንጎ ጨዋታ፣ አሁን ደሞ በኮረንቦላ ጨዋታ፣ በዳማ፣ በቼዝና በግቢው ውስጥ በሚሰሩ አንዳንድ የእንጨት ፍልፈላ ዕቃ ገዢነት ነው::

ለነገሩ መስራት እንሞክር ብንልም ለቅንጅት ታሳሪዎች የሚፈቀድና የማይፈቀድ ተብሎ የተለየ ስላለ መሥራት አይፈቅዱልንም:: በግቢው ውስጥ ለአንዳንድ ሥራ ማስታወቂያ ይወጣል:: በወህኒ ቤቱ ደንብ ፍርደኛ ያልሆነ ማንም በማስታወቂያው ላይ በተገለጠው መካፈል አይችልም:: በተግባር እንደሚታየው ግን ገና ወህኒ ከመጣ ሳምንት ያልሞላውም የማስታወቂያ እወጃው ተካፋይ ይሆናል::

ትምህርት ለመማር የምትፈልጉ በግቢም ውስጥ የተልእኮም ትምሕርት ተብሎ ማስታወቂያ ወጣና የቅንጅት ታሳሪዎች የተልእኮ ትምህርት እንፈልጋለን ብለው ተመዘገቡ:: ለምዝገባው "አይሆንም፣ አይቻልም" አልተባሉም:: ቆይቶ ጊዜው ሲደርስና የተመዘገቡት እየተጠሩ ይህን አሟሉ ይህን አምጡ ሲባሉ የቅንጅት



ታሣሪዎችን "ይሆናልም" የለ፤ "አይሆንምም" የለ ዝም ነው:: ምነው ብለው ሲጠይቁም ጠብቁ ነበር የሚባለው:: ትምህርቱ ለሌሎች ተጀምሮ ጠብቁ ማለት ከንቱ ልፋት ሆነ:: በግቢው ያለው ደንብና መመሪያ የዞን ሃላፊ ሆኖ በሚመጣው ሃላፊ ፍላጎትና አመለካከት የሚወሰን ነው:: በዞን 5 የተለያዩ ሃላፊዎች ተቀያይረዋል:: ሁሉም የተለያየ ህግ ነበራቸው:: አብዛኞ ዎቹ ህጋቸው ተቀራራቢ ቢሆንም የግል ባሕሪያቸው ግን ይለያያል:: ያ ደሞ ለእኛ ያላቸውን አመለካከትም የተለያየ ያደርገዋል::

አንዱ «እኔ ስለፖለቲካው ጉዳይ የለኝም ከናንተ ጋር ያለኝ ግንኙነት እናንተ እስረኞች ናችሁ እኔ ጠባቂና ጉዳያችሁን የማስፈጽም ነኝ:: ከዚህ ውጪ በጠላትነት የምንተያይበት ምክንያት የለኝም» ይላል፣ ትንሽ ውሸት፣ ትንሽ ቅጥፈት፣ በጣም ትንሽ እውነት:: ሌላው ደግሞ እዚህ ግቢ ውስጥ መግባትም፣ ከኛ ጋር መተያየትም አይፈልግም:: ከእስረኛው መሃል ለተመረጡት ሃላፊነቱን ሰጥቶ ጠዋት እንደነጋ በሩን ያንኳኳና ሪፖርት አቀብሉኝ ብሎ ይሄዳል:: ፊት ለፊት የምንገናኘው ቅዳሜ ወይም እሁድ ተረኛ ከሆነ ነው:: ችግር ሲኖረን በዚያው በእስረኞች አስተዳደሮች በኩል ይደርሰዋል፤ የሚችለውን ያደርጋል፣ መልሱን ግን ማግኘት ብዙ ጊዜ ይወስዳል::

ሌላው እንደመጣ ከኛ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጠረ:: ምን ልፍጠር? ምን አማራችሁ? ይለን ነበር:: ድንገት አንድ ቦታ ላይ ምን እንደተፈጠረ አናውቅም ተለወጠ:: አይናችሁን አልየው ማለት ጀመረ:: ከሌላ ዞን በፊት ያለምንም ችግር በሌሎች እስረኞች እያስገዛን ለመታሰቢያ እናስመጣ የነበረውን ቅርጻ ቅርጽ ጨርሶ እንዳይመጣ የሚል ትእዛዝ አወጣ:: ግቢያችን በሱው ጥያቄ ፍተሻ በዛበት፤ ምንም ላይገኝ:: ጭርሱን ይባስ ብሎ በግቢው ውስጥ ተላላኪዎች ወረቀት እያወጡ ያደርሳሉና ሁሉም ከግቢ ሲወጣና ሲገባ ይፈተሽ የሚል ህግ አወጣ:: ከኛ ጋር ተካፍለው ምግብ የሚበሉትን እየገረመመና በዐይኑ እየገላመጠ አስጨነቃቸው:: በመጨረሻው ላይ አንዳንዶቹን "ለምን ትወስዳላችሁ?

መንግሥት የሚያቀርበው ምግብ እየተበላሸ ነው" ሲላቸው፣ "ያንን እንድንተው የዛን አይነት ምግብ አስመጣልን፣ አለዚያ ተወን" አሉት። የእስረኛ አስተዳዳሪዎችንም ስለዚህ ጉዳይ አንስቶባቸው ምን ችግር ፈጠረብህ ምግቡን እኮ ሲተርፍ ከመጣል በስተቀር ሌላ የሚደረግ የለምና ምናለበት ወስደው ቢበሉ? አይሆንም ካልክ ደም አንተው ንገራቸው እኛ ግን አናምንበትም ከማለትም አልፈው ሁሉም ባሉበት ስብሰባ ይደረግና አንስተህ እንወያይበት ስለአሉት አንጀቱ እያረረ አፉን ዘግቶ ዝም አለ።

ከሁሉም የዞን ሃላፊዎች፣ የሚሰራውን የማያውቅ ለምንም ሥራ የማይሆን የኢህአዴግ ሹመኛ እሱ ነው። ሁል ጊዜ ሲያወራ ጎንደር ትውልዴ መንደር ሳርስ፣ ስቆፍር፣ ከብት ስጠብቅ፣ ቆንጆ ነበርኩ፣ ጀግና ነበርኩ፣ አንበሳ ነበርኩ፣ እያለ መቀባጠር ነው። ሁሉም በባላገር እድገቱ አርሷል፣ ቆፍሯል፣ ከብት ጠብቋል፣ የሱ ልዩ ሆኖ ለምን እንደሚወራ እንኳን እኔ እራሱም የሚያውቀው አይመስለኝም።

የሄ ሃላፊ አንድ ልዩ ባሕሪ አለው።ከማንም የማይገጥም።ሁል ጊዜ ወደዞኑ ገብቶ መጣጠቢያ ቤት ደርሶ ሲመለስ ከኋላም ከፊትም መቀመጫው አካባቢ በተለይ ሱሪው ስለሚረጥብ በጣም ይገርመናል።አንድ ቀን ሚስጥሩን ማወቅ ፈለግንና እኔ ወደቢሮ ለሌላ ጉዳይ እንደገባ ሆኜ ልክ ከመታጠቢያ ቤት እንደተመለሰ ገባሁ።ስለ ህክምና ጠየቅሁትና እሺ ክሊኒክ ትሄዳለህ ብሎኝ እያለ ሱሪህ ረጥቧልና አስተኩሰው» አልኩት።

«ኦ ምን መሰለህ» አለኝ «ጠዋት ጠዋት በአካባቢያችን ውሃ ስለሌለ እዚህ ነው የምታጠበው ታዲያ ስጣጠብ ውስጥ ሱሪዬን አላወልቀውም ለዚህ ነው አሁን ይደርቃል» አለኝ።የሚገርም ስልጣኔና ጽዳት ነው።



የምስክሮች መሰማት ጉዳይ ቀጥሎ አሁንም የፖሊስ አባላት የምስክርነት ቃላቸውን አስመዘገቡ። በመሃል ፕሮፌሰር መስፍን አንድ ጥያቄ አነሱ

«ለመሆኑ የነውጡን ስፋትና መጠን ከየት ተነስቶ ነው የት የደረሰው? ስንት ተሳታፊ የነበረበት ነው? በየት በኩል የመጣው ከየትኛው ጋር ተገናኘ? በማለት ሲጠይቁ አቃቤ ሕግ «ይህ አግባብነት የሌለው ጥያቄ ነው ሊመልሱ አይገደዱም ሞያቸውም አይደለም» ሲል ዳኛው ጥያቄው እንዲመለስ ፈቀዱ። ፖሊሱ ለዚህ የሰጠው መልስ የጥጋብና የማንአለብኝነት መልስ ነው።

«ይህን አናውቅም በዚህም ላይ ጥናት አላደረግንም ምናልባት ይህን የሚያውቀው ያሰማራ ነው ያሰማራ ካለ ሊመልስ ይችላል» ብሎ በመቀናጣት መለሰ። ዳኛውም ለዚህ አንዳችም ተግሳጽ አላደረጉም። አቃቤ ሕግ ግን በዚህ ከሥርአት በወጣ አመላለስ መደሰቱን በሳቅ ባይሆንም በደረቀ ፈገግታ ሊያሳይ ሞክሯል።

ከዚህ ሌላ ቀርበው የነበሩት ምስክሮች አንባቢ እንዲገነዘበው ያህልና ምን ያህል ክሱ በሃቅ ላይ ተመስርቷል ወይስ የፈጠራ ክስ ነው የሚለውን ለመፍረድ እንዲችል አቀርበዋለሁ። ምስክሮቹ ከአርበኞች ግንባር በፈቃዳቸው ከድተው እጃቸውን የሰጡና የተማረኩ ናቸው ተብለው ነው የቀረቡት። ሲመሰክሩም

"የአርበኞች ግንባር አባላት ነበርን ሥልጠና የተሰጠን በኤርትራ ውስጥ ነው፤ አብዛኛውን ወጪ የሚሸፍነው የኤርትራ መንግሥት ነው። አለቆቻችን ከእንግዲህ የቅንጅት አቋም አቋማችን መሆኑን አምነን ለዚሁ ትግል አጋር መሆን አለብን ይህ በበላይ አመራር ተወስኗል። ሶስት የሚሆኑ የቅንጅት አመራሮች ኤርትራ ድረስ መጥተው መግለጫ ሰጥተውናል፣ ወደፊትም ግንባሩን በአስፈላጊው ሁሉ እንደሚረዱ ቃል ገብተውልናል። ከነዚህም አንዱ ብርሃነ መዋ ሌላው

እንዳርጋቸው ጽጌ ሲሆኑ ሶስተኛውን አላውቀውም። የሚሉ ናቸው፤ በአብዛኛው።

የአንዳርጋቸው ጽጌ መጽሐፍ ሽያጭ ለቅንጅት እንዲሆን በስጦታ መልክ መበርከቱ እንደ አንዱ ማስረጃ ሆኖ ቀርቧል። የዶ/ር ነገደ ጎበዜም መጽሀፍ ስጦታም አልነበረም፣ ብቻ መጽሐፉ በምን መነሾነት እንደሆነ ባይታወቅም በማስረጃነት ቀርቧል።

አቃቤ ሕግ እንግዲህ ይህን በመሰለ ክስ መስርቶ ምስክሮች ቆጥሮ፣ ማስረጃ የሚለውን አቅርቦ 21 ወራት ፈጅቶ ያስፈረደውና፣ ያም የተሰጠው የዕድሜ ልክ ፍርድ አልበቃ አላጠግብ ብሎት የሞት ፍርድ የጠየቀብን።

ጠላን፤ አላማርነውም። ጀግንነቱስ በምን ይታይለት? ምናልባትም አቃቤ ሕጉ፤ የፍትህ ሥራ ሰርቶ ስለማያውቅና ወደፊትም ይህን የመሰለ እድል ስለማያገኝ የሞያ ድህነት ስላለበት ከጥፋት፤ ከተንኮል ሌላ ምን ይጠበቃል?

አቃቤ ሕግ አንድ ያነሳውና ያልተባለውን ያለበት ጉዳይ እንመልከት። ጋሼ መስፍን (ፕሮፌሰር) በቴሌቪዥን ክርክር ወቅት፣ «ሕገ መንግሥቱ ካካተታቸው አንቀፆች ከ30 በላይ የሚሆኑት ስለ መብት የሚደነግጉ ናቸው። ሕገ መንግሥቱ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችን በሚገባ ያካተተ በመሆኑ ችግር የለበትም። ችግሩ በተግባር በሚውልበት ጊዜ የተርጓሚዎች ወይንም ተግባራዊ የሚያደርጉት ኃይሎች የሚፈጥሩት ችግር ነው። ከዚያ አኳያ ስንመለከተው አተገባበሩ ሕገ አራዊት ያደርገዋል» አለ። አቶ በረከት ቱግ አሉና «ሕገመንግሥቱን ሕገ አራዊት አለው» አሉ።

በመድረኩ ላይ የነበሩት የቅንጅት ሌላው ተናጋሪ፣ «እባካችሁ፣ ረጋ ባለ መንፈስ ህሊናችንን እየገዛን እንነጋገር» ሲሉ፤



ጋሽ መስፍን «እነዚህ ሰዎች የህሊና ብቻ አይደለም፣ የጆሮም ችግር አለባቸው። የሚሰሙት እኔ ያልኩትን ሳይሆን መስማት የሚፈልጉትን ብቻ ነው። «ሕገመንግሥቱ ሕገአራዊት ነው» ያለው አሁን አቶ በረከት ነው። እኔ ያልኩት ሕገመንግሥቱን የሚተገብሩት ሰዎች ወደተግባር ሲተረጉሙት ሕገአራዊት ያደርጉታል ነው» አለ። አቃቤ ሕግ ለክሱ «ሕገ መንግሥቱን ሕገ አራዊት አሉት» አለና ክስ መሠረቱ።

ከዕውነት በራቀ መልክ ክስ ማጠናከርያ ወይም ወንጀለኞች ለማድረግ የተሰበሰበ በርካታ ነበረ። «ሕገመንግሥቱን ሊንዱት ነበር» ተብለን የተወነጀልን ሰዎች ወንጀላችን ምርጫ ከማሸነፍ ሌላ ምንም ወንጀል የለውም። ምርጫ ማሸነፍን ደሞ ሕገ መንግሥቱ ወንጀል አይለውም ምርጫ ማሸነፍን ወንጀል የሚያደርገው ተደፈርኩ የሚል ጉልበተኛ ወገን ብቻ ነው። አቃቤ ሕግ የጉልበተኛ አጋር ሆኖ ነው ሕግን የተረጐመው። ከዚህ አይነት የፍርድ ሂደት ምን ሊጠበቅ ኖሯል?

አምባገነኖች ሕዝብን እንደባሪያ እነሱ እንደቅኝ ገዢዎች የሚጠቀሙበት ዋነኛ መንገድ የህዝብን ሕሊና ፍርሃት ውስጥ በመጨመር ነው። በቅድሚያ የሚያስቡለት፣ የሚቆረቆሩለት በመምሰል ትናንሽ ጥቅሞቹን እያከበሩ፣ ሕብረተሰቡ በነዛ ጥቃቅን ጥቅሞች ላይ ተመስርቶ ብዙ እንዲጠብቅ ካደረጉት በኋላ እነሱ የሚቻላቸውን ያህል ጉዳት ያደርሳሉ። ለምን ብሎ የሚነሳን ሃይል በማሰር በመግደል፣ ቤተሰቡን በመበተን፣ ለሌላው ትምህርት እንዲሆን ያደርጋሉ።

ይህን የተመለከተ ሕብረተሰብ ደሞ ትንሽ ትንሽ መፍራት ይጀምራል። ያን ጊዜ አምባገነኖች ትንሹ ፍርሃት ላይ በመንጠልጠል ትላልቅ ፍርሃቶች ይፈጥራሉ፤ ለዚህ የሚሆናቸውንም መሳሪያ በገፍ ያዘጋጃሉ። መሣሪያዎቹ የደህንነት ሃይል፤ ወህኒ ቤት፤ በየቦታው በገፍ የማሰር መብት ለተወሰኑ የቡድን አባላት መስጠት፤ የፍትህን ሂደት ለራስ በሚጠቅም

መልኩ ማዋቀር፤ በፖሊስ ኃይሉ ውስጥ የራስ የሆኑ ወሳኞች ማስቀመጥ፤ የሌለ ቀውስ ያለ በማስመሰል አዳዲስ ህጎችና ደንቦች በሕዝቡ ላይ ማውጣትና መተግበር የመሳሰሉት ሁሉ ተዳምረው ሕዝቡ መብቱን እንዳይጠይቅ አፍነው ይይዙታል፣ ፈሪ ይሆናል:: በየአቅጣጫው ጥቂት ጥቂት ፈሪዎች በመፍጠር አጠቃላዩን ሕብረተሰብ ፈሪ ያደርጋል:: አምባገነኖች የፈሪ ሕብረተሰብ መፈልፈያ ፋብሪካዎች እስኪሆኑ ይህንኑ ተግባር ይቀጥላሉ:: ግድያውን ጫን፤ ኑሮውን ወደድ፤ ከማድረጉ ባሻገር እስራቱን በገፍ፤ ያካሂዳሉ::

ሕዝብም የሚያደርገው ሲጠፋው የባሰ አታምጣ እያለ ከሁሉም በከፋውና በባሰው ላይ ሆኖ የባሰ እንዳይመጣ ይጸልያል:: ወደፈጣሪው አቤቱ የባሰ አታምጣብኝ ማለትን አማራጭ የሌለው መፍትሔ ያደርገዋል::

በሃገራችን በሁሉም መስክ የታየው ይሄው ነው:: ሕዝቡ ግን ፈርቶ ስለበቃውና ከዚህ የባሰም እንደሌለ በመረዳቱ፣ የመጣው ይምጣ እንጂ ከእንግዲህስ በፍርሃት መብቴን አላስነካም፣ ብሎ ታጥቆ የተነሳው::

አቃቤ ሕግ ደግሞ ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው የቅንጅትን አመራሮች፣ ነጻውን ፕሬስና የሲቪክ ማሕበራት መሪዎች ለሞት ፍርድ የተመኛቸው:: ሕዝቡ መሪ ሲያጣ አርፎ ይገዛል አይነት አካሄድ ነው:: ሕዝቡ ግን በቃኝ ማለት በቃኝ ነው ብሎ አሻፈረኝ አለ:: ለመሪዎቹ መፈታት ተሟገተ፤ለፍትህ ሉአላዊነት ጥብቅና ቆመ::

በሃገራችን ታሪክ ታይተው የማይታወቁ አዲስ ባህል ተብለው የሚጠቀሱ ጉዳዮች አሉ:: የመጀመሪያውና አስገራሚው በግንቦት 7 ቀን የተካሄደውን ምርጫ በተመለከተ ሕዝቡ አንዲት ድምጽ ያላትን ዋጋ በመረዳት ለዚያች ድምጽ የሰጠው ዋጋና ያገኘው ውጤት ነው::



ሁለተኛው አንዲት የምርጫ ካርድ እንግዛህ ላሉት መሸጥና በድጎማ ተታለህ እኛን ምረጥ ሲባል፣ ያን ከማደርግ ሞቴን እመርጣለሁ በማለት በድምጹ ላይ የወሰደው ቆራጥ አቋም ነው:: ሌላው ከምርጫ በኋላ በተፈጠረው የካርድ ዝርፊያና ጉልበተኝነት ላይ ሕዝቡ የወሰደው ውሳኔ ነው:: በዚህ ውሳኔው የዴሞክራሲ ጠበቃ፤ ተሟጋች በመሆን የተፈለገው ጦር ቢመዘዝ የመብታችን ጉዳይ ነውና ነጻነታችንን አሳልፈን አንሰጥም በማለት ለዴሞክራሲ የቆመበት የጥቅምት 22 አዲስ ክስተት ነው::

አባቶች ሲተርቱ «በጥቅምት አንድ እሸት» ይባል ነበር፣ በዘመነ ኢህአዴግ በ98ቱ ጥቅምት ግን «በጥቅምት እስራት» ነው የተባለለት:: እንደ እውነቱ ከሆነ ወህኒ ቤት መግባት መጥፎ ነው:: መጥፎነቱ የአንድ ሰው ነጻነት፤ ሰብአዊ መብት፤ ዴሞክራሲ፣ ሙልጭ ብሎ ጠፍቶ እንደ ክብት ያውም ሊሰለጥን እንደማይችል ክብት የሚነጠቅበት ቦታ ነው::

እያንዳንዱ የዞን ሃላፊ አልጋወራሽ ነው ለዚያ ላለበት ዞን:: ለምን ንጉሥ አልሆነም ቢባል ንጉሶቹ ከሱ በላይ በቢሮ ተቀምጠው በየጊዜው ከዞን ሃላፊው ሪፖርቱን እየተቀበሉ አስረኛው ምን ይደረግ ብለው የሚወስኑት ስለሆኑ ነው:: እኔ ብዙ የዞን ሃላፊዎች አይቻለሁ፣ አንዳንድ የዞን ሃላፊዎች በእውነት የክብት ጠባይ ያላቸው ናቸው:: አንዳንዶቹ እስረኛ ማለት እቃ የሚመስላቸው አሉ፤ እስረኛ አድርግ የተባለውን ብቻ የሚያደርግ፣ ራሱ ሕልውና የሌለው አድርገው ያዩታል:: አዋቂ በሆኑት ስለሚቀኑና የበታችነት ስለሚሰማቸው እሱን ለማዋረድ ይቸኩላሉ፤ በመጨረሻው ግን ተዋርደው የሚቀሉት እነሱ ናቸው::

በወህኒ ቤት 5 ዓመት ታስሮ ገና ውሳኔ ያላገኘ ብዙ ነው::2 ዓመትና ከዚያም በላይ ታስሮ ፍርድ ቤት ጨርሶ ያልቀረበም በሽ ነው:: 7 ዓመት 9 ዓመት ታስሮ ፍርድ ቤት ቀርቦ ነጻ የሚባልም በርካታ ነው:: ያም ሆኖ "ተመስገን" ብሎ፣ ታሳሪ ጓደኞቹም እንኳን ደስ አለህ" ብለው ይጋብዙታል፣ ይሸኙታል:: አንዳንዱ 9

ዓመት ታስሮ ነጻ ተብሎ እንደገና መፈቻ ስላልመጣለት ወይም በሌላ ምክንያት በትንሹ 2 ሳምንት የሚቆየው ከምንም በላይ ያሳዝናል።

በአስገድዶ መድፈር ተከሰው በወህኒ ቤት ያሉ በርካቶች ቢሆኑም የአንድ ሁለት ተከሳሾች እንቆቅልሽ ሆኖብኛል። አንዱ የአይነስውሩ የአሸናፊ ጉዳይ ነው።ቤቱ ወደ ሳፍቶ ገደማ ሲሆን አስገድዶ ደፈረ የተባለው ደሞ አውቶቡስ ተራ ፤ አልቤርጎ ውስጥ ነው። አልቤርጎ ለመያዝ ማወቅን ይጠይቃል፤ ተደፈሪዋም ከሰፈሯ አውቶቡስ ተራ ድረስ ስትሄድ ተገዳ ከሆነ በየመንገዱ ላይ ያለው ሰው ሁሉ ጉዳዩን ስለሚያይ ብትጮህ የሚደርስላት አታጣም። አልቤርጎውንም ሲይዙ በስምምነት ካልሆነ በስተቀር ለገንዘብ ተቀባዩ ወይም ለአልጋው ክፍል ብትናገር ሊያድኗት ይችሉ ነበር። አሸናፊ "ሴትዮዋ በስምምነት አብራው ታክሲ አስቁማ ከፍላ፣ ሰው እንዳያይ ብላ ራቅ አርጋ ወስዳው ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ በሌላ ጉዳይ በተፈጠረ አለመግባባት ነው ክስ የተጀመረው፤ ከዛም ተሰሚነት ስላላት አሳሰረችኝ" ነው ያለው።

ሌላው የተሰማ ጉዳይ ነው። ተሰማ በቦምብ ወገቡን ተመቶ በሁለት ዱላ በመከራ የሚራመድና ከወገቡ በታች ሰውነቱ የማይሠራ /Paralysed የሆነ/ የአካል ጉዳተኛ ነው። እንደነገረኝ፣ የሚኖረው በእናቱ ቤት ከእህቱ ጋር ሲሆን እህቱ ባል ስታገባ "ቤቱን ልቀቅልኝ" ትለዋለች። ተሰማም እንዴት አድርጌ ከኔ ይልቅ አንቺ ትሻያለሽ፤ እኔ ወዴት እሄዳለሁ ብሎ አይሆንም ይላል። "በዚህ ጊዜ ቤቱን ማስለቀቂያ ዘዴ ተፈልጎ አስገድዶ መድፈር ክስ ተመሰረተብኝ፤ ያውም የእህቴን ልጅ፤ ለመሆኑ በምን አቅሜ?" ያለኝ ሌላው ነው።

እርግጥ አስገድደው የሚደፍሩ ሞልተዋል፤ ያውም በጣም በሚዘገንንና ከሰብአዊ ፍጡር አድራጎት ውጪ በሆነ መልኩ። እንደምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉትን እኔ በነበርኩበት ዞን ያለውን እንመልከት። በጣም



ከሚዘገንነውና የወንጀሉ ፈጻሚ የሆነው ዓለሙ የሚባለው አሁንም ሲወጣ ያንኑ ተመሳሳይ ድርጊት አይፈጽምም ብዬ የማልመሰክርለት ሰው ነው። አሁንም ስለወንጀሉ ሲያወራ አንዳችም ስህተት እንዳልፈጸመና የዳኝነት ስህተት ተፈጸመብኝ ብሎ የሚያምን ነው።

ዓለሙ በኦሮሚያ ክልል በአካባቢ ሚሊሺያነት ይሰራ የነበረ ሲሆን፣ አንድ ቀን አንዲት ሲመኛት የነበረችን ልጅ ከመጠጥ ቤት ሞቅ ብሎት ሲመለስ ከጓደኞቹ ጋር ይጠልፍና የሕዝብ ማመላለሻ የሆነውን ተሽከርካሪ በመሣርያ አስገድዶ ልጅቱን ወደ ቤት ይወስዳታል። ወዲያው ለጋዋ ልጅ እያለቀሰች ስትለማመጠውና ስትለምነው ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆን በመጠጥም በስሜት ተወጥሮ ይደፍራትና ቤቱን ቆልፎባት ወደ ዘመዶቹ ይሄዳል። በበነጋው ተመልሶ ደም እየፈሰሳት እንደገና ይገናኛትና አሁንም በሩን ቆልፎባት ይሄዳል። ከሶስት ቀናት በኋላ ሲመለስ ደክማ ሲያገኛት ቤተሰቡን ይጠራል ሲያይዋት ደም በብዛት ፈሷት ሞታ ትገኛለች።

ዓለሙ ይህን ሲያወራልኝ እየዘገነነኝ ሰማሁት። ለምን አደረግህ ስለው እንዴ ምን ነውር አለበት አገባኋት እንጂ ምን አደረግሁ መሞቷ በኔ ጥፋት አይደለም ሲለኝ በጣም ጠላሁት።ዓለሙ አሁንም ሲወጣ ያንኑ ተግባር የሚፈጽም መሆኑንና ምንም ጉዳት እንደሌለው ምንም ወንጀል እንዳልፈጸመ ነው የሚሰማው።

ሌላው ደግሞ፣ የኤይድስ ታማሚ መሆኑን ቀድሞ ይፋ በማውጣቱ ተከራርቶ የሚናገር ነው። የኢህአዴግ አባልም ነው። እሱም ቢሆን ስለፈጸመው ድርጊት አያምንም፣ እንዲያውም በሚሊኒዬሙ ምህረት ይደረግልኛል ብሎ የምህረት ቅጽ መሙላቱን አይቻለሁ። እሱ የተያዘው የኤች. አይ. ቪ በሽተኛ መሆኑን እያወቀ፣ በቤቱ ውስጥ በሰራተኛነት ይሁን በዝምድና አብራቸው የምትኖረውን አስገድዶ ደፍሮ ነው። የሱ አስገድዶ መድፈር ለሞት መዳረግንም የሚጨምር ነው። እያወቀ፣ አስተምራለሁ እያለ

ጭርሱን ወደአስገድዶ መድፈር ከተረማመደ ምኑን አስተማረ?

ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ችግር በሕንድ ተከስቶ የሕንድ የፍትህ አካላት ችግሩን ከተመለከቱ በኋላ አንድ ውሳኔ አሳልፈው ችግሩን አቁመውታል። በሕንድ አንድ ሰው ሚስት አጭቶ ሲያገባ ከሚስት ቤተሰብ ጠቀም ያለ ጥሎሽ ይከፈላል። ይህ እውነት የሆነ ጉዳይ ነው። ታዲያ የሕንድ ጎረምሳ ሁሉ ያገባና ሚስቱ የምታስገኝለትን ዳዋሪ በርከት አድርጎ ከበላ በኋላ ወዲያው ሚስቱ ትሞታለች። ባል ገንዘቡን ተቀብሏል ሚስት ሞታለች። ስለዚህ አንድ ስድስት ወራት ይቆይና ደሞ ከሌላ መንደር ሌላ ያገባል እንደገና ጠቀም ያለ ጥሎሽ ይበላል። በዚህ አይነት እስከ አራት አምስት ሚስት የሚያገቡና ከበርቴ የሚሆኑ ስለበዙ ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ይሄድና ሲጣራ ሚስጥሩ  ይወጣና ባል ገዳይ መሆኑ ይታወቃል። ስለዚህም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማስታገስና መልክ ለማስያዝ አንድ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አምስት አመት ሳይሞላ፣ ሚስት ከበሽታ ውጪ ሞታ ብትገኝ ባል ተጠያቂ እንዲሆንና የወሰደውን ጥሎሽ እንዲከፍል ህግ በመውጣቱ ጉዳዩ እልባት አገኘ። የኛም አስገድዶ መድፈር ማጣራትን የሚጠይቅ ሊሆን ይገባል፣ አለበለዚያ የቂም በቀል መወጫ፤ የልዩ ፍላጎት ማሟያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። እያንዳንዱ ታሳሪ የገባበት ቀን እንደመለያየቱ ወንጀሉም እንዲሁ ይለያያል፣ የየታሳሪውም ጠባይ እንዲሁ ነው።

አንዳንዱ እስረኛ በዞን ሃላፊዎች የሚወደድ፤ የእስራት ዘመኑ የሚቀነስለት ይመስለውና የሆነ ያልሆነውን ፈጥሮ በሬ ወለደ አይነት ወሬ ያቀርባል።

በኛ ዞን በሚስታቸው ጡት ላይ አራት ጥይት ተኩሰው በመግደል ሙከራ የታሰሩ ተ/ሃይማኖት ሐጐስ የሚባሉ የቀድሞው ጦር አባል የነበሩ ታሳሪ የሚያደርጉት የጠፋቸው አይነት ናቸው። አሁንም እዚያው ናቸው። ተፈርዶባቸው ይግባኝ ብለው ሲቀርቡ አለመጸጸታቸውን ፍርድ ቤቱ ተገንዝቦ አጸንቶባቸው



ተመልሰዋል። ታዲያ ጋሽ መስፍን በሚስታቸው ላይ ያደረጉት ትክክል እንዳልነበረና ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባቸው እንዲሁም ከፈቃዷ ውጪ አግብታ ጠላኋት ስለሚሏት ልጃቸውም ምርጫዋን ማክበር እንዳለባቸው ሲነግራቸው ቀስ እያሉ እየተቀየሙ በመጨረሻው አኮረፉት። ለጥቀው እኔን ከሰሱኝና ወዳጅነታችን ቀረ። ከዚያ ከኛ ጋር ያላቸው ግንኙነት ጨርሶ ከተቋረጠና እኛም እሳቸው እደረሱበት መድረስን ስንተው ከረምቦላ የሚያከራየው ገቢዬ ቀነሰ በማለት ክበብ የሚሰራውም እንዲሁ እያሏቸው ብቻቸውን ስለቀሩ በመጨረሻው «ሌባ ሳመሉ ዳቦ ይልሳል» እንዲሉ የሰብቅ ሱስ አድሮባቸው የእስረኛ አስተዳዳሪውን ታሳሪ ከሰሱት፣ አሳበቁበት። በዚህም ለየላቸውና የፈሳች ዝንጀሮ ሆነው ወድቀው ተነሱ የሚላቸው በማጣታቸው አማላጅ ልከው ነበር እልባት ሳይገኝ የተለያየን።

ሰውየው ቀድሞ ከነበሩበትም ዞን ተዛውረው ወደኛ ዞን የመጡት ወሬ ወዲያ ወዲህ እያሉ በማስቸገራቸውና እንደ ሰላይነትም ስለሚሰሩ በክልሉ ያሉ ጎረምሶች እንገላቸዋለን" ስላሉ ነው። አሁን እንዴት ሆነው እንደሆን ስጠይቅ ከዚያ ዞን ወጥተው መጥፎ ወደተባለው ዞን ሄደዋል ብለውኛል። አንዳንድ ታሳሪዎች ደግሞ፣ ከአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ወደ ዝዋይ ወይም ሸዋ ሮቢት፣ አለያም ወደ ሌላ ቦታ ላለመዛወር በማለት ታሳሪውን ሁሉ የተለያየ ተግባር ፈጽሟል በማለት ጠዋት ጠዋት በድብቅ  ሪፖርት በማቅረብ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚጥሩ አሉ። ሌላው ታሳሪ እየደረሰባቸው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ቢያስታግሳቸውም፤ ጉዳቱ መድረሱ አይቀርም። አንዱ ሲታወቅበት ደሞ ሌላው ይተካል።

በጣም የሚገርሙኝ አቶ አድማሱ የተባሉ ታሳሪ ናቸው። አቶ አድማሱ እድሜያቸው ወደ 90 ይጠጋል። የተከሰሱበት ወንጀል አስገድዶ መድፈር ነው። አቶ አድማሱ ሲጠየቁ አላደረግሁም ወይም ፍርድ ተዛብብኝ አይሉም። ማድረጋቸውን ያምናሉ። ምነው ስላቸው «እኔ» በሕይወቴ የምወደውና ቢለየኝ የማልፈልገው

ጥሩ ጠጅና ሴት ነው አሉኝ። እንግዲያ አድርገውታላ ስላቸው «ምን ጥርጥር አለው» ነው መልሳቸው። የእስር ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲፈቱ « አቶ አድማሱ በሉ ተመልሰው እንዳይመጡ ያቺን ነገር ሁለተኛ እንዳይደግሙ ብላቸው «አይ አሁን ወደ ቤትህ ሂድ ከሚሉኝ እዚሁ ሴቶቹ ዞን ወስደው ቢያስሩኝ ደስታዬ ነበር» ነው ያሉኝ፣ እየቀለዱ። አቶ አድማሱ ተፈተው ወጥተው አሁን ድረስ በሰላም ከምኑም ከምኑም ተጠብቀው በቤታቸው አሉ። ይህን ይህን ስንጠይቅ ስንሰማ ምንም ያህል የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቢረዝምም ቀኑ ቶሎ ይደርሳል።

ብዙዎቻችን ወህኒ ቤትን የምናውቀው ከውጭ በወሬ ወይም በአካባቢው ስናልፍ፣ አለያም በአጋጣሚ ሰው ታስሮብን ለመጠየቅ ስንሄድ ነው። የወህኒ ቤትን ምንነት በሚገባ ለማወቅ ግን መታሰርን ይጠይቃል። እኔ ደሞ ባይታወቅ እድሜ ልክ ይቅር እንጂ የማንንም መታሠር አልመርጥም። ይልቅስ ሁሉም ገብቶ የወጣ የወህኒ ቤት ልምዱን ቢችል በመጽሐፍ መልክ ካልሆነም በሌላ ለሕዝብ በሚደርስ ቢየስተላልፍ አማራጭነት አለው።

ወህኒ ቤት መማሪያ፣ ካለፈ ስህተት መታረሚያ ሊሆን ሲገባው በሃገራችን ያለው ሁኔታ ግን ለበለጠ ወንጀል መዘጋጃ፤ ለከፋ ተንኮል ማሠልጠኛ፤ አዳዲስ ወንጀሎችና የወንጀል ጥበቦችን መቅሰሚያ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ከነዚህ አዳዲስ በሽታዎች ለመራቅ ወይም የትምህርት ተሳታፊ ላለመሆን የግል ጥንካሬን ይጠይቃል። ያን ደግሞ ለማግኘትና ጠንክሮ ለመውጣት አካባቢውና በወህኒ ቤት ያለው ሁኔታ ብዙ ጊዜ አይፈቅድም። በወህኒ ቤት በፖለቲካ ስም ከመታሰር ይልቅ በነፍስ ግድያ፤ በአስገድዶ መድፈር፤ በዘረፋ፤ ብቻ ከፖለቲካ ውጭ በሆነ ማንኛውም አሰቃቂ ወንጀል መታሠር የበለጠ ተቀባይነት፤ የተሻለ አያያዝና ክብር ያስጣል። በፖለቲካ መታሰር ማለት ጠላት ሆኖ መታየትና ከማንኛውም የወህኒ ቤት «መብት» መታገድ ማለት ነው።



አንድ በነፍስ ግድያ ወይም በዝርፊያ ተወንጅሎ የታሰረ ሰው፤ ትምህርት ለመማር፤ ወይም በወህኒ ቤት ባለው የሕንፃ የሽመና፤ የልብስ ስፌትና ሌላም ሥራ ላይ፣ አነስተኛም ቢሆን እየተከፈለው እንዲሠራ፤ ትምህርቱንም በተልእኮም ሆነ በግቢው ባለው ትምህርት ቤት የመማር እድል ይሰጠዋል። በፖለቲካ የታሰረ ከሆነ፣ ግን በተለይም ከቅንጅት ወይም ከኦሮሞ ነጻ አውጪ ጋር ግንኙነት ያለው ከሆነ፣ ንክኪ አለው ከተባለ የዚህ ሁሉ መብቱ ይገፈፋል። የወህኒ ቤት ደንብ በሚባለው ግን ወህኒ ቤቱ ሁሉንም ታሳሪዎች በእኩል አይን የሚያይ፤ ለሁሉም ታሳሪዎች እኩል አገልግሎት የሚሰጥ ነው ይባላል። ሌላው ይቅርና በቤተሰብ ጥየቃ እንኳን ማለት በአወደ በአልና ቅዳሜና እሁድ በሚካሄደው የቤተሰብ ግንኙነት፣ ለቅንጅት አባላት የሚፈቀደው ሰአትና ለሌሎች ታሳሪዎች የሚፈቀደው በጣሙን ይለያያል።

ለሌሎች ታሳሪዎች

ጠዋት ከ3 ሰአት እስከ 6 ሰአት፣ ከቀትር በኋላ ከ7 ሰአት አስከ 9 የቤተሰብ ግንኙነት ሲፈቀድ፣ አንድ ጠያቂ ለጥየቃ እስከገባ ድረስ በየዞኑ እንደፈቀደው እየተዘዋወረ የተለያዩ ታሳሪዎችን ይጠይቃል፣ ገደብ የለበትም።

ለቅንጅት አባላት ደግሞ

ከቀትር በኋላ ከዘጠኝ እስከ አስር ነው። ለዚያውም አንድ ዞን ከጠየቀ ወደ ሌላ ዞን መሄድ አይፈቀድለትም።ይሄ ብቻ አይደለም፣ አንድ የቅንጅት አባል ከተፈታም በኋላ የቀሩ አባሪዎቹንም ሆነ ሌሎች አብረውት ታስረው የነበሩ የዞኑን ታሳሪዎች እንዲጠይቅ ጨርሶ አይፈቀድለትም።

የቅንጅት ሰዎችን ሲጠይቅ የነበረ ሰውም ሲጠይቃቸው የነበሩ ከተፈቱ በኋላ ሌሎችን መጠየቅ አይችልም። ለነገሩ የወህኒ ቤት የቤተሰብ ጥየቃ የሚመራው በዚያው አካባቢ በጥበቃ ላይ ባሉ የጥበቃ

አባላት ችሮታ የሚወሰን ስለሆነ ማን ምን እንደሚወስን የሚታወቅ ጉዳይ አይደለም። ሁሉም አዛዥ ነው። ሁሉም ከልካይና ፈቃጅ ነው። አንዱ የፈቀደውን ሌላው ይከለክላል። በበሩ ላይ ያሉት ደግሞ በተለይ በቤተሰብ ግንኙነት ወቅት፣ የቅንጅትን ቤተሰቦች በማንገላታት ለአለቆቻቸው ታማኝነታቸውን የሚያረጋግጡበት መንገድ እየሆነ ነበር የሚሰማቸው።ይህም አንድ ወጥ የሆነ አመራር የሚያስፈልገው ነው።

በግንኙነት ሰአትም ቢሆን ጠያቂና እኛ ስንነጋገር ለያንዳንዳችን ሁለት ሁለት የፖሊስ አባላት ተመድበው የምንናገረውን በማዳመጥ ሪፖርት እየተደረገ በሚቀጥለው ሳምንት አንዳንድ ጠያቂዎች እንዳይገቡ ይከለከላሉ። ጠያቂዎቻችን የውጪ ተወላጆችም ሆኑ የሀገር ውስጥ ከአማርኛ ሌላ መነጋገር ይከለከላል። ያ ጠያቂ ከሚናገረው ቋንቋ ሌላ አማርኛ ባያውቅስ። አዎን፣ አትናገር ተብለው ቢከለከሉም እኛም አሻፈረን በማለታችን የመጡትን ጠያቂዎች በሚችሉት ቋንቋ እያነጋገርን ሸኝተናቸዋል።

የወህኒ ቤት ፖሊሶች እንደ ማንኛውም ሰው፤ እንደማንኛውም ፍጡር ስሜት አላቸው። በዚህ ስሜታቸው በመመራትም አንዳንድ ጊዜ ወደ ዞኖች ሲገቡ ሰላምታ ይሰጣሉ ጥያቄ ይመልሳሉ፣ ቆም ብለው ቅሬታ ወይም ችግር ያዳምጣሉ። ለምሳሌ የዞኑ ሃላፊ ከአካባቢው ዘወር ብሎ እንደሆን አንድ ፖሊስ ወደ ዞኑ ለተለያየ ሥራ ከመጣ፣ እባክህ ጥራልኝ ወይም ለሌላ ሃላፊ ንገርልኝ ሊባል ይችላል። ፖሊሶች ለተለያየ ጉዳይ ወደዞኖች ይገባሉ። ልብሳቸውን ለማስተኮስ፤ ሲጃራ፤ ለስላሳ ለመግዛት፤ ቡና ለማዘዝ ይገባሉ። በዚህን ጊዜ ከእስረኞች ጋር ይገናኛሉ፣ ሰላምታ ይለዋወጣሉ። በዚህም ተወንጅለው ተገምግመው ከሥራ እስከመባረር የደረሱ አሉ። አበዛኛዎቹ እኔን ከቴሌቪዥን ውጪ ወይም የተሳካላቸው ከቴያትር መድረክ ውጪ አይተውኝ ስለማያውቁ እዚያ ሲያዩኝ ሰላም ይሉኛል ያ ግን በቅንጅትነቴ ሳይሆን በጥበብ ሞያዬ ነው። አንዳንዶቹ ቪዲዮህን አይተናል ይላሉ ጥቂቶች ደሞ የተለያየ ሥራ ስሰራ ያዩኝ ናቸው። ይህም እንደ



ወንጀል ተቆጥሮ ከሥራ ለመባረር ሰበብ ሆኗል። በስርቆት፣ በግድያ፣ በሌላ ሌላ ወንጀል ከታሰረ ጋር ግን ሰላምታ አይደለም ስለፈለገው ጉዳይ ሲያወራ ቢውል የሚጠይቀው የለም። ታዲያ ወህኒ ቤቱ ሁሉንም እኩል ነው የሚያየውና የሚያስተዳድረው የሚባለው እንዴት ነው?

ይህ የተለየ አመለካከት ይደርስብን የነበረው በወህኒ ቤቱ ብቻ ሳይሆን በፍርድ ቤትም ነው። ፍርድ ቤቱ የራሱ የሆነ የስነስርአት ተቆጣጣሪ ስለአለው እንደ ደንቡ የወህኒ ቤት ፖሊሶች ለፍርድ ቤት ፖሊሶች አስረክበው እንደገና ችሎቱ ሲያልቅ ነበር መረከብ ያለባቸው። በኛ ላይ ግን የፍርድ ቤት ፖሊሶች አንዳችም መብት የላቸውም ነበር። በዚያም ፈላጭ ቆራጮቹ እነዚያው የወህኒ ቤቶቹ ነበሩ።

ፍርድ ቤት እንደሚለው፣ ታሳሪዎችን ለወህኒ ቤት በአደራ መልክ ነው ያስረከበው በተለይም እስኪፈረድባቸው ድረስ። ከተፈረደባቸው በኋላ ሙሉ በሙሉ ይረከባል። ታዲያ ያልተፈረደብንን ሰዎች ያውም በአደራ የተቀበለንን፣ በልዩ ልዩ ዘዴ ማሰቃየትን ምን አመጣው? ፍርድ ቤቱስ በዚህ አያያዝ በኩል የሚቀርብለትን አቤቱታ አዳምጦ ለምን? ብሎ የማይጠይቀው ምናልባት የውስጥ ስምምነት ኖሯቸው ይሆን?

የጋሼ መስፍን ቅሬታ በትንሳኤ ሬዲዮ እስኪደመጥ ድረስ በፍርድ ቤት ውስጥ ጠመንጃ የያዙ ፖሊሶች ነበሩ፣ ከበው የሚያንቀጠቅጡን። አቤቱታው በተሰማ ማግሥት ጠመንጃ መያዝ ቀረና ባዶ እጃቸውን ይቀመጡ ጀመር።

የፖሊስ አባላቱ፣ በተለይ ፍርድ ቤት የቪዲዮ ማስረጃ በሚታይበት ጊዜ ሲመደቡ ደስ ይላቸው ነበር። ቅንጅት በየወረዳውና በየቀበሌው ሕዝባዊ ስብሰባ ሲያካሂድ፣ የፖሊስ አባላት መገኘት ክልክል ስለነበር፣ ያመለጣቸውን የቅንጅት ንግግር፤ መርህ፤ በተለያዩ ርእሶች ላይ ያቀረቡትን የመከራከሪያ ነጥብ ለማድመጥ

በመፈለግ ተለወጡ ሲባሉ ከፍተኛ ቅሬታ ነበር የሚሰማቸው::

አንዳንዶቹ ከፍርድ ቤት ስንወጣ ምን ያህል እንደተደሰቱ፣ ለሚቀጥለውም ቀጠሮ እድል ቢያገኙና ጥበቃ ላይ ቢመደቡ እንደሚደሰቱ ይነግሩን ነበር::አንዳንዶቹ የቪዲዮው ኮፒ በኛችን እንዳለም በመጠየቅ ለመዋስ ይጠየቁን ነበር:: ይህ ደግሞ በተራዎቹ ፖሊሶች በድብቅ ይጠየቅ እንጂ፣ ሃላፊዎቹም አንዳንዱን ትምህርታዊ ነው በማለትና ውጪ ለሚኖር ቤተሰብ ለመላክ በማለት የጠየቁን ነበሩ::

ፖሊስ ማስረጃ ብሎ በራሱ ፊልም አንሺ አስነስቶ ያቀረበው እንኳን፣ እኛን ሊያስወነጅል የሚበቃ ምስል አልነበረውም:: ተመቱ የተባሉት የፖሊስ አባላት አንድም ቦታ ላይ ሲደበደቡ ወይም ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ወደ ፖሊስ ሲጠጉ የሚያሳይ ሁኔታ አልነበረውም:: እንዲያውም በአብዛኛው ማለት ይቻላል፣ የታየው ሰልፈኞቹ ሲሸሹ ነበርና እንዴት እየሸሹ ሊማቱ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ከታዛቢ ተመልካቾች አስነስቷል::

ዳኞቹ አንድም ቦታ ላይ ይህ ምን ለማለት ነው? ካስመዘገባችሁት ሃሳብ ጋር ጨርሶ አይሄድም ወይንም አይገናኝም ብለው የጠየቁበት ጊዜ አልነበረም:: በአቃብያኑ የቀረበውን ሁሉ አሜን ብለው፣ እንዲያውም በሚሰጡት ውሳኔ ላይ በአቃቤ ሕግ ያልተነሱ ነጥቦችን እያካተቱና ለነሱ እየወገኑ ነበር ሲወስኑ የነበረው:: ፍርድ ቤቱ አንድም ቀን በአንድም ጭብጥ ላይ ለተከሳሾች የሚሆን ዳኝነት አላሳየም:: ዳኞችና አቃብያኑ እጅና አንድ ጓንት ሆነው ነበር ችሎቱን የሚያካሂዱት::

## ፍትሕ ገደል የገባበት ዕለት

ከመጋቢት 27/99 እስከ ሚያዝያ 1/99 ድረስ ከተካሄደው ብይንና 26 ሰዎች ነፃ ተብለው ሌሎቻችን ተከላከሉ ከተባልንበት ጊዜ ጀምሮ ለመከላከያ ይሆነን



ዘንድ ቪዲዮዎችን በጋራ ወህኒ ቤቱ ውስጥ እያየን ነበር:: ሀሳቡ ከዚያ በኋላ በተናጠልም ሆነ በቡድን መከላከያ ለማቅረብ እንዲያስችለን ተነጋግረን ያደረግነው ነው::

ግንቦት 24/99 ጠዋት ቀደም ብለን ነበር ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ የተዘጋጀነው:: ቁርስ እየበላን ያላየነው ቪድዮ መኖሩንና ፍርድ ቤቱ እንድናይ ቢያዝልንም፣ ከሬጂስትራር ተሟልቶ አልመጣልንም በማለት ወህኒ ቤቱ ያለውን ብቻ አሳይቶ አቆመ:: ለጎደለው ቪዲዮ አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ጽፈን ለወህኒ ቤቱ ብንሰጠው በማድረስ ፈንታ እራሱ ወሳኝ በመሆን፣ በቡድን ሆናችሁ አቤቱታ አትጽፉም በማለት ከለከለን:: የተከሰስነው በአንድ የክስ መዝገብ ሆኖ ሳለ ለምን በአቤቱታ አቀራረብ ላይ አይቻልም እንደምንባል ግልጽ አልነበረም:: ሬጂስትራር ወይም ችሎቱ ኢይሆንም ማለት ሲገባው በጉልበት ወህኒ ቤቱ ውሳኔ መስጠቱ አግባብ አልነበረም::

ለወህኒ ቤቱ አቤቱታችንን የሰጠነው በሳምንቱ ሁለተኛ ቀን ማክሰኞ ሲሆን፣ ለፍርድ ቤት ሳይላክልን በወህኒ ቤቱ እንደማይቻል የተነገረን አርብ ወደ 10 ሰአት ተኩል ነበር:: እኛ ሰኞ ፍርድ ቤት ልንቀርብ አርብ አቤቱታው አይቻልም ሲባል ትእዛዙን ተቀብለን ወህኒ ቤቱ እንደፈለገው በተናጠል እንጻፍ ብንልስ ምን ጊዜ ሊደርስ ነው? አካሄዱ የተንኮል እንደሆነ ስለገባን ግድ የለም ለፍርድ ቤቱ አቤት እንላለን በሚል የፍርድ ቤት መሄጃውን ስንጠብቅ ሰዓቱ ደረሰና እንሂድ ተባለ:: አሁንም፤ የደረሰው የኛ ወደ ፍርድ ቤት መሄጃ ሰአት ነው እንጂ ዳኞች የሚሰየሙት በጣም አርፍደው ነው::

ልክ 2 ሰአት ከሩብ ሲሆን ከቃሊቲ ወህኒ ቤት ወጣን:: ዛሬ ጥበቃው ሌላ ነው፣ በየመኪናው ውስጥ ያለው አጃቢ ቁጥሩ ናር ያለ ነው፤ በየመኪናው ውስጥ የእጅ ማሰሪያ ካቴና አለ፤ የአጃቢ መኪናዎችም ቁጥር በጣም በርክቷል:: የወህኒ ቤት ባለሥልጣኖች አንዱም በግቢ የቀሩ አይመስልም:: እነሱ ይወሰናል ብለው ሲያስቡ እኛ ደሞ ያላየነውን ቪድዮ ለማየት ፈቃድ

እንጠይቃለን፣ ያንን ዕድል ስለማይከለክሉንና ሕጉም ስለማይፈቅድላቸው ባይሆን ቀጣዩን ቀጠሮ ያረዝሙብናል እንጂ ወደ ውሳኔ አይሄዱም" በሚል ነው ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ የተዘጋጀነው:: እነሱ ከአደራ ጠባቂነት ወደ አስረኛ አስተዳዳሪነት ሊዘዋወሩ፣ እኛ ደሞ እስከሚቀጥለው ቀጠሮ ድረስ በአደራ ለመቆየት::

ከቃሊቲ ወህኒ ቤት ግቢ የመውጫው ሰአት ደረሰ በመውጫው ላይ ያለው መንገድ ተዘጋ:: ሞተረኛው ቀድሞ በምንሄድበት ጎዳና ላይ ትራፊኩን እያስቆመና ጥግ እያስያዘ፣ ፍርድ ቤት ደረስን:: ከሰሞኑ የተለየ ጉዳይ ቢኖር ቤተሰብ በሙሉ ገብቶ በአዳራሽ ቦታውን ይዟል:: ታዛቢዎችም ገብተዋል:: አካባቢው በፖሊስ ታጥሯል:: በየማቋረጫው ላይ ያየነው የጥበቃ ሃይል ከሌላው ቀን በተለየ መጠናከሩን ያሳያል:: ግቢው እንደደረስን እንደተለመደው መኪና ውስጥ ሆነን የዳኞቹን የአቃብያኑን መምጣት እንጠብቃለን ወዲያውም የዛሬው የፍርድ ሂደት ምን ሊሆን እንደሚችል ሁላችንም የየራሳችንን ግምት እየተናገርን ነው:: አብዛኞቻችን ያላየነውን ቪድዮ ለማየት ስንጠይቅ ያንን ሰበብ አድርጎ ለመስከረም 2000 ይቀጥረናል ስንል ጥቂቶቻችን ደሞ የለም ዛሬ አያችሁም አላያችሁም ተከራከሩ ይለናል:: ከኛ ምንም ሲያጣ አጭር ቀጠሮ ይሰጥና በሚቀጥለው ሳምንት ይፈርዳል እንላለን:: ሁሉም የግምቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሰበቡን ያቀርባል:: ይህን እያልን የዛሬው ከሌላው ቀን በተለየ በጣም በመርፈዱ ለሽንት የሚሄደው እግሩንም የሚያፍታታው አብሮ እያስፈቀደና እየታጀበ እየሄደ ይመለሳል:: የዳኞቹና የአቃብያኑ ማርፈድ የሁሉንም ግምት ወደ አንድ ወገን አሰባሰበው:: ዳኞች ስላልተሟሉ ሌላ ቀጠሮ ይሰጡናል ተባለ:: እስካሁን በግቢው ሲደርስ የታየው ዳኛ አዲል ብቻ በመሆኑና ዳኛ መሃመድ አሚን ከአዲል ጋር ስለሚመጣ ሳናየው ገብቶ ይሆናል ብንልም፣ ልኡል ግን ስላልታየ ቀጠሮው አይቀሬ ነው ተባለ:: አቃብያኑም አልታዩም::

ልክ አራት ሰአት ከሩብ ገደማ ሲሆን ፖሊሶች ግቡ ትእዛዝ ሰጡና ሁላችንም እየወረድን ናፍቆታችንን



በመሳሳም ሰላምታ እየተወጣን ወደ ፍርድ ቤቱ አዳራሽ ገባን:: ቤተሰብም ተመልካቾችም ቆመው ጠበቁን:: በተለመደው ኢትዮጵያዊ አክብሮት የሰላምታ ሰጥተን ወደ የመቀመጫችን አመራን:: ሁሉም መቀመጫ ያዘ:: በምልክትና በአፍ እንቅስቃሴ ከቤተሰብ ጋር መነጋገር ሰላምታው ቀጠለ:: ትንሽ እንደቆየን አቃብያኑ በሰልፍ ሽመልስን አስቀድመው ከኋላ እየነዱት እየተጀነኑ ገቡ:: ሁሉም በትዝብትና በመገረም ይመለከታቸዋል:: አቃቤ አብርሃም ተጠምቀ ድሮ በጣም ዱሮ የአራዳ ልጆች ሲጀነኑ መነጽራቸውን በጥርሶቻቸው ነክሰው እንደሚይዙት ሁሉ ዛሬ ወደኋላ ቀርተው መነጽራቸውን ነክሰው ነው የገቡት:: ሁልጊዜም ያንን እያየን እንስቃለን::

በመጨረሻ ዳኞች አልተሟሉም ስንል ተሟልተው ገቡ:: ወዲያው እንደተለመደው የዳኞች ስም ተዘርዝሮ፤ አቃብያኑም ስማቸውን ተናገሩ፤ የዳንኤልና የነጻነት ጠበቃም አስመዘገቡ፤ ተከሳሾች ተሟልተው ቀርበዋል? አሉ ዳኛ አዲል፤ የወህኒ ቤቱ ተወካይ ተሟልተዋል አለ::

ዳኛ አዲል «ዛሬ ያደረው ጉዳይ» ሲሉ

ዶር ብርሃኑ ሁላችንንም ወክሎ «የተከበረው ፍርድ ቤት አቤቱታ አለን» ሲል

ዳኛ አዲል ድንገት ቱግ ብለው «አልተፈቀደልህም» አሉ::

ዶ/ር ብርሃኑም እንደዚያ ቱግ የሚያደርግ ምንም ሰበብ አልነበረምና በደንብ ያላዳመጡት መስሎት «የተከበረው ፍርድ ቤት አንድ አቤቱታ ስላለን.. .. ..» ሲል

«አልተፈቀደም አልኩ እኮ» አሉ::

«ክቡር ፍርድ ቤት ከጉዳያችን ጋር የተያያዘ አቤቱታ አለን የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ስላልተከበረ.. .. » እንዳለ

ዳኛ አዲል ይብሱን ቱግ ብለው ጥርሳቸውን ነክሰው በእልህ እየተርገፈገፉ «ብርሃኑ» አሉ ቁጣቸው ዶ/ር የሚለውን ማንጠልጠያውን እያስጣላቸውና ማን ይፈራሃል አይነት ብስጭት እየታየባቸው:: «ብርሃኑ አንተ እንደፈለከው አይደለም አልተፈቀደም፣ አትናገርም፣ በቃ ይሄው ነው» ብለው ሊቀጥሉ ሲሉ

ሻለቃ ጌታቸው «የተከበረው ፍርድ ቤት! የመናገር መብት የለንም ማለት ነው?» ሲል

ዳኛ ልኡል ድንገት ትዝ ያላቸው ይመስል ወይም ለሰበብና ለምክንያት ያነሱት በሚመስል የቂም በቀል ስሜት «ምነው እስከዛሬም ፍርድ ቤቱን እንደናቃችሁት ነው ስናይ የነበረው ዛሬም ያው ነው ለምን በስነስርአት አይሆንም?» አሉ::

ለመሆኑ ስነስርአት የጠፋው በየት በኩል ነው? ተከሳሽ ለሞት የሚያበቃ ክስ ተመስርቶበት፣ የተመከሩ ምስክሮች፣ በማስፈራራት «ምስክርነት፣ የሰጡበት «ጠ/ሚኒስትሩ ገና ጉዳዩ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ እስከሞት የሚደርስ ፍርድ የሚያስፈርድ ወንጀል ፈጽመዋል ብለው ሳይጀመር የጨረሱት ክስ የተመሰረተባቸው ተከሳሾች ለመናገር ፈቃድ ሲጠይቁ መከልከላቸው ነው ስርአት ያጣው ወይስ መጠየቁ? አሁንም ከየአቅጣጫው ተከሳሾች አካሄዱ ግራ ስለሆነባቸው የ«እንደመጥ» ጥያቄ አነሱ፤ በዚህ ጊዜ ዳኛ ልኡል የማዳመጥ ፍቃደኛነት ሲያሳዩ ዳኛ አዲል ግን ከዚያው ከሚፍለቀለቅ ንዴታቸው ሳይወጡ በቃ«ከአስር ደቂቃ በኋላ እንመለሳለን » ብለው ተሽቀዳድመው አንዱ በሌላው ላይ ተደራርበው ወጡ::አወጣጣቸው የፍርድ ቤቱን ስነስርአት የተከተለ ሳይሆን በእኔ እይታ የአጭር ሩጫ እሽቅድድም ነበር የሚመስለው::

ተከሳሾችም፣ ቤተሰብም፣ ተመልካቾችም ጠባቂ ፖሊሶችም የደህንነት ሠራተኞችም ሁሉም ትእዛዙን ተቀብሎ ይጠብቅ ጀመር:: ተከሳሾች የጠየቁት ቪዲዮውን የማየት ውሳኔ ይሰጠናል የሚል ተስፋ አደረብን:: አሁንም ግን የዳኞቹ ውሳኔ የተለየ ሊሆን



እንደሚችል የጠረጠሩ አልጠፉም:: ሰአቱ አለፈ፣ 10 ደቂቃ የተባለው ወደ 30 ደቂቃ ሄደ፣ አልመጡም:: 45 ደቂቃ፣ አንድ ሰአት፣ ምንም የለም:: ሁለት ሰአት ሲሆንም ዳኞቹ ብቅ አላሉም ድንገት ግርግር ተፈጠረ:: አንድ የወህኒ ቤቱ መለስተኛ ሃላፊ በተለይ የቅንጅትን ታሳሪዎች ለህክምናና ለአንዳንድ ጉዳይ ፈጻሚነት የተመደበውና በእለቱ የወህኒ ቤት ተወካይ ሆኖ ፍርድ ቤት የቀረበው ፖሊስ ተጠርቶ ወደ ዳኞች ክፍል ገባ:: ጥቂት ቆይቶ በገባበት ሳይሆን በጀርባ ወጥቶ ተጨማሪ ፖሊሶች ያስማራ ጀመር:: በተለይ ወደመጸዳጃ ቤት ሄደው የተመለሱ አባሎቻችን እንዳዩት ፖሊሶቹን በከፍተኛ ተጠንቀቅ ማሰማራቱን አይተዋል:: ምን እንደመጣ ምን እንደተፈጠረ ማንም ያወቀ የለም:: ዳኞቹ ከ10 ደቂቃ በኋላ እንመለሳለን ብለው ችሎቱን ጥለው ከወጡ ከሁለት ሰአታት በኋላ ተመልሰው በቅድም ተከተል ገቡ:: ቤተሰቦች፣ ተመልካቾች፣ እኛም እንደተለመደው በፍርድ ቤቱ ሥነስርአት አስከባሪ ፖሊስ ትዕዛዝ ተነስተን ተቀበልናቸው:: ዳኛ አዲል አሁን ንዴት ሳይሆን ድንጋጤና አለመረጋጋት ነበር የሚታይበት:: ከእንግዲህ አንቱታዬን ጥየ አንተ ልለው መርጫለሁ:: 1ኛ በዕድሜ እበልጠዋለሁ፣ 2ኛ በዕውቀት እበልጠዋለሁ፣ 3ኛ በልምድ እበልጠዋለሁ፣ 4ኛ በሙያ ስነምግባር አክብሮት እበልጠዋለሁ፣ 5ኛ ቃል በመጠበቅ እበልጠዋለሁ፣ 6ኛ ሰአት በማክበር እበልጠዋለሁ፣ 7ኛ ፈጣሪን በመፍራትና ትእዛዙን በማክበር እበልጠዋለሁ፣ 8ኛ ለሰብአዊ መብት በመቆም እበልጠዋለሁ፣ 9ኛ ለዴሞክራሲ ማበብ በመታገል እበልጠዋለሁ፣ 10ኛ ለሕዝብ በመገዛትና ሕዝብን በማክበር እበልጠዋለሁ:: ስለዚህም እሱንና እሱ የሚመራቸውን ዳኞች ጨምሮ አንተ ማለትን መርጫለሁ::

መሐመድ ሳኒም ያው ነው:: ከዘወትር ሁኔታው የተለወጠ ነገር ቢኖር ድንጋጤ በገጹ ላይ ይታያል:: ዳኛ ልኡልም ቢሆን የቁጭትና የቂም በቀል ስሜት ቢታይበትም «ሊሠራላችሁ ነው» በሚል ስሜት ነበር የሚመለከተን:: ዳኛ አዲል ተቀመጡ አለንና ተቀመጥን:: ወዲያው የመከላከል መብታችንን ሙልጭ አድርጎ በመሻር፣ በኢትዮጵያ ታሪክ በየትኛውም

የሃገሪቱ የፍትሕ ስርአት ላይ ታይቶ የማይታወቅ ውሳኔ አሳለፈ:: በፍትሕ ስርአት መሰረት አንድ ተከሳሽ እከላከላለሁ ወይም አልከላከልም የሚለው ካለ ያንን በጽሁፍ አድርጎ ያስገባል እንጂ በዘፈቀደ መከላከልን ዳኛ ው የሚሰጠው ወይም የሚከለክለው ጉዳይ አይደለም::

ተከሳሾች አቤቱታ አለን የመደመጥ እድል ይሰጠን በማለታቸው ዳኞች ተናደው ችሎቱን ትተው ወደቢሮ ሄደው ስልክ ደውለው ምን እንደሚያደርጉ ፈቃድ የሚጠይቁበት ሳይሆን አቤቱታቸውን ሰምተው ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ሙያዊ ግዴታ አለባቸው:: የዛሬው የፍትሕ ስርአት በየትም ያልተከናወነ በተለይ ለኛ ለቅንጅቶች እንዲሆን ዳኛ አዲልና ግብረ አበሮቹ ቀርጸው ያመጡት ነው:: ለመሆኑ አንከራክርም ያልንበትን ማስረጃ ችሎቱ ሊያቀርብ ይችል ይሆን? አላወቁት እንደሆን እንጂ ይህን የመሰለው ማስረጃ በሃሰት ምስክሮች የሚረጋገጥ ሊሆን አይችልም::

እነ ዳኛ አዲል እንደተመለሱ የሰጡት ውሳኔ "ጥፋተኞች ናችሁ:: የዚህን ዝርዝር ፍርድ ለማሰማት **ለሐምሌ 1/99 ጠዋት ተቀጥሯል፣** ጨርሰናል::" ብለው እንደአገባባቸው ተግተልትለው ወጡ::

**ሐምሌ 1/99 ደሞ ዕሁድ ነው!!** ይህ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲነገር ሁላችንም እፎይ ነው ያልነው:: የውሳኔው በዚህ መልክ መወሰን ወይም መዘግየት በፍርዱ አፈጻጸም ላይ አንዳችም ለውጥ እንደማያመጣ ብንገነዘብም ለሥርአቱ ያህል የመከላከል መብታችን ሊከበርና ሊጠበቅ ይገባ ነበር:: ይህ ብቻም አይደለም፣ ከነጻው ፕሬስ አባላትና ካልተለቀቁት የቅንጅት ተከሳሾችና የሲቪክ ማህበር መሪዎች መሃል በጠበቃቸው አማካይነት ለመከላከል ማመልከቻ አስገብተው የሚጠባበቁትም ጭምር ናቸው የመከላከል መብታቸውን የተነፈጉት:: ቀጠሮ የተሰጠበት ሐምሌ 1/99 የሚውለው ዕሁድ መሆኑን ስንገነዘብ ደግሞ፣ያ ፍርድ ቤት በሂደቱ ላይ ምንም ትኩረት እንዳልነበረውና ውሳኔውም ከፍርዱ መጀመር በፊት ያለቀለት ጉዳይ እንደሆነ ነው የተረዳነው:: ለነገሩማ ዳኛ አዲል



ቀጠሮውን ከመስጠቱ አስቀድሞ አጀንዳውን ባዶ የቀጠሮ ቀን ፍለጋ በሚመስል መልኩ ብዙ አገላብጧል:: ሌሎቹም ዳኞች የሚቀጥለውን የቀጠሮ ቀን ለመመዝገብ አጀንዳቸውን ከፍተዋል:: እንዴት አንዳቸው እንኳን ሳይገነዘቡት ቀሩ?ድምጽ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ:-

ይህን ውሳኔ በተመለከተ «አቃቤህግ» ሽመልስ ከጀርመን

<u>«.. .. .. እኛም በጣም ገርሞናል፣ አይከላከሉም ብለን አልገመትንም ውሳኔው አስገርሞናል.. .. .. »</u>

ነበር ያለው:: ወዲያው በስልክ ይሁን በገጽ ተጠርቶ «ምን ማለትህ ነው?» የሚል ግልምጫ ደረሰበት መሰል ያንን ለወጠ ፣ያኛውን ሊሰርዘው የሚችል የማረሚያ አስተያየት አልሆነም:: እንዲያውም ያን ያዳመጠ ሁሉ « አይይ ምነው ዝም ብሎ ቢተወው ኖር?» ነው ያለው:: ከአስተያየት ሰጪዎች እንደተነገረው «ዕውነተኛ ስሜቱን ከገለጸ በኋላ ለምን መዋሸት አስፈለገው?» ነው ያሉት:: ነገሩ ከስርአትና ከፍትሕ ዲሲፕሊን ውጪ የሆነ ሂደት ስለነበረ እርግጥ ያስገርማል ከዚያ ውጪ ሊባል የሚችል ጉዳይ የለውም:: ከውሳኔው በላይ የሚያስገርመው ግን የሽመልስ ለመጀመርያ ጊዜ በስህተት እውነት መናገር ነው::

ያን ጉዳይ ያዳመጠና በተከሳሾች ላይ የተፈጸመውን የፍርድ መዛባት የሰማ ሁሉ፣ ነገሩ አስቀድሞ የተወሰነ፤ ግን ለይስሙላና ዓለም አቀፉን ሕብረተሰብ ለማታለል የተዘጋጀ እንደሆነ ነው ያረጋገጠው::ገና ከጅምሩ ጠቅላይ ሚኒስትሩ «ወንጀለኞች ናቸው፣ እስከሞት የሚደርስ ቅጣት ያስፈርዳል፣ማንም በምንም መልኩ ሊያድናቸው አይችልም፣ .. .. .. .. » ብለው ነበርና ቀድሞውኑ የተሰጠ የፖለቲካ ውሳኔ ነበር:: አቃብያኑም በዚያው መስመር ፈሰሱ፣ ዳኞችም ቦዩን አስተካክለው የጠቅላይ ሚኒስትሩን ፍርድ አጸደቁ እንጂ፣ ፍትሕን አልተገበሩም::

*«ፍትሕ በኢትዮጵያ» የሚል ጥናታዊ ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ወቅት ትልቁ አሳፋሪና ኢፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ተብሎ የሚመዘገበውና ለታሪክና ለትውልድ የሚቀረው ይህ ሂደት ይሆናል የሚል እምነት አለን።*

ያም ሆነ ይህ የይስሙላ ውሳኔ ተሰጠ፣ የሚቀረው ቀኑን ማስተካከልና ሐምሌ 1 ዕሁድን ወደ ሐምሌ ሁለት ሰኞ ለውጦ ፍርዱን እያተቱ በቁጥር ማስቀመጥና ዕድሜ ልክና ሞት ብሎ መናገር ነው። ወደየዞናችን ስንመለስም ያንን ውሳኔ የጠበቀ ባለመኖሩ ስንነግራቸው ለማመን ተቸግረው ነበር። ቀልድ የመሰላቸውም ነበሩ። ገና ውሳኔ ባይሰጥ ነው እንጂ ያላየነው ቪዲዮ አለ እየተባለ ወደ ውሳኔ አይገባም ያሉንም አልጠፉም። ዕውነቱ ያ መሆኑን በቁርጥ ስናረጋግጥላቸው ግን በጣም ደንግጠው እንዴት? ከማለት ውጪ ቋንቋ አላገኙም። አንዳንዶቹ ሳትከላከሉ እንዴት ይሆናል? ቢሉም የመከላከል መብታችንን እንደተገፈፍን ስንነግራቸው «እንዴት! ተደርጎ የማይታወቀውን? ተሰምቶም አይታወቅ ለመሆኑ እንዲህ አይነት ሕግ አለ እንዴ? በማለት የመገረም ነበር ጥያቄያቸው። እኛም ስላልገባን የተባለውን ከመንገር ባሻገር፣ሕጉንም ጠንቅቀው ከአቃብያኑም ከዳኞችም በበለጠና በጣም በላቀ መልኩ የሚያውቁትም የቅንጅት ተዘሳሾችም ምን ማለት እንደሆነና በየትኛው አንቀጽ ላይ እንደተደነገገ ማወቅ አልቻሉም። ታዲያ ሕገ መንግሥቱን እንወክለዋለን በሚሉት በነሽመልስና በነአዲል ሕገመንግሥቱ አልተናደም የሚል ይኖራል? በዚህ ድርጊታቸው መቼም ይሁን መቼ ቀኑ ሲደርስ፣ወቅቱ ሲመጣ፣በሕገመንግሥት ማፍረስ፣ መናድ፣አለአግባብ መተርጎም፣የሌለ አካቶ በማሳሳት ፍርድ ፊት እንደሚቆሙ ጥርጥር የለኝም።

የሞት ወይም የዕድሜ ልክ አስራትና በተዋረድ እንደየፍላጎታቸው የሚወስኑብንን የእስራት ዘመን ለማዳመጥ የአንድ ወር ከአሥራ አምስት ቀን ገደማ ቀጠሮ ነበር የተሰጠን። መጠበቁን ለምደነዋል። ምንም ፍርድ ቢሰጥ ለመቀበል ዝግጁ ነን። ገሚሱን ዕድሜ ልክ ሌላውን 15 ዓመት ቀሪውን 10---5---3----እያሉና



በነጻ ወይም የታሰረው በቂ ሆኖ የሚለቀቅ እንደሚኖር ገምተን ነበር ቀኑን ስንጠብቅ የከረምነው።

በአንድ ወቅት ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ለመሄድ ከሌሎች ታካሚዎች ጋር ሆኜ ሰአቱን ስጠብቅ ወደ ሆስፒታል የሚወስደን በተለይ በኛ ላይ ያለው አመለካከት የጠላትነት የሚመስለው ከስሙ በስተቀር ማዕረጉን እስክንወጣ ድረስ ሳላውቀው የቀረሁት የማነ ነበር። የማነ ሁል ጊዜ ወደ ሆስፒታል ሲወስደን በጣም በመሰላቸትና በኛ ወደሆስፒታል በመወሰድ ቅሬታ የነበረው ሰው ነው። ዛሬም ልክ እንደለማኝ ወይም ሃኪም ቤት ሄደን እንደማናውቅና ከታሰርን በኋላ ሆስፒታል ያየን በሚመስል በዐይኑ ቁጥ እያየን መኪናው ላይ ጫነን። የማነ ሆስፒታል የመውሰድ ተረኛ ሲሆን እኔ ብቻ ሳልሆን አጃቢዎቹም፣ አሽከርካሪዎችም፣ የፖሊስ ሆስፒታል ሰራተኞችም ደስተኞች አይደሉም። ከዛሬ በፊት በተገናኘንበት ጊዜያት ሁሉ ያየሁትንና የታዘብኩትን ልጥቀስ።

ገና ፖሊስ ሆስፒታል ስንደርስና ከመኪናው ስንወርድ ለያንዳንዳችን የሚመደቡትን አጃቢዎች ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣እኛንም ታካሚዎቹን አቁሞ ወደየምንታከምበት ክፍል ከመሄዳችን በፊት በተለያየ ምክንያት ትንሽ ይገትረናል፣ በተለይ ፊዝዮቴራፒ የምንታከመውን ሰዎች እሱና ሌሎች አጃቢዎች ናቸው የሚወስዱን ስለዚህ ሌሎቹ ከተሰማሩ በኋላ ነው የምንሄደው።ልክ ስንደርስ ሃኪሞቹ ላይ ነርሶቹ ላይ ቁጣ ይጀምራል።ምንድን ነው ይሄ ሁሉ ሰው? ለምን አንድ ጊዜ ጨርሳችሁ አታክሟቸውም?የሽርሽር መዝናኛ ይመስላል። አሁንም በየቀኑ እየቀጠራችሁ ታመላልሱናላችሁ፣ አይበቃም? በማለት ግራ ያጋባቸውና እንዲያውም አንዳንዶቻችንን መርጦ እነዚህ ሌላ ቀጠሮ እንዳይሰጣቸው ብሎ ይወስናል። ሃኪሞቹም፣ ነርሶቹም፣ ድሬሰሮቹም ሁሉም እሱን ለመገላገል ሲሉ ያላቸውን ይፈጽማሉ። ለነገሩ እምቢ መታከም አለባቸው ቢሉም ከሱ ግልምጫና ቁጣ ባሻገር፣ ወህኒ ቤት ባለው ተስሚነት ህክምናውን

ያቋርጠዋል። ይህን ደሞ ደርሶብኝ አይቼዋለሁ። ይህ ባለፈው ያጋጠመኝ ነው፤ በተደጋጋሚ።

አሁን ደሞ የባሰ አጋጠመኝ። ሁላችንም ከተሳፈርን በኋላ ከወህኒ ቤቱ ግቢ ወጥተን በቀለበት መንገድ ወደ ሆስፒታል በመሄድ ላይ እያለን ከመገናኛ ማሰልጠኛ አጠገብ አንድ ፒክአፕ መኪና ለማለፍ ሲሞክር በቀኝ ያለውን መንገድ ይዘን በመሄድ ላይ ነበርን። በቀኝ ሊያልፍ ሲሞክር እኛ ያለንበት መኪና ሾፌር ከግራ ወደቀኝ ገባበት። ያኛው ሾፌር ክላስክ አሰማ እንዳይጋጩ ብሎ። ይህን ያየው የማነ ብው ብሎ፣ ተቆጣና ሾፌሩን «ድረስበት» አለው፣ ደርሰንበት እንዳያልፍ መንገድ ተዘጋበትና የማነ ሽጉጡን መዝዞ ወደ ሾፌሩ ሲንደረደር ከሾፌሩ አጠገብ ተቀምጦ የነበረው ቻይናዊ እንደጥይት ተተኩሶ ከመኪናው ወርዶ ሞባይሉን ከፍቶ ይደውል ጀመር። የማነ ያንን የደነገጠ ቻይናዊ ከምንም ሳይቆጥረው፣ ይታዘባልም ሳይል፣ ሾፌሩን ጎትቶ አውጥቶ እኛ ያለንበት መኪና ውስጥ በማስገባት መንጃ ፈቃዱን ነጠቀው። መኪናው እቆመበት ቦታ እንዳለ ቻይናውም ዳር እንደቆመ፣ ሾፌሩ ከኛ ጋር ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ተወሰደ። እኔና ሌሎች እንዲተወውና ይቅርታ እንዲያደርግለት፣ ያም ቻይናዊ ምናልባት ሊያወራና ስም ሊያጠፋ ስለሚችል እለፈው ብዬ ብንለምነውም አልሰማንም። ያ የፈረደበት ሾፌር ከድርጅቱ ፈርሞ የተረከበውን ተሽከርካሪ መንገድ ላይ ከነቁልፋና ከያዘው እንግዳ ጋር ትቶ ሳይታመም ላይታከም ፖሊስ ሆስፒታል ገብቶ እኛ ታክመን እስክንጨርስ ድረስ መኪና ውስጥ ዋለ። የማነ ከኔ ጋር ፊዚዮቴራፒ ክፍል ሲመጣም በጣም ለመንኩት፣ ጉዳዩ ከቻይናዊው ሰው ጋርም ሊያስከትል የሚችለውን ቅሬታ በተመለከተ ለማስረዳትና ለሾፌሩ ይቅርታ ለማስገኘት ሞክሬ ተቀባይነት አላገኘሁም።

ህክምናችንን ጨርሰን ወደ ወህኒ ለመመለስ ስንሰባሰብ እንደገና ልመና ጀመርን በየተራ። ሾፌሩም እራሱ ለመነ።በመጨረሻው ላይ የማነ ሾፌሩን መታወቂያውን አምጣ አለውና አይቶ ሲያበቃ በጣም በለሰለሰ አንደበት ለምን ቀስ ብለህ ረጋ ብለህ አትነዳም፣



እኛንም አደጋ ልታደርስብን ትችል ነበር።በማለት ያ ሁሉ ቁጣ ብስጭት ቀረ ይህን ሁኔታ በመጠቀም እንደገና ለመንኩት ምን እንዳቀዘቀዘው ባላውቅም ቀዝቅዟልና።በመጨረሻውም መኪናው ቆሞበት በነበረው ቦታ ስንደርስ መኪናውም ቻይናዊውም የሉም።የማነ የሾፌሩን መሥሪያ ቤት ሲጠይቀው ከቆርኪና ጣሳ ፋብሪካ ፊት ለፊት መሆኑን ነግሮት እዚያ ስንደርስ ሾፌሩን መንጃ ፈቃዱንና መታወቂያውን መልሶለት አሰናበተው።ሾፌሩ በወህኒ ቤት እያለሁ ሁለት ጊዜ ፍራፍሬ ይዞ መጥቶ ጠይቆኛል፣ የማነ ለምን ከቁጣው ባንድ ጊዜ መታወቂያውን ሲያይ እንደተለወጠ የገባኝ ሲጠይቀኝ ባገኘሁት መረጃ ነው። ለካ ሾፌሩ የአድዋ ልጅ ነበር።

የማነ ከዚህ የባሰም ሲያደርግ ባየው አይደንቀኝም።አንዳንድ ጊዜ ወደኛ ዞን ይመጣና ማንንም ሳያናግር የዞንን አስተዳደር ሳይጠይቅ ወይም የዞን ሃለፊውን ሳይዝ ዝም ብሎ መጥቶ በየክፍሉ ገብቶ ተሽከርክሮ ይወጣል።ፍተሻ በሚኖርበትም ጊዜ የተለየ ሁኔታ አይበታለሁና ጠባዩ እንዲሁ ነው ብዬ ትቼው ነው የከረምኩት። እሱ ግን ሁል ጊዜ ስንገናኝ ያው ሆስፒታል ስሄድ ሊያናግረኝ ካፌ ክፉ እንዲወጣ ይሞክራል እኔ ደሞ ትርፉ ስለማይታየኝ « ችግርህ አለማወቅ ነው» ስለው እየነደደው ዝም ይላል። ለኔ ያ ግልግል ነው።

ወደ ሆስፒታል የሚወስዱን ሃላፊዎች የተለያየ ጠባይ አላቸው።አንዳንዶቹ እያጫወቱን እያበረታቱን፣ ለምንጠይቀው ተገቢ መልስ እየሰጡን የሚቻለውን ትብብር ሁል ሳይነፍጉን ስለሚወስዱን እናከብራቸዋለን።አንዳንዶቹ ደግሞ ሲያዩን በመደንገጥ ይጀምሩና ድንጋጤያቸው ሳይለቃቸው በየምክንያቱ እንደበረገጉ ደርሰን እንመለሳለን። ልዩ ስሜት የሚፈጥሩብንና ለጊዜውም ቢሆን ታሳሪነታችንን የሚያስረሱን አሉ።በነጻነት ሳይጨነቁ፣ ሳይበረግጉ፣ አሳክመው ቀጠሮ እንዳንረሳ አስታውሰው፣ሃኪሞች ጋር እንደልብ እንድንነጋገርና በሽታችንን በረጋ መንፈስ

እንድናስረዳ ሲያስፈልግም እያገዙንና ሁኔታውን በማስረዳት የሚረዱን ሰዎች የሆኑ ሰዎች አሉ።

በቤተሰብ ጥየቃ ሰአትም አንዳንድ ጊዜ የማነ ሲመጣ እየተጀነነና « እኔ ነኝ ፈላጭ ቆራጭና ብትጠነቀቁ ይሻላል» በሚል ስሜት ነው አረማመዱ ሁሉ።አንድ ቀን ትዝ ይለኛል የማነ የፖሊስ ልብስ ለብሶ ኮፍያውን ሳያደርግ ከውስጥ የለበሰው ደም የሚመስል ቀይ ሆኖ በጭራሽ ከአለባበሱ ጋር ስለማይሄድ «የማነ ካናቴራህ ከልብስህ ጋር አልተዋሃደምና የሸሚዝህን ቁልፍ ቆልፈው» ብዬው ነበር ያን እለት የሰጠኝ መልስ ምንግዜም የማልረሳው ነው። ያለኝ «አንተ ሸሚዜን ምን አሳየህ?» ነበር ያልገባው ጉዳይ ቢኖር እኔ ፈልጌ ሳይሆን ያየሁት ሸሚዙ ከሩቅ ስለሚጣራ ነበር ግን የማነ ይሄ አልገባውም።

በሌላ ቀን እንዲሁ ቤተሰብ ግንኙነት ቦታ ሲያልፍ ወንድሜ ጓደኛዬ ሞሐመድ ያመጣልኝን ፖምና ሌላም ስንቅ ብዛቱን አይቶ «ካለዚህ አትበሉም እንዴ ዳሩ ይህን እየበላችሁ ምኑን ታሰራችሁ» በሚል የቁጭት አነጋገር ተለያየን።

የማነ ባለበት ቦታ ሁሉ የማይጠፋውና ለኛ ያለው ብቻ ሳይሆን ታራሚውን በሙሉ የሚያይበት አመለካከቱ በጣም ጭካኔ የተሞላበት ሰብአዊነት የማይታይበት ከደንብን ሕግ ውጪ የራሱን እርምጃ የሚወስደው ደሞ ፋንታሁን ይባላል።ከኔ ጋር ለመቀራረብ ቢጥርም ቤተሰብ ፍተሻ ላይ የሚያደርገውንና ፍርድ ቤት ስንሄድ በሌሎች ላይ የሚያደርገውን ስለማይ አዝንበታለሁ፣እሱም አንድ ቀን በስነስርአት ጉድለት ወይም የግቢው ሃላፊዎች ሳያውቁ በድብቅ በሚያደርገው የእስረኞች ግንኙነትና ድጎማ መግባቱ የሚቀር አይመስለኝም።በኔ በኩል ግን አያድርግበት ነው የምለው። እስር ቤትን ለማንም አልመኘውምና።

ይህን ይህን እያየሁና እየሰማሁ ያ የተባለ የቀጠሮ ቀን እንደምንም ይደርስና ቁርጣችንን አውቀን



እንገላገላለን፣ እርግጥ ምንም ይሁን ምን ፍርዱ ከሕግ ስነስርአት አኳያ እንደማይሆንና ከበላይ በሚመጣ የውሳኔ ሃሳብ እንደሚፈጸም እናውቃለን ያም ቢሆን ቁርጡን አውቆ ለዛ ተዘጋጅቶ መቀመጥን የመሰለ አማራጭ አይታይም።

ቀስ በቀስ ያ የሚጠበቅ ቀን ደረሰ።ዳኞችም አቃቢያኖችም በሰአቱ ይመጣሉ ተብሎ ይገመታል።ዛሬም ልክ እንዳለፈው ፖሊሶቹ ቁጥራቸው በርከት ያለ ሆኖ አብዛኛዎቹ አዳዲስ ናቸው።እኛም ተዘጋጅተን ስንጠብቅ የውጡ ጥሪ መጣና ወደተዘጋጀልን መኪና ስንገባ ፍተሻው ከሌላው ጊዜ የተለየ ነበር።እያንዳንዷን ወረቀት አገላብጦ ማየት፣ሻርፕ አታድርጉ ማለት፣መለዮም ያደረግነውን ተዉት እንደማለትም እየቃጣቸው ነበር።በዚህ ላይ የኛ ዞን ምክትል ሃላፊ ቀደም ሲል ዋና የነበረው ወሮታው ደንጋጣና ከጳጳሱ ቄሱ አይነት ለኛ ያለውን ጥላቻ በማሳየትና እኛንም ቢሆንለት በማበሳጨት ታማኝነቱን ለበላዮቹ ለማረጋገጥ የሚሞክር ሞኝ ነውና ዛሬም በፍተሻው ጊዜ በሩ ላይ ቆሞ ፈታሽ ፖሊሶችን ምልክት በመስጠት ጠንክር እንዲሉ ይመክራል።

የተፈለገው ሁሉ እየተደረገ ወደ መኪናው ገብተን ተንቀሳቀሱ የሚል ትእዛዝ ሳይሰጥ መነቃነቅ የለምና እንጠብቃለን።ግማሽ ሰአት ያህል ከጠበቅን በኋላ መኪናው ከዞኑ በር ላይ ተንቀሳቅሶ ወደ ዋናው በር ተጠግቶ ቆመ። ሌሎች አባሪዎቻችንም በየመኪናቸው ሆነው በመጠበቅ ላይ ናቸው።ሃላፊዎቹን ሲያሰኛቸው ወጥተን ወደ ፍርድ ቤቱ መንገዳችንን ቀጠልን።ዛሬም ስንደርስ ዳኞችም አቃቢያንም የሉም።ቤተሰቦቻችንና ተመልካቾች አስቀድመው ገብተው አዳራሽ ውስጥ ናቸው። ይህን የምናውቅበት መንገድ በር ላይ መዝጋቢዎችና ፈታሾች ከቦታቸው ሲጠፉ ነው።ቦታቸው ከአጥር ግቢ ውጪ በበሩ ጎን ላይ ነው።ዛሬም በቦታቸው ስለሌሉ መግባታቸውን ያወቅነው በዚያ ነው።

ያው እንደተለመደው በመኪናችን ቁጭ ብለን ሳለን ወደመጸዳጃ ቤት በሚል ሰበብ እየወጣን እግራችንን እናፍታታለን።እንዲህ እንዲህ እያልን ቀስ በቀስ ዳኞች መጡ፣አቃቢያን ግን ድራሻቸውም የለም።የተለመደ ነው አርፍደው እየተጀነኑ መምጣትና አዲስ አልሆነብንም።ወደ አዳራሽ ግቡ ተባልንና ከመኪናው እየወረድን ወደ በሩ ስናመራ ላለፉት ጥቂት ሳምንታት ያላገኘናቸውን አባሪዎቻችንን ስላገኘን መግባቱን ትተን ሰላምታ መለዋወጥ አስቀደምን።ፖሊሶቹ ከሃላፊዎች በሚደርስባቸው ቁጣና ግልምጫ ግቡ እያሉ ያዛሉ እኛም ሲበቃንና ወደአዳራሽ ስንገባ አሁንም እንደተለመደው ቤተሰቦቻችንና ሌሎችም (ከኛ በስተጀርባ ከሚቀመጡት ፖሊሶችና የደህንነት አባሎች በቀር) ቆመው ይጠብቁናልና እንደገባን በአክብሮት ሰላምታ ሰጥተን ወደየመቀመጫችን በመሄድ ከቤተሰብ ጋር የምልክት ሲያመችም በሹክሹክታ መነጋገሩን ቀጠልን።

ሰማዩ በደመና እንደጠቆረ ሁሉ የቤተሰቦቻችንም ፊት የወዳጆቻችን አመለካከትና ስሜትም እንደሰማዩ ነው።እኛ አስቀድሞ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከሞት የሚደርስ ቅጣት ሊያስወስን ይችላል የሚል መመርያ የሆነ አስተያየት ከተላለፈ እለት ጀምሮ ከዚያ የተሻለ ነገር እንደማይወሰን መጠርጠራችን አልቀረም እርግጥ ቀደም ብሎ አንዳንድ የተለየ ግምት ያለን ነበርን።

የተለየ ግምቱም ቢሆን የሚሻሸውና የሁሉንም ሊባል የሚችለውን ቁጥራችንን ወደ አንድ ግምት ያመጣው ባለፈው ችሎት ዳኝ አዲል አላዳምጣችሁም ከማለትም አልፎ መከራከር አለመከራከራችንን እራሱ በወሰነልንና አይከራከሩም በሚል፣ የኛ ውክልና ሳይሰጠው አሳፋሪ የግሉን ውሳኔ በመስጠቱ ነበር።

አቃቢያን በተለመደው መጀነናቸው ገቡ።የዳኛ አዲልን ውሳኔ ያወቁት ይመስላል።ወደኛ እየተመለከቱ «ተሰርቶላችኋል» የሚሉ አይነት እየተጠቃቀሱ ይሳሳቃሉ።አንዱ ላንዱ አንድ ነገር ሹክ ይለዋል፣ ደሞ ሌላው በተራው፣ሳቁ ቦታውን ስቷል ዛሬ በሚወሰነው



ውሳኔ የሚሳቀው በኛ ሳይሆን በፍርድ ሥርአቱ ላይ ነው።ደርግም ፈርዶ ገሎ ነበር።ያንንም ፍርድና ግድያ ልክ ነው ብለው የተቀበሉ 10 ይሁኑ 15 አልጠፉም።ዛሬም የዚያን አይነት ነው።ብዝሃኑ ኢትዮጵያዊያን በሚሰጠው ፍርድ ያዝናሉ፣ የሃገራችንን የፍትሕ ስርአት ያማርሩታል፣ ይታዘቡታል።

አቃቤ ሕግና ዳኞች ምናልባት በዛሬው እለት በሚከናወነው የፍርድ ሂደትና ውሳኔ በበላዮቻቸው ምናልባትም ሚሌኒየሙ ደርሷልና የሚሌኒየሙ ምርጥ ዳኞችና የሚሌኒየሙ ምርጥ አቃቢያን ተብለው ሳይሸለሙ ቢቀሩ ይህን ፍርደ ገምድል ፍርድ ያስተላለፉበትን ቀን በምር ደግግመው ይረግሙታል።

እርግጥ ያ ቢደረግ ፊት ለፊት መድሎው ሊታይ ስለሚችል በሌላ ዘዴ ሊደረግላቸው ይሞከር ይሆናል ቢደበቅ ከሕብረተሰቡ የሚሰወር አንዳችም ነገር ሊኖር ስለማይችል መሰማቱ አይቀሬ ነው።

በደርግ አገዛዝ ዘመን የተፈጸመ አንድ አስቂኝ የፍርድ ሂደት እንደቀልድ ተደርጎ ሲነገር ነበር።

አንድ ነጋዴ የንግድ ቤቱን ንጸህና አልጠበቅህም ተብሎ ዳኛ ፊት ይቀርባል።ክሱ እንደሚያመለክተው ነጋዴው የንግድ ቤቱን ሽረሪተረ በሸረሪት ድር አድርጎ የሚሸጠው እቃ ሁሉ በሸረሪት ድር የተሸፈነ ነው ይህ ደግሞ የሕብረተሰቡን ጤንነት ይጎዳል።የንግድ ፈቃድ ሲያወጣም የገባው ቃል ለተጠቃሚው የሚያቀርበውን ቁሳቁስ ንጽህና እንደሚጠብቅና ያንንም ውል እንደሚያከብር ቃል ገብቷል ተብሎ ነው።

ይህ የክሱ መሰረት ነው ነው ያሉት ከሳሾቹ።

ተከሳሽ ደግሞ እኔ የንግድ ቤቴን በንጽህና የምይዝ ለመሆኔ የአካባቢው ተጠቃሚ ሕብረተሰብ ሊመሰክር ይችላል።የ ሱቁን ንጽህና የሚጠብቅልኝ በወር የምከፍለው ለዚሁ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያም አለኝ።እርግጥ ቀደም ሲል ይህንን ሥራ

ሲሰራልኝ የነበረው ሰው የአሁኑ ከሳሼ ቤተሰብ ነበር ግን ሥራውን በደንብ ማከናወን ስላልቻለና እኔም የገባሁትን ቃል የሚያፈርስብኝ ሆኖ ስላገኘሁት አስፈላጊውን የሥራ መፈለጊያና ካሳም ከፍዬ በማሰናበት አሁን ብቃትም እውቀትም ችሎታም ንጽህናም ያለው ሰራተኛ ቀጥሬያለሁ ስለዚህ የተመሰረተብኝ ክስ አለአግባብ ነው ይላል፡፡

ዳኛው ከሳሽ አቃቤ ሕግ ዘመዱን ማስቀጠሩንና የክሱም መሰረት ሽረሪት ድር ሳይሆን የከሳሽ አቃቤ ሕግ ቤተሰብ ከሥራ መባረር መሆኑን ሲረዱ በንዴትና በማስጠንቀቅ «እዚህ የቀረብከው የንግድ ቤትህን ንጽህና አልጠበቅህም ውለታ አፍርሰሃል በሚል እንጂ ስለሰራተኛ ቅጥር ጉዳይ አይደለም፡፡በሱቅህ ውስጥ ሸረሪት ድር ተገኝቷል ነው ክሱ፣» ሲሉት «ምንድን ነው ሸረሪት? ክቡር ዳኛ» ብሎ ሲጠይቅና ድንገት ወደ ዳኛው አናት ቀና ሲል አንድ ድር የሚመስል ነገር በጣራው ላይ ተጋድሞ በማየቱ «የዚያ አይነት ነው?»ሲል ዳኛው ቀና ቢሉ በአናታቸው ላይ ሸረሪት አድርቶባቸው ጉዳዩ ወደእርሳቸው፣ ሕብረተሰቡን በፍትሕ ስርአት በሚያስተናግዱበት የችሎት አናት ላይ ተጎልቶ በማየታቸውና ተከሳሽ ወደ ጣራው ሲያመለክትም በዚያ የነበረ ተመልካች ሁሉ በማየቱ ዳኛ ው በንዴት ቱግ ብለው «ተከሳሽ ስለቀረበበት ክስ ማፍረሻ የሚሆን ምንም ባለማቅረቡ ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቷል የዚህንም ውሳኔ በሚቀጥለው ችሎት እንሰጣለን» ሲሉ ተከሳሽ «ክቡር ዳኛ ለመሆኑ በከሳሼ ቤትና በዚህ በተከበረው ፍርድ ቤት ያለውን ሽረሪት በተመለከተስ ማነው ፍርድ የሚሰጠው? እኔ ግን ሽረሪት ማለት ምን እንደሆነ ዛሬ በዚህ ችሎት በማየቴ ከቅጣቱ ይልቅ ያገኘሁት ትምህርት በልጦብኛልና ፍርደ ገምድል ቢሆንም ቅጣቱን ለመቀበል ዝግጁ ነኝ» በማለት የሚቀጥለውን ቀጠሮ ለመጠበቅና ውሳኔውንም ለመቀበል ተዘጋጀ፡፡

የችሎቱ ስርአት ተፈጽሞ ዳኛው ሊወጡ ሲሉ ተከሳሽ « ክቡር ዳኛ የኔ የሌለ ሽረሪት ድርስ ተወሰነበት ለመሆኑ በከሳሼ ቤት ከመግቢያው ጀምሮ የተዘረጋው



ሽረሪትና በዚህ በፍትህ ቤት ስላለው ሽረሪትስ መቼ ሊወሰን ነው?»ብሎ ቢጠይቅም መልስ ሳይሆን በአፍ እልፊት ተጨማሪ ቅጣት እንደሚጣልበት ተበይኖ ችሎቱ በሰጠው ቀጠሮ ተዘጋ፡፡

ያ ፍርድ አሰጣጥ ትንሽ ተጨምሮበት እንደሁ እንጂ በእውነት የተፈጸመ ነው፡፡ ሂደቱ በዚያን ዘመን ላይ አልቆመም አሁንም መልኩንና ይዘቱን እየቀየረ አለ፡፡ዛሬም ከዚያ የተሻለ አንጠብቅም፡፡የሽረሪቱ ድር ያደራው ዳኛው አናት ላይ ስለሆነ ከራሳቸው አይወርድም የሚል ግምት የነበራቸው በርካታ ነበሩ፡፡

ፍትሕ ለሁሉም የሕብረተሰብ አካላት እኩል የሚያገለግል፣ ከራሱ ስነስርአት ውጪ ማንም መመርያም ሆነ አመራር ሊሰጥበት የማይችል መሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ላይ በዝርዝር ተቀምጦ ሳለ ያን ሕዝባዊና ሕገ-መንግሥታዊ አደራ ለመብላት ምን ያህል ይሉኝታ ቢስ መሆን እንደሚያስፈልግ በኛው ክስ ላይ እያየነው ነው፡፡እነሱ ንደው ንደው የጨረሱትንና ባዶ ያደረጉትን እኛን ሊንዱት ነው ብለው ያልተደፈረ በማስመሰል ክስ መመስረታቸው ምን ያህል ሕዝባዊና ሃገራዊ ንቀት እንደሆን እያስገነዘቡን ነው፡፡

«ሌባ እናት ልጇን አታምንም» ወይም «የገብርኤልን ስለት የበላ ያስለፈልፈዋል እንዲሉ» ሆነና ወያኔ/ኢህአዴግ ያደረገው ነገር እያስበረገገው ምንም ያላደረግነውንና ሲያደርገውም በአካባቢው ያልነበርነውን ለክስ ለውንጀላ ማቅረቡ የተረቱ አይነት ሆኖበት ነው፡፡

ዛሬ ሻእቢያን እየኮነነ እኛን ከሻእቢያ ጋር ሊያስተሳስረን የሚሞክረው አቃቤ ሕግ ሽመልስ እኮ በ92 የሻእቢያና የእኛ ሃገር ጦርነት ወቅት ኢትዮጵያ ኤርትራን መውረር የለባትም ብሎ ወራሪን ተወራሪ ተወራሪን ወራሪ አድርጎ በጨነገፈችው ጋዜጣው ላይ ለሻእቢያ ወግኖ ጥብቅና ቆሞ የነበረና በዚህም ለጥቂት ወራት እስርን ቀምሶ የወጣ ነበር፡፡ ዛሬ ደሞ ከጳጳሱ ቄሱ ሆኖ እኛን ኢትዮጵያዊያኑን በሀገር ማጥፋት

ወንጀል ለመክሰስ መድፈሩ በታሪክ የሚያስተዛዝብ ጉድ ነው::

ማን ያውቃል ምናልባትስ ይህ ጉዱ እንዳይወጣበት ሳይሆን ይቀራል እድሜ ልክ አይበቃቸውም በሞት ይቀጡልኝ ብሎ እሪ ኡኡ ሲል የነበረው? ለመሆኑ ዳኞችም ሆኑ አቃቢያን በሕዝቡ መሃል አንገታቸውን ቀና አድርገው ለመሄድ ብቃቱና ጥንካሬው ይኖራቸው ይሆን? በፍትሕ ሚኒስቴርስ ባለው ቢሯቸው ወንበር ላይ እንደፍትሕ ባለሙያ ደፍረው ይቀመጡበት ይሆን?

ያም ሆነ ይህ ገብተን ጥቂት እንደቆየን ከመግባታቸው ወዲያው ዳኛ አዲል ወደ ውሳኔያቸው ለመግባት በመቸኮል ስሜት እየተጠራን መኖራችን ተረጋገጠ::ወሀኒ ቤቱ ሁሉም ተከሳሾች እንዳለን አረጋገጠ::

ዳኛ አዲል የመግቢያ ንግግር አደረጉ::ጉዳዩ ለዛሬ ያደረው ባለፈው በተበየነው መሰረት ውሳኔ ለመስጠት ነው::ካሉ በኋላ በቡድንም በተናጠልም ስማችንን በመጥቀስ ከየተከሰስንበት ወንጀል አንዳንድ በመጣልና ሌላውን በማጽደቅ የፍትሕ ስርአቱን ሚዛናዊ ዴሞክራሲያዊና፣ ገለልተኛ ለማስመሰል ወደ ብይኑ አመሩ::

ከማንም ላይ ምንም ይቀነስ ይጣል ሁኔታው ግን ሁሉንም አቃቤ ሕግ በፈለገው መንገድ ሊያስፈርድብን በሚያስችል መልኩ ነው የተዘጋጀው::

የሁሉም እንደአስፈላጊነቱና እንደሚያመች ሆኖ ተዘርዝሮ ማጠቃለያው በዕድሜ ልክ እሥራት እንዲቀጡ ወስነናል የሚል፤ ሆነ::ይህ ፍርድ ሁሉንም የቅንጅት አመራር አባላትን የሥራ አስፈጻሚ አባላትን፣ ተመራጮችን፣ጥቂት ጋዜጠኞችን ያካተተ ነው::

ፍትሕ ጭልጥ ብሎ ገደል የገባበት፣ ታይቶ የማይታወቅ የፍትሕ ሂደት የተከናወነበት፣ ለወደፊት



ትውልድና የፍትሕ ሙያን ለሚማሩ ሁሉ ፍትሕ እንዴት ተዛብቶና ግን እውነት መስሎ፣በመመርያ እየተከናወነ ግን እንዴት ነጻ ነው ሲባል እንደሚችል፣የፍትሕ ባለሙያዎች እንዴት የጭንቅና የምጥ ፍርድ ሊሰጡና እንቅልፍ ሊያጡ እንደሚችሉ፣ የሚታይበትና የመማርያ መዝገብ እንደሚሆን እምናለሁ::

በዚህ ሂደት በተከናወነ የፍርድ ሂደት ዕድሜ ልክ ተበይኖብንም አላጠግብህ ያለው አቃቤ ሕግ ምንም እንኳን ቀጠሮው ለሌላ ጊዜ ተላልፎ ቀጣዩ የይግባኝ ቀጠሮ ሳይነገረን ቢቀርም ሞት እንዲፈረድብን ይግባኝ ብሎብናል::

እውነቱን ነው እኛን በእድሜ ልክ ማሳሰር ማለት ያው ከ18 ዓመት በኋላ መፈታት ስለሚሆንና ጥቂቶቻችን ደግሞ ያንን የሚያህል እድሜ ልንሰጠው የማንችል ቢሆንም ወጣቶቹ ተርፈው ወደፊት ሊፋረዱትና

«አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ

እንደገና ዳቦ እሳት ነደደብህ»

ሊያሰኙት ስለሚችሉ ከወዲሁ በሞት ተገላግሎ የኛንም ሕይወት የፍርዱንም ፋይል መዝጋት ነበር የተመኘው፣ አልሆነም::

ፍርዱ ሲጠቃለል ሁላችንም እሮይ ነው ያልነው::አዎን እሮይ::በየቀጠሮው ወደፍርድ ቤት መመላለስና ቤተሰብ በማይሆን አጉል ተስፋ ከሚጓጓ እንዲህ እቅጩን አውቆ መቀመጡን መርጠናል::ለነገሩ እኛ በጠባቡ ቦታ ታሰርን እንበል እንጂ እውነቱ ግን ሃገሪቱ ሙሉ እስር ቤት ነው:: ኑሮው ከአቅም በላይ ሆኖ፣ሰላም ሳይኖር፣ እርስ በርስ ተፈራርቶ፣ ወጥቶ መመለስ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ምኑ ነው ኑሮ ተብሎ የሚኖረው?

የ«ፍርድ ቤቱ»ን አካሄድና ብይን በተለይም የመጨረሻውን ብይን እለት በተመለከተና ዳኞች ማስረጃ ብለው ሲቀበሉ የነበረውን ማስረጃ ለአይነት ያህል ማስረዳት የሚችለውን የጋሽ መስፍን (ፕሮፌሰር) አንዲት ፅሁፍ እንመልከት።

ጋሽ መስፍን እኔን በተመለከተ ይበል እንጂ የሁላችንም የተለየ አልነበረም። እያንዳንዳችን ላይ የቀረበ ማስረጃ የተባለው ሁሉ ቅንጅት ለራሱ በመዝገብነት የቀረጸው የስብሰባ የክርክር ቪድዮ እንጂ ሌላ የቀረበ የለም።

## በሕግ ዓምላክ

## ከመስፍን:ወ/ማርያም:(ፕሮፌሰር)

## ቃሊቲ/1999

### 1– እግዚአብሔር ያሳይዎ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕግ ረግድ ልዩ ባሕል አለው፤ በኢትዮጵያ ባሕል ማንም ዳኛ ነው፤ማንም ምስክር፤በሕግ ዓምላክ ሲባል ውሃም ይቆማል ተብሎ የሚታመንበት ባህል ነው፤ የመንገድ ወይም የጎረቤት «ዳኛ»የባላጋራቹን ኩታ ጫፍና ጫፍ አስሮ ብቻቸውን ወደ አጥቢያ ዳኛ እንዲሄዱ የሚያደርግበት ባህል ነው፤ማንም ኢትዮጵያዊ በዳኛነትም ሆነ በአስተዳደር በደል የደረሰበት እስከመጨረሻው ባለስልጣን አስከ ንጉሠ ነገሥቱ የመድረስ መብትን የሚያጎናፅፍ ነው።በእግዚአብሔር የማያምኑ ከወንበሩ ላይ ሲወጡ እግዚአብሔር ያሳይ የሚባል ነገር ቀረ፤እግዚአብሔር ሲሻር በሕግ ዓምላክም አብሮ ተሻረ። የታሰበው ባህላዊውን የሕግ ሥርአትና ዕምነት በአዲስ ዘመናዊና ምእራባዊ «በሕግ መገዛት» በሚለው ሥርአት ለመተንት ነው ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕግ ዓምላክም ሳይሆን በፈረንጆቹ በሕግ መገዛትም



ሳይሆን በጠመንጃ መገዛትን እንደባሕል እንዲቀበል ተገደደ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቤተ እግዚአብሔርንና ፍርድ ቤትን ያከብራል በአንድ በኩል ሁለቱም የእግኢአብሔርን የበላይነትና የእግዚአብሔርን ሕግ የሚቀበሉ ናቸው፤በሌላ በኩል ሁለቱም የሰው ልጆች ሁሉ በእኩልነት እንዲታዩ የሚያደርጉ ናቸው፤በዚህ ባህል ውስጥ ያለፍሁ በመሆኔ እኔም ለሁለቱም ከፍተኛ አክብሮት አለኝ።የሚያረክሳቸውም ሁኔታ ሲፈጠር በጣም ያሳዝነኛል፤ያሳፍረኛል፤ከውስጤ ያለ አንድ ክቡር ባሕርይ የጠፋ ይመስለኛል።ቤተ እ4ግዚአብሔርንና ፍርድ ቤትን የሚያረክስ ነገር ሳይ እኔም አብሬ መርከሴ ይሰማኛል። በአፄኃይለሥላሴ ዘመን ቤተክርሰቲያን ውስጥ ጠመንጃ ሳይ ቤተእግዚአብሔር የረከሰ መስሎ ይታየኝ ነበር፤አሁን በወያኔ ዘመን በፍርድ ቤቶች ውስጥ ጠመንጃ ሳይ የፍርድ ቤት መርከስ ይሰማኛል።( እኛ በተከሰስንበት ችሎት ለ12 ወራት ያህል ወታደሮቹ ጠመንጃቸውን ትተዋል፤በሌላው ፍርድ ቤት ግን ያው ነው)።የመርከሱ ስሜት የግል ብቻ አይደለም ማሕበረሰባዊ ነው፤ሃገራዊ ነው ግንቦት 24 ቀን 1999፤ም በከፍተኛው ፍርድ ቤት የነበረ ሰው ሁሉ የፍርድ ቤቱን መርከስና መዋረድ እስከ ነፍሱ ጠልቆ ተሰምቶታል በሁዋላ እንደታወቀው አቃቤ ሕግ የተባሉትንም አስገርሟል።

ጠመንጃ ፍርድ ቤትን የሚያረክሰውን ያህል ባቃቤ ሕግ ስም ባጌጠ ካባ ተሸፍነው ፍርድ ቤቱን የሚያነቃንቁት ሎሌች ፍርድ ቤቱን ያረክሱታል፤አቃቤ ሕግ ማለት ሕግን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ የቆመ የሕዝብ የሃገር አገልጋይ ነው። በኛ ክስ አቃቢያነ ሕግ ተብለው የቀረቡት ሶስቱ ቢያንስ ሁለት ተኩሉ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል። ቁም ነገሩ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው ሳይሆን የወያኔ ማሕበር አባሎችና ሎሌች መሆናቸው ላይ ነው፤ በዚህም የተነሳ በትእቢት ተሞልተው ለፍርድ ቤቱ እንደአዛዥ ለመሆንም ይቃጣቸው ነበር፤ዋናው ሥራቸው አድርገው የያዙት ዕውነትን መደበቅ

ዕውነትን ማጣመምና ውሸትን ማምረት ነበር፤፡ በምርጫ 97 የተነሳ ባጣሪ ኮሚሽኑ መረጃ መሠረት 193 ሰዎች በግፍ መገደላቸውንና ከሰባት መቶ በለይ መቁሰላቸውንና አከለ ጎደሎ መሆናቸውን ለመጥቀስ የመንፈሰ ወኔም ሆነ የሕግ ግዴታ አልተሰማቸውም። ተከሳሾችን አድመኞችና ወንጀለኞች እያሉ ሲናገሩ የሕጉ መንፈስ በአእምረሯቸው እንዳልሰረጸ ያሳይ ነበር።ለሕጉ ታማኝ መሆንን ትተው አሳዳሪያቸውን ለማስደሰት ተከሳሾቹን በጭፍን ውሸት ሲወነጅሉ መስማት የፍርድ ቤቱን መዋረድ የሚያመለክት ነበር፤ፍርድ ቤቱ ውስጥ ባዛኸኝነትና በበላይነት መገኘታቸውን በተጨባጭ የሚያሳየው የከሳሽ ጠበቃዎች ፊት ያለው ጠረጴዛ ደማቅ ጨርቅ የለበሰ ሲሆን በተከሳሾች ጠበቃች ፊት ያለው ግን እራቁቱን ነው፤ይህ በጠረጴዛዎቹ ልዩነት የሚታየው አድል በሥራቸው ላይም ይንጸባረቃል «እኛ እኮ የምንወክለው መንግሥትን ነው» በማለት ለማስፈራራት መሞከራቸው ሕግን ለመወከል ሃላፊነት እንዳለባቸው የማያውቁና በድፍረታቸው ብቻ የተመረጡ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል።

ፍርድ ቤቱ በነዚህ ሰዎች ተጽእኖ ሥር ሆኖ ባለጉዳዮች ያቀረቧቸውን ጉዳዮችና ጥያቄዎች ሁሉ ውድቅ እያደረገ ከ20 ወራት በላይ በእስር እንዲቆዩ አደረገ፤ በዚህ ረጂም ጊዜ ውስጥ ፍርድ ቤቱ በከሳሽ ጠበቃች እየተመራ ዓለም እያየው አዘቅት ውስጥ ገባ፤የከሳሽ ጠበቃዎች አዘቅቱ አፋፍ ላይ ሲደርሱ ዘወር አሉና በመዳናቸው ተገርመው «ያልጠበቅነው ነበር» አሉ፤ እዚህ የደረሱት እንዴት ነው።

ሁለት አጠቃላይ አስተያየት

ብዙ አጃቢ ክሶች ቢደረደሩም ዋናው ክስ የሕገ መንግሥቱን ስርአት በአመፅ ለመገልበጥ መሞከር የሚል ነው።

ለከሳሽና ለተከሳሽ ሕገመንግሥቱ አንድ ከሆነ ተከሳሾች ሕገመንግሥቱን በሃይል ለማፍረስ አንድም ምክንያት የላቸውም አቅምም የላቸውም፤ እንዲያውም



ተከሳሾች ሁሉ ሕገመንግሥቱ የሚያጎናጽፈውን መብትና ነጻነት ሁሉ ተመርኩዘው የተነሱ ናቸው፤አለኝታና መከታ ያደረጉትም ሕገመንግሥቱን ነበር፤ ከሳሽና የከሳሽ ጠበቆች ሕገመንግሥቱን አያውቁትም ወይም ክደውታል ለማለት የሚያስደፍሩ ብዙ ምክንያቶች አሉ፤ ከሁሉ በፊት ሕገመንግሥቱ የመደራጀት የመሰብሰብና ሃሳብን ያለምንም ገደብ የመግለጽ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ የመምረጥና የመመረጥ መብቶችና ነጻነቶች በእኩልነት ያጎናጽፋል።

የመንግሥት ስልጣን ባለቤትና ምንጩ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ሕገ መንግሥቱ ያስታውቀል፤( አንቀጽ 8 ) በድምጽ ብልጫ የሕዝቡን ድጋፍ ያገኘ የፖለቲን ቡድን ሥልጣንን በሰላም እንደሚረከብ ይደነግጋል አንቀጽ 56--60። በዚህም መሰረት አዲስ መንግሥትን መፍጠር እንደሚቻል ይናገራል።(አንቀጽ 60/2)። በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ከተደነገገው ውጪ በሃይል ወይንም በጉልበት የመንግሥት ስልጣን እንዳይያዝ ይከለክላል፤( አንቀጽ 9/3) ሕገመንግሥቱ ፍጹምና ዘለአለማዊ ባለመሆኑም የሚሻሻልበትን መንገድ ደደነግጋል (አንቀጽ 105)። ባጠቃላይ በመብቶች ጉዳይ ሕገመንግሥቱ ይህ ቀረው የሚባል የሌለበት ሰነድ ነው።

በሚያዝያ 29/97 ወያኔ/ኢህአዴግ ከመንግሥት ጋር በመተባበር በመስቀል አደባባይ ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ በነበረ ጊዜ ሊቀመንበሩና የመንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ስብሰባውን «ሕዝባዊ ማዕበል» ብለውት ነበረ «ማዕበል» የሚለውን ቃል የመረጡበትን መነክንያት ማብራራት አያስፈልግም፤ ሆኖም በሚያዝያ 30/97 ቅንጅት በዚያው ቦታ በጠራው ስብሰባ አዲስ አበባን በሙሉ አጨናንቆ « ሕዝባዊ ማዕበል» ከተባለው እጥፍ ድርብ የሆነ ሕዝብ ታየ፤ ይህ ስብሰባ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተከሂዶ አንድም እንከን ሳይገኝበት የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨዋነት አስመስክሮ ተጠናቀቀ፤ የተከሳሾቹን ሕጋዊነትና ሰላማዊነት ከዚህ ስብሰባ የተሸለ ተጨባጭ ማስረጃ ሊገኝ አይቻልም።

በምርጫው ጊዜስ? ገና ምርጫው እየተካሄደ ባለበት ጊዜ ግንቦት 7 ማታ የሕገመንግሥቱን ስርአት የሚጥስ ያስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለአንድ ወር ታወጀ ይህም ሕገመንግሥታዊ ስርአት ታገተ፣ የሃይል ወይም የጠመንጃ አገዛዝ በይፋ ታወጀ ማለት ነው፡ ቀጥሎም ግንቦት 8 ቀን ቀና ቆጠራው ሳይጠናቀቅና ለምርጫ ቦርድ ሳይደርሰው በአዲስ አበባ ከተማ ቢሸነፍም በሃገሪቱ ባጠቃላይ አሸናፊ መሆኑን ወያኔ/ኢህአዴግ አወጀ፣በዚህ አዋጅ የምርጫ ቦርድን ሕገመንግሥታዊ ሥልጣን ገረሰሰው፣ በነዚህ በተጠቀሱት ሁለት የሃይል እርምጃች በምርጫው ተወዳዳሪ የነበረው የፖለቲክ ቡድን ከሕግ ውጪ በመንግሥት የጦርና የፖሊስ ሃይል ተጠቅሞ ራሱን ወደ መንግሥትነት ለውጦ ለአሰቃቂ የግፍ እርምጃች በርን ከፈተ፣ ስለዚህም በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ብዙ ሰዎች ተገደሉ፣ተደበደቡ፣ታሰሩ፣ከቤት ንብረታቸው ተፈናቀሉ፣ ሌላ ማስረጃ ሳይፈለግ የራሱ የመንግሥት አጣሪ ኮሚሲዮን ከሞላ ጎደል በሰበሰበው መረጃ 193 ሰዎች ሲገደሉ ከ700 በላይ አካለ ጎደሎ ሆነዋል፡ ከተከሳሾቹ መሃከል ድብደባና ማስፈራራት የደረሰባቸው አሉ፣ሕገመንግሥቱን የሚቃረን ዛቻና ማስፈራርያ ዛሬም አልቆመም፣ በቅርቡ በምክር ቤቱ ውስጥ ጣታቸውንና እጃቸውን እንቆርጠለን በማለት የሕግንም የሰብአዊነትንም ሚዛን ሲሰብሩት ሰምተናል።እንደገና የግፉ ድርጊት እንዲጀመር ካልሆነ ቀደም ሲል የተደረገው ቡራኬ መስጠት መሆኑ ነው።ከሳሾች የእንደዚህ ዓይነት ግፍ ባለቤቶች ናቸው።

እነዚህ ፀሐይ የሞቃቸውና ዓለም ያወቃቸው ዕውነቶች በጥቁር መጋረጃ ተሸፍነው እንዲቆዩ የረዳው የውጭ ኃይል አፍንጫ ሰንጎ ዋጋውን እያስከፈለ ነው። በጉልበት የመንግሥት ስልጣን ይዞ ግፍን የፈጸመው ከሳሽ የግፉ ሰለባዎች ተከሳሾች ሆነው በእስር ላይ ሁለት ዓመታት ሊሞላቸው ነው፣ሃላፊነት ተጠያቂነት ከአጥቂው ወደተጠቂው ተላለፈ፣ግፍ ማለት ይህ ነው፣የበደለው ንጉሥ ባላገር ይካስ ተባለ፣ ግፍ በየትኛ ውም መልኩ ቢሆን አስከፊ ነው፣ ምክንያቱም ዜጎች



ሁሉ በሕግ ላይ ያላቸውን አመኔታና አለኝታ የሚደመስስ በመሆኑ ነው።

3-በእኔ ላይ የተሰጠው ብይን

የፍርዱን ስርአት ሽውራራነት ለማስረዳት ከዚህ አጠቃላይ መንደርደርያ ተነስቼ በተለይ በእኔ ላይ ወደ ተሰጠው ብይን እገባለሁ፣ከብይኑ ሶስት ዋና ነጥቦችን አነሳለሁ። በቅድሚያ ግን የከሳሽ ጠበቃ ዋና ማስረጃች ቪዲዮች ናቸው፣ ሰቹ የሚናገሩት ሁሉ በግልጽ ይሰማልየከሳሽ ጠበቃ የሚፈልገውን የወንጀል ማስረጃ ከማንም አንደበት ለማግኘት ባለመቻሉ ከድውይ አእምሮና ከእኩይ መንፈስ ብቻ የሚመነጭ የውሸት ጥላሸት እየቀባ ማቅረብ ግዴታ ሆኖበት ነበር።

ሀ) ቅንጅት በሰሜን ሆቴል በጠራው ስብሰባ ላይ እኔ አድማጭ ነበርሁ። መግለጫው ከተሰጠ በኋላ መድረኩ ለጥያቄና አስተያየት ሲከፈት እኔ አስተያየጥ ሰጥቻለሁ።።። ስለዚህ አስተያየቴ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ብይን ላይ «ሥልጣን ባለው መንግሥት ከፍተኛ ውንጀላዎችን ከሰነዘረ በኋላ» ይላል። ውንጀላዎች የተባሉትን ፍርድ ቤቱ አልገለጸም፣የከሳሽ ጠበቃ ለፍርድ ቤቱ በጽሁፍ አወላግዶ እንጂ ማስረጃ ተብሎ የቀረበው ቪድዮ ውስጥ የሌለ ነገር ነው።ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ተብሎ ከቀረበው ቪድዮ ውጪ የሆነውን ነገር እንዴት ተቀበለው?በትእዛዝ ነው? ወይስ በትብብር? ፍርድ ቤቱ እኔ እንድከላከል ትእዛዝ ሲሰጥ እራሱም ለማያውቀውና እኔም ለማላውቀው ጉዳይ መሆኑ እንዴት አልተሰማውም? እኔስ ብከላከል ምን ብዬ ነው?

ለ) በአንድ በአፍሪካ አዳራሽ ውስጥ በተደረገ ክርክር ውስጥ እኔ ተሳታፊ ነበርሁ፣ብይኑ እንደገና «ውንጀላ-ዎች ከቀረበ በኋላ» ቢልም ውንጀላዎች የተባሉትን አይገልፅም፣ አያይዞም የዓለም ሶሻል ሳይንቲስቶች በሙሉ የደረሱበት ውጤት እንደአከራካሪ ጉዳይና እንደወንጀል ተቆጥሮ ቀርቦአል። ይኼውም ዴሞክራሲ እንደማናቸውም ሰው ሰራሽ ሥርአት ግድፈቶች አሉት፣ዴሞክራሲን ከሌሎች ሥርአቶች የተለየ

የሚያደርገው እራሱን እያረመ የሚያድግና ወደፊት የሚራመድ መሆኑ ነው፤በአንጻሩ የአገዛዝ ስርአት በባህርይው እራሱን ማረም አይችልም፤የሚል ነው:: በምንም ዓይነት መንገድ ይህንን ደረቅ እውነት ለማስተባበል አይቻልም፤ የሚቻለው መማር ነው:: በነጻነትና በጦርነት በብልጸግናና በድህነት በእውቀትና በድንቁርና በእድገትና በኋላ ቀርነት መሀከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት ይኸው በዶሞክራሲና በአገዛዝ መሃከል ያለው ነው::እንግዲህ ፍርድ ቤት ተከላከል የሚለኝ ምኑን ነው?

ሐ) በብይኑ ውስጥ የተገለፀው ሦስተኛው ነጥብ በጣም የመነያስገርም ነው:: እንዲህ ይላል፤-

«ያለውን ሥርአትና ሕገመንግሥቱና ሙሉ በሙሉ ከማስወገድ በቀር መሻሻልና፤መታረም የማይታሰብ እንደሆነ ሲቀሰቅስ መቆየቱ፤.. .. ..

የፍርድ ቤቱ ብይን የሚያስገርምበት ምክንያት ማስረጃ ተብሎ የቀረበው ቪድዮ ሲሆን ይህንን ስናገር የሚሰማበት አይደለም:: ስለዚህም ፍርድ ቤቱ በፍፁም ያልተባለውን አሉባልታ ይዞ ብይን ለመስጠት የተገደደበት ምክንያት ምንድን ነው?

የከሳሽ ጠበቃ የውሸት ቋት መሆኑን በተደጋጋሚና በተጨባጭ አሳይቷል:: ነገር ግን ፍርድ ቤቱን እንዲህ ያሳስታል የሚል ጥርጣሬም አልነበረኝም::ብይኑ በውሸት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ያሳዝነኛል፤በጣም ያሳፍረኛል::

በቪዲዮዎቹ ላይ ሁሉ እንደተሰማው እኔም ሆንሁ ሌሎች ተከሳሾች ከሕጋዊና ከሰላማዊ ንግግር ውጪ አልተዛነፍንም::በሕገ መንግሥቱ ከተፈቀደውሃሳብን የመግለጽ ነፃነት ውጪ በነቢብም በገቢርም ቅንጣት ወንጀል አልፈጸምንም:: በበኩሌ ደሞ አንድም የምከላከለው ነገር የለም::




ተከሳከሱ ያለው ፍርድ ቤት ለመከላከል ብንሞክርም ያዳምጠናል ለማለት አያስደፍርም:: እስራ ዘጠኝ ወራት ያህል ስንታሰር የከሳሽ ጠበቃ እንደልቡ በፈለገ ጊዜ ሲናገር ለእኛ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ጥያቄችንና አቤቱታችንን ለማዳመጥ በወር አንድ ደቂቃ ሂሳብ እንኳዋንጊዜ አልሰጠንም::

በግንቦት 24 ቀን ጥያቄዎቻችንን አድምጡን የሚል የሁሉም ጥያቄ በመቅረቡ ፍርድ ቤቱ ተረበሸ፤ችሎቱን አቋርጠው ዳኞቹ በንዴትና በችኮላ ሲወያዩበት ወጡ::ሁለት ሰአት ተኩል ያህል ተከሳሾቹንም ተመልካቾቹንም የተከሳሽ ቤተሰቦችንም ከአቆዩ በኋላ በሰባት ሰአት ተኩል ግድም እንደተናደዱና እንደተበሳጩ ገብተው የጥፋተኛነት ውሳኔና የሚቀጥለው የብይን ቀጠሮ ሐምሌ 1 መሆኑን ነግረውን በችኮላ ሲወጡ ተከሳሽ ሁሉ «እግዚአብሔር ይስጣችሁ!»በማለት ተሰናበትናቸው::

በኋላ እንደተገነዘብነው ሐምሌ 1 ዕሁድ ነው!!! ይህንን ስሕተት የፈጠረው ሁኔታ « ጥፋተኛ ናችሁ» በሚለው ውሳኔ ላይ ተፅእኖ አልነበረውም ለማለት ይቻላል?

## በብዙ ሰዎች ሕይወት ላይ ፍርድ መስጠት



**እሁድና ሰኞን** የማሳሳት ያህል ከቀለለ ምን ይከብዳል?::

# ቀድሞ ወዳጆቼ ለነበራችሁ

«ታዘብኳችሁ  እንጂ........»

ወደ ቅንጅት ፖለቲካ ፓርቲ ከመቀላቀሌ ቀደም ብሎና ከዚያም እስከጥቂት ወራት ድረስ ብዙ ወዳጆች ነበሩኝ::ለችግራቸውም ለደስታቸውም ቀድሜ እየደረስኩ ከጎናቸው ቆሜያለሁ::

በመዝናናቱም ቢሆን አብሬያቸው አቅሜ በፈቀደ መጠን እየተገባበዝን ማን ይበልጡን ጋበዘ ለየግላችን የሚተው ሆኖ አብረን ወቅቶች አሳልፈናል::ስቀን ተጫውተናል፣ክፉውን እንደአመጣጡ በመቀበል መፍትሔ እየፈለግን አብረን ተቋቁመነዋል::ለትላልቅ ተግባራት አብረን ትላልቅ ቦታዎች ሄደን እምነታቸውን አጉድለው ያንን በመቻል ስማቸው እንዳይጠራ የጎደለውን ሞልቼ ስማቸውን ጠብቄያለሁ::ሊያገኙ የማይችሉትን የውጭ ጉዞም ቢሆን እንዲያገኙትና ልምድ እንዲያገኙ የተቻለኝን አድርጌያለሁ::

ሚስጥራቸውን ጠብቄ፣ አመለካከታቸውን አክብሬ የኔንም እንዲያከብሩ አድርጌ አብረን ኖረን ነበር::ብዙ አብረን አምተናል::ሁለቱንም መንግሥታት እስኪበቃቸው አገላብጠን አምተናል::ጥፋታቸውን ከመልካም ተግባራቸው እየመዘንን አበሻቅጠናቸዋል::

አንዳንዶቹ ክህደት ልማዳቸው ስለሆነ አብረንም እያለን ወዳጆቻችን የሚሏቸውን የሚፈልጉትን ጥቅም በተለይም የፋይናንስ ጥቅም ሲያጡባቸው ሲክዷቸው እያየሁ ለመምከርና ለማስታረቅ ሞክሬያለሁ::ያንዳንዶቹ ክህደት አባትን ያህል ነገር እስከመካድ የሚጨክኑ ናቸው::አንዳንዶቹ ለወለዷቸው ልጆቻቸው ( ከጋብቻ ውጪ ) ምንም እሳቤ ስላላሳዩ እነሱንም በመተካት ልጆቹን ትንሽም ቢሆን ለመርዳት ወደኋላ አላልኩም::



ከራሳቸው አልፎ በቤተሰብ ደረጃም ያጋጠማቸውን ችግር እየነገሩኝ አቅሜ በፈቀደ ለመርዳትና የችግራቸው ተካፋይ ለመሆን ወደ ኋላ አላልኩም::አንድንዶቹ ከኔም አልፈው ከቤተሰቤ ጋር ቅርበት የፈጠሩ ናቸው::ቤተሰቤም በችግራቸውም በደስታቸውም በቻለው ሁሉ አብሮ ለመቆም ሞክሯል:: ይህን አድርጌ መልሱ ክስና ጥላቻ ሆነ እያሉ ሲያጫውቱኝ ግድ የለም መቻል ነው እያልኩ እንዲያልፉትና እንዲረሱት ይልቅስ ወደፊት እራሳቸውን የሚችሉበትንና በራሳቸው እራሳቸውን ሊያስተዳድሩ ሊከተሉ የሚገባቸውን መንገድ እንዲቀይሱ በመጠቆም ለማስተማርና ለመርዳት ወደኋላ አላልኩም ነበር::

የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት እያለም ወዳጅ ጓደኛ መሆን እንደሚቻል ሳያውቁ ቀርተው ወይም ለአሳዳሪዎቻቸው አለያም ለደምወዝ ከፋዮቻቸው ደስታ ለመፍጠር ሲሉ ታስሬ ስላልጠየቁኝ በፍጹም ቅሬታ አልተሰማኝም አልተቀየምኳቸውም ነበር::እኔን እሺ ቃሊቲ መጠተው አይጠይቁኝ ግና እንዴት ቤተሰቤን በስልክ እንኳን እንዴት ናችሁ ማለት አቃታቸው? ለምን ልጆቼንና ባለቤቴን ሲያዩ መንገድ መለወጥ አስፈለጋቸው?እውነት አለቆቻቸው እኔን ቢጠይቁ ቤተሰቤን በስልክ ቢያበረታቱ ተከታትሎ ጉዳት ያደርስባቸው ነበር?ምናልባት ይህ ዝም ብለው በራሳቸው ለራሳቸው የፈጠሩት ፍርሃት ይሆናል አንቀ ይዞ የሚያንደፋደፋቸው:: ያም ሆኖ እድሜ ለቅንጅቴ አንዳችም ቅያሜ አላደረብኝም::

አሁንም የሚገርመኝ ነገር ቢኖር አንዱ ካንደኛው ቀድሞ መጥቶ ግን ሌላው ሳያየው በድብቅ እንኳን ለቤትህ አበቃህ የሚሉኝ እውነትም ያስገርሙኛል::ምን አደባበቀ? ምን ከምን ከማን ነው የሚደበቀው?ለአለቆች የሚቀርብን የእጅ መንሻ ሰብቅ ፍራቻ ነው ወይስ እኔን አሁንም ወዳጅህ ነኝ ለማለት?

ውድ ወዳጆቼ!

ታስሬ ስላልጠየቃችሁኝ ወይም ቤተሰቤን ስላላበረታታችሁልኝ አንዳችም ቅሬታ ወይም ቅያሜ የለኝም::

በማከብረው ድርጅቴ በ«ቅንጅት»ነት ከተማርኩት አንዱ በጣም ጠቃሚና ሰውን ሙሉ የሚያደርግ ነገር ቢኖር ሰውን አለማኩረፍ አለመቀየም ይልቅስ በመነጋገር ማስተማር ወይም መማርን በመሆኑ ቅያሜ የለኝም::

ትዝ ይላችሁ እንደሆነ በምርጫው ሰሞንም ሆነ በምርጫው ማግስት እኮ አብረን እያመሽን አናንተም ቅር ሳይላችሁ እኔም የኔን አቋም ያዙ ሳልል፤እንዲያውም ምን ያህል ለቅንጅት ፍቅር እንዳላችሁና የተገኘውም ድል ብዙዎችን ወደ ነጻነት የሚወስድ እንደሆነ እየነገራችሁኝ ከአንድ ጠርሙስ ጠጥተን ከአንድ መሶብም ቆርሰን ነበር::

ትዝ ይላችሁ እንደሆነ ቅንጅት አዲስ አበባን መረከቡ «ለወደፊት የሞያችን እድገት ትልቅ ተስፋ የምንጥልበት፤ቢያንስ በሙያተኛነት ደረጃ ብቻ የሚመለከተንና አባል ካልሆናችሁ ይህ አይገባችሁም ከመባል ያድነናል» እንባባል ነበር::ምናልባት አሁን ረስታችሁት ከሆነ ለመርሳት ፈልጋችሁ ነውና የረሳችሁት መርሳት ሳይሆን እራስን መካድ ነውና አስታውሱት::በህሊናችሁ አንድ ቦታ ተሸጉጦ አለና አውጡትና መርምሩት::

የቅንጅት መርሃ ግብር ማንም ከእምነቱ ጋር ሆኖ ሌላ አመለካከትና አተያይ ካለው ጋር አይገናኝ አይግጠም አይጠያየቅ አይልም:: የሁሉንም ያመለካከት ልዩነት ያከብራል::ሁሉም የየራሱ እውነት እንዳለውም ይረዳል ግን የትኛው እውነት ነው ፍጹም እውነት ብሎ ይመዝናል ያ ማለት ግን በዚህ ሳቢያ አካኪ ዘራፍ የሚልበት ምክንያት የለውም::ይህም ከቅንጅቴ የተማርኩት ነው::



ከናንተም የተማርኩት ነገር ቢኖር ወዳጅን እንዴት መክዳት እንደሚቻልና ክህደት ሩቅ እንዳልሆነ ስለሆነ እባካችሁ አንኩራረፍ:: ኩርፊያ ያለበሰሉና ያላዋቂዎች ባሕል ነውና!!::

እውነት እውነት እላችኋለሁ

**እኔ ታዘብኳችሁ እንጂ አልተቀየምኳችሁም::**

ውድ የቀድሞ ወዳጆቼ:-

ትዝብትን አትከልክሉኝ ቢያንስ እውነቱን እየነገርኳችሁ ነውና::

በሙያዋና በጠባይዋ የማከብራት ከማንም ጋር ፍቅር እንጂ ጠብን የማታውቀው ቀድምትና ተወዳጇ የጥበብ ሰው አሰለፈች አሽኔ (አሰለፍ) ከማእከላዊ እስከ ቃሊቲ ሳትለየኝ ከጎኔ ቆማለችና ከነበረኝ አክብሮት የበለጠ እንዳከብራት እንድመካባት አድርጎኛል የሚገርመው ከብዙዎቻችሁ የተሸለ ደምወዝ የሚያገኘውና ጥሩ ቦታ የሚሰራው ዮሐንስ፣ ወንድም/ጓደኛነቱን በችግሬ ወቅት ደጋግሞ ያረጋገጠልኝን ጆኒን(ዮሐንስ:ብርሃኑን) አከብረዋለሁ::ከማእከላዊ ጀምሬህ ሳትለየኝ ቤተሰቤንም በማበረታታት ምንግዜም ወንድሜ እንደሆንክ አረጋግጠህልኛል::

ከናንተ ዝቅ ያለ ደምወዝ የምትከፈለውን ኑኑ አሰፋን አትንኩብኝ እግሯ እስከሚቀጥን የጠየቀችኝ ግን ከናንተ ያነሰ ውለታ የሰራሁላት የክፉ ቀኔ ነች::

እናንተም ብትሆኑ አሁንም ክፉ አይንካችሁ፣ምንም ችግር ቢያጋጥማችሁ ቃል ለምድር ለሰማይ ከጎናችሁ እንደምሆን ቅንጣት ታህል አትጠራጠሩ::

**እኔ ታዘብኳችሁ እንጂ አልተቀየምኳችሁም::**

ለአንድነትና ለዴሞክራሲ

ቅንጅት ያስተማረኝ ትልቅ ነገር ቢኖር አለመቀየምን ነው።ባላችሁበት መጥቼ «ታዲያስ» እንዳልላችሁ ምናልባት ብትሸሹኝ የበለጠ ስለምታዘባችሁ ነው ያላደረግሁት።

## ከቃሊቲ መልስ

# ጋዜጣዊ መግለጫ

ሐምሌ 13/99 ከእሥር ከመፈታታችን ቀደም ብሎና ከወጣንም በኋላ ለጥቂት ቀናት እኛን ከሕዝብ ለማጋጨትና ለማስጠላት የመንግሥት መገናኛ ብዙሃንና አንዳንድ ዳረጎት በላዎች ሲያብጠለጥሉን ነበር።አንድም ቃል አልወጣንም፣ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በድርድሩ ላይ ማንኛውም ወገን ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ እንዳይደርግና አንዱ ባንዱ ላይ የጥላቻ ስሜት ከመንዛት እንዲቆጠብ የተደረሰበት ስምምነት ስለነበረ ዝምታው ያንን በማክበር ነው። ቅንጅት ምንግዜም ቃሉን ያከብራል።ይህንንም ግልፅ ለማድረግ ጋዜጣዊ መግለጫ አወጣ፣ ያውም ውሎ አድሮ በጥንቃቄ።

## ሐምሌ 13/1999 ዓ.ም ከእሥር ከተፈቱት

<u>የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር አባላት የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ</u>



የግንቦት 97 ምርጫን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ምስቅልቅል ምክንያት የሰው ሕይወት ጠፍቶአል የብዙ ዜጎች ነጻነት ተገፎአል የድሃ ሃገር ንብረት ወድሞአል፡ በተጨማሪም በቀላሉ ሊሽር የማይችል የሥነ ልቡና ቁስል በማሕበረሰባችን ላይ ደርሷል። ይህንን አጠቃላይ ችግር በአንድ ጊዜ መፍታት ባይቻልም ቀስ በቀስ ከጊዜ ጋር እንደ ማሕበረሰብ እያገገምን ወደፊት እንሄዳለን ብለን እንደ ሃገርና ሕዝብ ማመን የወደፊት ሥራችን መሰረት ነው።

የዚህ ሰፊ አገራዊ ቀውስ ሰለባዎች አንዱ እኛ የቅንጅት አመራሮች ነን። ከ20 ወራት እሥር በኋላ ሐምሌ 13/1999 ዓ.ም ከእስር ተለቀናል። ከእስር እንድንለቀቅ የተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ ሃይሎች ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።ብዙ ኢትዮጵያዊያን በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ በየሃይማኖት ቤታቸው ጸሎት አካሂደዋል።ሌሎችም ከእኛ ጋር ያላቸውን አጋርነት ለፀሃይ ግለትና ለብርድ ሳይበገሩ በተለያየ ቦታ በሕዝባዊ ሰልፎች ገልፀዋል። ለረጂም ቀናት በፆም ምህላ አድርገዋል። የሃገር ሽማግሌዎች ችግሩን በሰላምና በእርቅ ለመፍታት ላይ ታች ብለዋል። በቅድሚያ ለእነኝ .ህ ሁሉ ዜጎቻችን፡ እንዲሁም ኢትጵያውያን ላልሆኑ የመብት ተከራካሪችና የዴሞክራሲ ጠበቆች በአደረጉት ጥረት በእስር እያለን ይሰጡን የነበረውን የሕሊና እረፍት በማስታወስ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ሕይወታቸውን ላጡት ዜጎቻችን ያለንን ከፍተኛ አክብሮት የምንገልጸው እኛም ሆንን ሌሎች ኢትዮጵያዊያን መቼም የማንረሳቸው የዴሞክራሲ ሰማእታት መሆናቸውን በማስታወስ ነው።ለቤተሰቦቻቸውም ፈጣሪ መጽናናትን እንዲሰጣቸው ሁሌም በጸሎታችን አንዘነጋቸውም።

እኛን ከእስር ለማስፈታትም ሆነ በፀብና በእልህ አጣብቂኝ ውስጥ የገባውን የኢትዮጵያን ሰላማዊ የፖለቲካ ሂደት ከገባበት ለማውጣት የተወሰኑ የሃገር ሽማግሌች ቢያንስ ላለፈው አንድ ዓመት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር ይታወቃል። የጥረቱ መሠረታዊ

መንፈስ እኛን ከእስር ማስፈታት ብቻ ሳይሆን ሀዲዱን የለቀቀውን የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ጉዞ ወደ ተገቢው መስመርና አቅጣጫ መመለስ ነው።

ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ሽማግሌቹ አስፈላጊ ነው ብለው ያመኑበትንና እኛም ከልባችን የተቀበልነውን የአገራችን ባሕል በሆነው ይቅርታ መባባል መንፈስ ችግሩን ለመፍታት ተስማምተናል።

ያለፈውን በሚመለከት ጥፋት ያጠፉትን ሃይሎች ሁሉ ይቅር በማለት፡በዚህ ሂደት የተጎዱትን ከጉዳታቸው የሚያገግሙበትን መንገድ በመሻት በዋነኛ ነት ደግሞ የወደፊቱን በመመልከት ከእርቁ በኋላ በሚፈጠረው አጠቃላይ ሁኔታ ላይ በማተኮር፡ ሁኔታች ከሁከቱ በፊት ወደነበሩበት መመለስ አስፈላጊ መሆኑን ተማምነናል።

ጥረቱም በይበልጥ በዚህ ሁኔታና ከዚያም በኋላ በተፈጠረው የተበከለ መንፈስ ምክንያት ሁላችንም የምንወዳት ሃገራችን የበለጠና በኋላ ልትወጣ ከማትችልበት ማጥ ውስጥ እንዳትገባ ለመከላከል ያለመ ነው።ከጅምሩም እኛ የቅንጅት አመራሮች በተቻለን መጠን በጥላቻ ባለመመራትና ተጎዳን የምንለውን ሁሉ በትእግስት በመያዝ እስከመጨረሻው ተጉዘናል።

ዘላቂ የሆነ የእርቅ መንፈስን ለማስፈን አስፈላጊ ናቸው በተባሉ የተለያዩ ነጥቦች ላይ ከሽማግሌች ጋር ሰፊ ውይይቶችን አድርገናል።በብዙ ነጥቦችም ላይ ተስማምተናል። የደረስንባቸው ስምምነቶችም የእኛና የሽማግሌች ብቻ ሳይሆኑ ጉዳዩ በሚመለከተው ሌላው አካል ዘንድም ስምምነት እንደተደረሰባቸው በሽማግሌች ተገልጾልናል።ምንም እንኳን በመጨረሻው በመንግሥት በኩል ስምምነት ተብሎ የተገለጸው ከዚህ ከሽማግሌች ጋር ከተደረሰው ስምምነት የተለየ ቢሆንም የስምምነቱን እውነተኛ ይዘት ወደፊት እነኚሁ የሃገር ሽማግሌች አስፈላጊ በሆነ ጊዜና በሚመቻቸው ሁኔታ ለሕዝቡ ይገልጹታል ብለን እናምናለን። ስምምነቱ ከተፈጸመም በኋላ በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በሰፊው እየተሰጠ



ያለውን የፕሮፓጋንዳ ምንነት የኢትየጵያ ሕዝብ በቅጡ እንደሚያውቀው በውል እንረዳለን። በዚህም ፕሮፓጋንዳ ምክንያት ቅንጅት በሕዝቡ ዘንድ ያለው ተሰሚነት ቅንጣት ታህል እንኳዋን ዝቅ ይላል ብለን አንገምትም።ይህንንም ከተፈታን በኋላ ሕዝቡ ያሳየን አክብሮትና የሰጠን አስደናቂ ፍቅር አረጋግጦልናል።

ስለዚህም ለተሰነዘረው ፕሮፓጋንዳ አጸፋ መልስ መስጠቱ ሽማግሌችም ሆኑ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲፈጠር የፈለጉትንና እኛም ያመንበትን መንፈስ የበለጠ ከመበከል ውጪ ምንም ፋይዳ የለሌለው መሆኑን ተገንዝበን አልፈነዋል።

ይልቁንም እኛ እንደ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ባለፈው ላይ ከማተኮር ወደፊት ማየትን መርጠናል።ይህም የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ድርጅታችን የተመሰረተበትንና የታገለለትን የኢትዮጵያ ሕዝብም ከልቡ የሚፈልገውንና የሚገባውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በእግሩ ለማቆም የሚደረግ ትግል ነው።እኛ የቅንጅት አመራሮች ለዚህ ትግል ያለንን የማይነቃነቅ ቁርጠኝነት እናረጋግጣለን።የዚህ ሂደት የመጀመርያው እርምጃ በስምምነታችን መሰረትና የሃገር ሽማግሌች ለማስፈጸም ቃል ከገቧቸው ጉዳዮች አንዱና ለአሁኑ ጊዜ ዋና የሆነው ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ በእስር የሚገኙት በሙሉ ከእስር ተፈትተው ማየት የእኛም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ አጀንዳ ስለሆነ ይህንን ጉዳይ የሃገር ሽማግሌዎች በአስቸኳይ እንዲያስፈጽሙ እናሳስባለን። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን በሌሎች አጀንዳዎች ላይ ወደፊት መሄድ አስቸጋሪ መሆኑን እንገነዘባለን።

በመጨረሻም እኛ የቅንጅት አመራሮች ኢትዮጵያችን አሁን ከገባችበት የፖለቲካ አጣብቂኝ ወጥታ አውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲፈጠር የጀመርነውን ትግል እንደምንቀጥል፡ ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሃገራችን መፈጠር፡እኛ ከያዝነው አቋም ጋር ከሚስማሙ ከማናቸውም ሃገራዊ ሃይሎች ጋር በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን።በቀጣይነትም ቅንጅቱ አሁን በሀገራችን

ባለው ሁኔታ ላይ በሰፊው መክሮ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለሕዝቡ ይገልጻል:: ብቻ ነው ያለው::

በቅድሚያ መፈታታችን ዱብ እዳ ነበር:: ማንም ያልጠበቀው::ሽማግሌዎቹ ከቀሩ፤ ድርድሩም ከተቋረጠና ከሽማግሌዎቹ ጋር ክፉና በጎ ተነጋግረን ከተለያየን ከወራት በኋላ በመሃል ላይ መጥተው ዝም ዝም ተብሎ ያለቀ ጉዳይ ነበር::

ያን እለት ሐምሌ 13ቀን 1999 ዓ/ም ድንገት ሃላፊዎች ሽር ጉድ አበዙ የዞናችን በር ያለወትሮው ከውጭ ተቆለፈ:: የተለያየ ወሬ ነበር የምንሰማው::አንዱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ግቢውን ለመጎብኘት ስለመጡ ነው ይላል፣ ሌላው ደሞ የለም የውጭ ሃገር ሰዎች ናቸው ይላል፣ ሌለኛው ደግሞ የቀይ መስቀል አባላት ናቸው ሲል በመጨረሻው ላይ ትልቁ ቡሽ የምንለው፣መጥቶ ዶ/ር ብርሃኑን፣አቶ አባይነህን እኔን ጠራን:: ወዲያው ደሞ ቆዩ ተባለ::ደሞ እንደገና ሁላችሁም ተዘጋጁ ተባልን::ተዘጋጀን::

ተቆልፎ የነበረው በር ተከፈተ፣ ከሌሎችም ዞኖች ሌሎች አባሎቻችን ሲሰባሰቡ አየን::እኛም ወጥተን በአዳራሹ ተቀላቀልን::አሁንም ለምን እንደተሰባሰብን ግልጽ አልሆነልንም::ሁሉም ተጠቃሎ ከገባ በኋላና የሚጠበቁት ሰው ከመጡ በኋላ የተሰበሰብንበት ጉዳይ ለመፈታት እንደሆነ ተነግሮን ወረቀታችን ተሰጠን::

ከእስር እንደተፈታን ተነግሮን ወደየቤታችን እንድንሄድ መመርያ ሲሰጠንና በፕሬዜዳንቱ የተፈረመው የመፈቻ ደብዳቤ ሲሰጠን አብሮ አንድ ያላሰብነው ሁኔታም ተፈጠረ::ሁላችንም ወደየቤታችን የምንሄደው በተዘጋጀልን መኪና መሆኑንና ከቤተሰቦቻችን ጋር ከበር ውጪ እንደማንገናኝ ተነገረን::ሌላው ቀርቶ እቃችንን እንኳን የምናዘጋጅበት ጊዜ አላገኘንም::

ለምን ቤተሰብ ጠርተን አይወስዱንም የሚል ጥያቄ አንስተን አይሆንም መኪና ተዘጋጅቷል በዚያ



ነው የምትሄዱት ተባለ::ሌላው ቢቀር የማያስፈልገን እንደመድሃኒት የመሳሰለ እቃችንን እንኳ እንድንወስድ ጊዜ ይሰጠን ብንልም ነገ መጥታችሁ ትወስዳላችሁ አሁን ግን በቅርብ ያለ እቃችሁን ብቻ ተብለን በጥድፊያ ያገኘነውን ብቻ ነው ይዘን የወጣነው::

ከቤተሰብ ደግሞ የጥቂቶቻችን የመፈታታችንን ወሬ ሰምቶ ኖሮ ቀድሞ መጥቶ ቃሊቲ ወህኒ ቤት በር ላይ ቆሞ ይጠብቃል:: የቅንጅት አባላትና አንዳንድ ወዳጆቻችንም አሉ::ከወህኒ መውጣታችን ሲነገረንና የመፈቻው ደብዳቤ ሲሰጠን ስንወጣ እቃ ስናስር ስንጭን ስንጫን ዝርዝር ወሬ ለመቅረጽ የተዘጋጀው የቴሌቪዥን ካሜራ አጠገባችን እንዳይደርስ በማለታችን ሌላውን ሁኔታ ሳያነሳ ቢቀርም በድብቅ ትንሽ ብጣሽ ወሬ አግኝቷል::

ወደቤታችን የምንሄደው በመንግሥት መኪና ብቻ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በሰፈር በሰፈር ተቀናጅተን በየተመደበው መኪና ገብተን ከግቢው ወጣን::

በር ላይ በተዘመድና ወዳጆች ደጋፊዎቻችን አሉ::ግማሹ ይስቃል ሌላው ያለቅሳል ደስታም ያስለቅሳል የተባለውን እያየን ባጠገባቸው በጨረፍታ እየተያየን ሄድን::በቃሊቲ በር ላይ የነበሩት ወዳጆቻችን መውጣታችንን ሲያዩ ለቤተሰቦቻችን እየደወሉ መጡ ሲሉ ወደ ቃሊቲ መንገድ ጀምረው የነበሩት ወደየቤታቸው ተመለሱ:: አንዳንዶቻችን ግን ቤተሰብን ቀድምን ቤት ደርሰናል::

ስንደርስ ምናልባት በሚል ቤተሰቡ ገሚሱ ወደ ቃሊቲ ቀሪው ቤት ስለነበር ሁሉም ሲደርስ በየመንደሩ ሕዝብ ተሰብስቦ እልልታው ቀልጦ እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ለቤታችሁ ያበቃችሁ የሚለው የደስታ መግለጫ የየአንዳንዱን ግቢ አጣቦት ነበር::ሰላምታ ለመስጠት ወረፋው አላደርስ ብሎ ጊዜ ያስጠብቅ ነበር::ሕብረተሰቡ ለኛ ያለውን ፍቅር አክብሮት ከምርጫው በኋላ ከነበረውየበለጠ ሆኖ አገኘነው::

ገና ግቢውን ሳይገቡ እልልታው በሴቱ ብቻ ሳይወሰን ወንዱም እልል ብሏል።ልክ እንደታቦት እግራችን ላይ እየወደቀ ነበር እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት።ሁሉም «ስለታችን ሞላ ምኞታችን ተሳካ ሕልማችን ደረሰ» ነበር የሚለው።

ይህ ነው ለካ የሕዝብ ፍቅር? እኔ በሙያዬ የህዝብ ፍቅር አይቻለሁ ያሁኑ ግን እጅጉን የበዛና አይቼው የማላውቀው አይነት ነው።ጾታ እድሜ ብሔር ሳይለይ ሁሉም ነው ፍቅርና አክብሮት ያሳየን። ያንን ሳይ ነው ገዢው/ፓርቲ ከመውጣታችን በፊትና ከወጣንም በኋላ ያንን ሁሉ የዘለፋ ፕሮፓጋንዳ ሲያካሂድብን ከርሞ መክሰሩን ያየሁት ከሕዝብ ባገኘነው ፍቅርና አክብሮት ነው። እንደፕሮፓጋንዳው አፈብራሪክ ቢሆን ኖሮ ያገኘን ሰው ሁሉ መንገድ ላይ እንደይሁዳ በድንጋይ ወግሮ ይጨርሰን ነበር።ምናልባት ያ ተፈልጎ እንደሆነ ፕሮፓጋንዳው የተሰራው አልተሳካም።

በማገኞት ነጻ ጊዜ እያንዳንዱ ጋ ስደውል የሚነግረኝ ሕዝቡ አላቋርጥ አለ ነበር።መስተንግዶው ለብቻው ነበር።የሁላችንም ግቢ የበግ ገበያ መስሎ ቤታችን የመጠጥ ማከፋፈያ ሆኖ ነበር።በተናጠል የሚመጣ አለ በቡድን ሆኖ የሚመጣ አለ።

ከታሰርኩበት ጀምሮ በማእከላዊም በቃሊቲም ካልጠየቁኝ ቤተሰቤንም ካልጠየቁት መሃል እንኳን ለቤትህ ያበቃህ ብለው የመጡትም ለምን እንዳልጠየቁኝ ሊያስረዱኝ ሲሞክሩ ገብቶኛልና ተዉት ነው ያልኳቸው። እርግጥ መጥቶ እኔን መጠየቅ ያስፈራል ምክንያቱም ከሥራ መባረርም ሊኖር ይችላል ተብሎ ስለሚፈራ።ቤተሰብም ለመጠየቅ ግንኙነት አለው ስለሚያስኝ።ለቤተሰብ ግን ስልክ ደውሎ እንዴት ናችሁ? የሚያስፈራ አይደለም ግን ያልተለመደ በመሆኑ ትዝ አይልም።መጠየቅ ያለበት የታሰረው ብቻ እንጂ ቤተሰብ መጠየቅ እንዳለበት ብዙዎች አያስቡትም።ቢሆንም የፍርሃትም ልክ አለው።



ደስታቸውን ለመግለጽ የሚመጡት ወዳጆቻችን በአንድ ቀን በአንድ ሳምንት በአንድ ወር አላቆሙም።ከክልል ጨምሮ እየመጡ ደስታቸውን ገልጸውልናል።

ዲያስፖራው፣ኤልፎራው፣ላሜ ቦራው በየተራ በነፍስ በስልክ እንኳን ደስ ያለን ካሉት ሌላ (በኢሜይል ደግሞ የማያውቁን ግን በዓላማ የተሳሰርነው) አበረታተውናል።ይህን የደስታ መግለጫ ያልለገሱን «ሰጋቱራዎች» ብቻ ናቸው፣ እኛም ከጉዳይ አናስገባቸውም አላስገባናቸውምም።

በጣም ሲያሳስበኝ የነበረው ወደመንገድ ስንወጣ ሊያጋጥመን የሚችለው ምን እንደሆነ አለማወቁ ነው።ሰዉ ሰላም ብሎን በቀላሉ ያልፋል ወይስ ልጋብዝ ይላል ወይ ቆሞ ማውራትና ለምን እንዳልጠየቀኝ ሊያስረዳኝ ይሞክራል? ይህ ከሆነ በጣም አስቸጋሪና አድካሚ ከመሆንም ያልፋል።

የመጀመርያውን ወር ነሐሴን ከግማሽ በላይ በቤቴ ቁጭ ብዬ እንግዶቼን ሳስተናግድ ቆየሁና አንድ ቀን ወደ ጥርስ ሃኪም ለመሄድ መኪና ይዤ ወጥቼ ሁኔታውን በጥርስ ህክምን ቦታ አየሁት በጣም አስቸጋሪ ነው።ሰዉ መልካም ምኞትና ስሜቱን ለመግለጽ በጣም ይፈልጋልና ለያንዳንዱ መቆም ሰላምታውንና መልካም ምኞቱን መቀበል ግዴታ ነበር።ከዚያ ወጥቼ ወደ አንበሳ ፋርማሲ መድሃኒት ለመግዛት ከመኪና ወርጄ ልገባ ስል ያልጠበቅሁት የሰው ብዛት ከበበኝ።ባለመኪናዎች ያለምንም ማጋነን መንገድ ላይ በማቆም ስለመጡ ትራፊክ ተዘጋ ትራፊኩም ምክንያቱን ለማየት መጥቶ እሱም የደስታ ተካፋይ ሆነ ስለመኪናዎች አቋቋምና ስለትረፊክ መዘጋት ማንም ምንም አላለም ሁሉም ቅድሚያ ለሰላምታ ነበር ያደረገው።

በመጨረሻም አመስግኜ መንገድ መዘጋቱ ደሞ ሌላ ችግር እንዳያመጣ ብዬ አሳስቄ መድሃኒቱን ገዝቼ ወደቤቴ ስሄድም ሲያዩኝ የመኪና ጡሩምባ እያሰሙ

ሰላም የሚሉኝ የቅንጅትን ምልክት የሚያሳዩኝ ሁሉም ማለት እችላለሁ፣ሁሉም ነበሩ።

ሁኔታው አሁንም ያው ነው።አልተለወጠም ሕዝቡ አመስግኖ አልጠገበም፣ደስታውን ገልጾ አላቡ-ቃም። አሁንም ሲያገኙን አንድ ነገር ለማድረግ ይፈልጋል። ቡና ልንጠጣ ገብተን ከፋዩ ሳይታወቅ ይከፈላል በምግብ ቤትም ይሄው ነው።የትም ቦታ።ይህ ደግሞ ለኔ በጣም ይከብደኛል።አይሆንም ሰዉ ከፍቅሩ የተነሳ ይቅር፣የለም አያስፈልግም፣ የሚባለውን መስማትም አይፈልግም።

ይቀንሳል፣የነበረው ፍቅር በጥላቻ ይለወጣል፣ብለው የጓጉ ሁሉ ኩም ነው ያሉት።በሬዲዮ አሸሙርና ሲያሰኝም በግልጽ አለአግባብ አፍ ሲከፈትብን የታሰበው ውጤት ሳይሆን ያልተጠበቀው ተገኝና ሰዎቹን ይበልጥ የሚያቃጥል የሚያንገበግብ ሁኔታ ሆነ።

ይህን ፍቅር ይህን አክብሮት የሰጠንን ሕዝብ መልሰን መውደድ ማክበር የሚፈልገውን እስኪያገኝ ድረስ ከጎኑ ቆሞ መታገል ብቻ ነው መልሱ ሊሆን የሚችለው።ይህ ደግሞ አማራጭ የማይቀመጥለት የቅንጅት መርሀ ነው።

ቅን አመለካከት ጨርሶ ያልፈጠረባቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም መመኘት ሞት ሆኖ የሚሰማቸው ግለሰቦችና ለክፋት የተጣመሩ ሁሉ፣ቅንጅት ያገኘውን ሕዝባዊ ፍቅር አለመቀዝቀዝ፣አለመቀነስ፣ ባዩ ቁጥር ለማስጠላት ደግሞ ሌላ ቅስቀሳ ሌሊቱን ቁጭ ብለው በማደር ሲጠነስሱ ያድራሉ።ያ ደግሞ የበለጠ ፍቅር ለቅንጅት ሲያስገኝ እርር ድብን በማለት ይታመማሉ።ለራሳቸው ይዋሻሉ። ሰዉ ስለቅንጅት መስማት ጠላ ብለው ለራሳቸው መጽናኛ እራሳቸው የፈጠሩትን ውሸት ለመሰሎቻቸው በማውራት የውሸት ደስታ ላይ ላዩን ይደሰታሉ ውስጣቸው ግን ያራል። በከንቱ ተስፋ፣ በማይገኝ ምኞት፣ይንተከተካሉ።



በቅርቡ አንድ የቀድሞ ወዳጄ ዘመድ ሞቶበት ለቀብር ግቢ ገብርኤል ነበር የሄድኩት። በዚህ ቀብር ላይ ለቅንጅት ክፉ አሳቢ፣ ግንባር ቀደምት ከሚባሉት ሶስት ያህሉ በዚያ ቀብር ላይ ነበሩ።የሟች ሕይወት ታሪክ ሲነበብ በአንድ መደዳ ቆመን ነበር የምናዳምጠው።ንባቡ እንዳለቀ በርካታ ሰው ወደኔ መጥቶ ሰላምታ መለዋወጥና አንዳንድ ጨዋታዎችን ይዘን የመጣንበትን ዋና ጉዳይ ዘነጋነውና ሳንሰናበት ቤተሰብ ወደሃዘኑ ቤት በመሄዱ እኛም በየመኪናችን ሄደን እንሰናበት ተባብለን ሄድን። በዚያም እነዚያም ጉዶች ነበሩ። ወደ ድንኳን ስገባ ለቅሶ ቤት መሆኑ ቀርቶ ወደ ደስታ ቤትነት ሲለወጥ ተሰማኝና የሟች ቤተሰብን ተሰናብቼ ስወጣ ከጉዶቹ አንደኛው ውጪ ከነበሩት ለቀስተኞች ጋር ግጭት ይዘዋል፣ብጠይቅ ሰዉ ለኔ ባሳየው ፍቅር ተናደው ነበርና አጉል አስተያየት ሲሰጡ ተሰምተው ነው ጠብ የተፈጠረው።

መቼም ሰውን ውደደኝ ብሎ ማስገደድ አይቻልም፣ ሰው የወደደውን ደግሞ ጥላ ብሎ መንገርም ያስቸግራል። ሕዝብ እንደዚህ ነው ቅንጅትን ወደደ ሌላውን ጠላ የተጠላው ደግሞ የግድ ካልተወደድኩ እያለ ነው ይህ ግን የሚቻል አይደለም።ለመወደድ የሚያስወድድ ተግባር መፈጸም ያስፈልጋል።ለመጠላት ደግሞ የቅንጅት ጠላት መሆን ይበቃል።

የአመለካከት ልዩነት ስለአለን ብቻ የቅንጅት አባላትና ሌሎች ለምን በጠላትነት ዓይን መተያየት እንዳለብን ሊገባኝ ያልቻለ ጉዳይ ነው።ሁላችንም ልዩነታችንን ይዘን የየራሳችንን የፖለቲካ ፕሮግራም መምራት ብንሞክርና ምርጫውን ግን ለሕዝብ መተው ነው የሚሻለው። ለሃገርም ለሕዝብም፣ለግለሰብም ለቡድንም።

ለግል ጥቅም፣ራስን በተመቻቸ ሁኔታ ለማስቀመጥ፣ ስለሌሎች ደንታ ቢስ በመሆን የሚገኝ ደስታ እውነተኛ ደስታ ሳይሆን ከሚያልፈው ጊዜ ጋር አብሮ የሚያልፍና ዘላቂነት የሌለው ደስታ ነው።የሕዝብ ፍቅር ሳይኖር በግዴታ ብቻ ስልጣንንና መሳርያን

መከታ በማድረግ ለመግዛት ከሚሞክር ሃይል ጋር ተጣምሮ የዛሬን ብቻ ዘላቂነት የሌለውን የደስታ ኑሮ ለመኖር መጣር የማያዋጣ መሆኑን ከጃንሆይ ባለስልጣናትና ደጋፊዎችም ሆነ ከደርግ መማር አልቻልንም፣ ይህ ደሞ ትልቅ በሽታ ነው፣ መድሃኒት የሌለው ራስን የመውደድ በሽታ።

በደርግ ጊዜ ተጠቃሚ ሆነው ደርግ ስልጣን ሲለቅ ገሚሶቹ ወደ ወህኒ ሲወርዱ ክህደትን ያወቁበት ደግሞ አልነበርንም ተገደን ነው መሳርያ ተደግኖብን ነው በማለት ከማንም አስቀድመው ያወደሱትን ስርአት በማውገዝ ታማኝ ለመሆን ያደረጉት ጥረት በጥቂቱም ቢሆን ተሳክቶላቸው አሁንም በዚህኛው ስርአት ውስጥ አሉ።ይህ ስርአትና የስርአቱ ሃላፊዎች ደግሞ ጠንቅቀው ስለሚያውቋቸው እስከጠቀሙና መሳርያ ሆነው እስካገለገሉ ድረስ በሸውራራው እየተቆጣጠረ ይይዟቸዋል።ያቺ ቀን ስትመጣና ተነቅረው ሲተፉ ግን ማረፊያቸው የት እንደሚሆን የሚያውቁት አይመስለኝም።ሕሊናቸው በጊዜያዊ ጥቅም ተሳስሮ በመደናበር ላይ ነውና።

ይህ ስርአት ደሞ እስከማእዜኑ የሚቀጥል መውደቂያ የሌለው የፈጣሪ ሥራ አይደለምና ወቅቱ ሲመጣ ለፍርድ ቀርበው በሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሰብአዊነታቸው ተጠብቆ ላፈረሱት ሰብአዊ መብትና እንዳይመጣ በሩን በዘጉበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ይዳኛሉ ለፍርድ ይቀርባሉ።ማን ያውቃል አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትስ አሳስታችሁኛል፣ በናንተ ምክንያት ሕዝብን በድያለሁ ተጠያቂዎቹ እናንተ ናችሁና ኑ ብሎ ሰብስቦ በፈረዱበት ቦታ እንዲፈረድባቸው ቢያስልፋቸውስ? ማን ያውቃል?



# «ቃሊቲ፤ነብሮ:ሚጢ፤ድመቶቼ

## <u>በቃሊቲ</u>

በማእከላዊ ካለው የወህኒ እስረኞች አያያዝና የፖሊስና የታሳሪ ግንኙነት ሌላ የማይረሳ ነገር ቢኖር አይጦቹ ናቸው።የዚያ ግቢ አይጦች እንዲያው አይጥ ተብለው ብቻ የሚጠሩ አይደሉም።በጣም ትላልቆች፣ በጣም ደፋሮች፣ በጣም ተንኮለኞች ናቸውና እንቱታ ሲያንሳቸው ነው።ከወፈሩ ሰው አይፈሩ ለዓይጦችም የሠራው ማእከላዊ ብቻ ነው።

አንዳንድ ጊዜ በሚፈጽሙት ተንኮላቸው በመገረም ከየት አመጡት ይህን ተንኮል ስንል በዚያ በተለያየ ወንጀል ተይዘው ያሉት ወጣቶች «ተንኮሉንማ ከዚሁ ከጨካኝና ተንኮለኛ ፖሊሶች የቀሰሙት ነው» ይሉናል።በጣም ተንኮለኞች ናቸው መቼ ሰው እንደሚዘናጋ ወይም እንደሚተኛ አለያም እንደማያያቸው ያውቃሉ።የሁሉም ክፍሎች በር አንድ አይነት ቢሆንና በቁጥር የሚለያይ ቢሆንም እነሱ ግን የሚበላ የት እንዳለ፣የማይከደን ስህን ወይም በቀላሉ የሚከፈተው ስህን የት እንደሚገኝ በሚገባ ያውቁታል።

በተለምዶ አይጥን ለመያዝ ባልዲ በግማሹ ሞልቶ በቀላሉ የሚወድቅ ክዳን መሰል ወረቀት ወይም ካርቶን በመክደን ሲረግጡት እንዲገቡ ማድረግ ነው።የማእከላዊ አይጦች ግን ይህን በሚገባ ስለሚያውቁት ጨርሶ በዚህ ዘዴ አይሸነፉም።

አንዳንድ ጎረምሶች መሰረተ ትምህርት የጨረሱ አይጦች ይሏቸዋል።

ወደ መጸዳጃ ቤት በሚኬድበት ሰአት አይጦች ሲሸሹና ወደ ጉድጓቸው ሲገቡ መለስተኛ ሰልፍ ያመስሉታል።በብዛት ስለሆነ የሚንቀሳቀሱት ያስፈራሉ።አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለመጸዳዳት ከተቀመጡ በኋላ ከጉያቸው ተስፈንጥረው ወጥተው ሲሄዱ በጣም

ያስደነግጣሉ።ይህ ያጋጠመው አንድ ጓደኛችን ደንግጦ ሱሪውን ሳይታጠቅ ዘሎ በመውጣት ለጥቂት ቀን መሳቂያ ሆኖ ነበር፣ ለነገሩ ሳይታሰብ የሚያጋጥም እንዲህ አይነት ዱብ እዳ ያስደነግጣል።

ለነዚህ አይጦች ቀንም ሆነ ማታ ከመጠንቀቅና መግቢያ ሊሆን የሚችልን ቦታ ሁሉ ከመዝጋት ሌላ አማራጭ የለውም።የየመኝታ ቤቱ በር ከተዘጋ በኋላ ቀዳዳውን ሁሉ መጠቅጠቅ ያስፈልጋል።

በአይጥ በኩል ቃሊቲም ያው ነው።ማእከላዊ የሚበልጠው በአይጦቹ ትልቅነት ሲሆን ቃሊቲ ደሞ ማእከላዊን የሚበልጠው በብዛት ነው።

በቃሊቲ እንደገባን ምድባችን የቀይ ሽብር ተፋራጆች ግቢ ስለነበር በዚያ አይጥ አልነበረም ማለት ይቻላል።ቢኖርም በመንገድ ተላላፊ እንጂ ነዋሪ የለም።ቃሊቲ ካሉት ዞኖች ሁሉ ትልቁ የህብረት ሱቅ ያለው በዚሁ ግቢ ሲሆን አይጥን ለመከላከል ባጀት ተመድቦላት የምትጠብቅ አንዲት ድመት አለች። ወተትና ምግብ አታስብም ፍለጋም አትዞርም ደምወዝተኛ ናት።ሌሎችም የሷ ልጆችና ያልሆኑም አሉ።በየክፍሉ ድመቶች አሉና አይጦች አካባቢውን አይሞክሩትም። ከዚያ ግቢ ፍቅራችሁ በረታ ብለው ካስወጡን በኋላ በተለያየ ዞን ሲመድቡን የአይጥ መንጋው ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ጀመርን።በዞን 5 የገባን ለት መተኛት በፍጹም አልቻልኩም ነበር። ቀደም ብለው የነበሩት ተለማምደውት ችግሩን ተወጥተውታል፣ይተኛሉ።እኔ መልመድም ተቸገርኩ። ገና ገብተን ጋደም ስንል በጣራው ውስጥ ከድምጹ አኳያ ቁጥሩን ገምት ብባል በአንድ ጊዜ የሚሰማው ድምፅ 50 አይጥ ብዬ እገምታለሁ።ሁኔታው በጣም አስቸጋሪ ስለሆነብኝ ሻለቃ አፈወርቅን (ሻለቃ እንኳን ሲሉት አይወድም) ቀድሞ ከነበርንበት ዞን እንዲለምንልኝ ጠይቄው አንድ ድመት አመጣልኝ ትንሽ ነበረች።ምግብ መብላት ስላልጀመረች የግድ ወተት እየገዛሁ ማሳደግ፣ከኔው ጋር ማስተኛት ካርቶን አዘጋጅቼ አሸዋ አድርጌ በዚያ ላይ ባጠገቤ መተኛትን ሁሉ ሰለጠነች።



ስሟም «ቃሊቲ» ተባለ።ሁሉም የወደፊት ጥቅሟን በማሰብ ይመስለኛል በጣም ይንከባከባት ጀመር።

ከቃሊቲ ተጨማሪ አንድ አሳዳጊዎቹ የሞቱበት ድመትም መጣና በማደጎነት ለኔው ተሰጠኝ።ጋሽ መስፍን ከመልኩ ቀለም የተነሳ ነብሮ ብሎ ሰየመው።ነብሮ እንደቃሊቲ አይደለም ዘገምተኛ ይመስላል።ምግብ ላይ ግን አይታማም።ቃሊቲና ነብሮ በአንድ ላይ ቢያድጉም አንድ አይነት ጠባይ የላቸውም። ቃሊቲ አይጥ አይታ አታልፈውም ውላም ቢሆን ትይዘዋለች። አንዳንድ ቀን ሙሉ ቀን አፍጥጣ ጠብቃ ትይዘዋለች።ነብሮ በዚህ አይታማም። ተይዞለት እንዲሰጠው ነው የሚጠብቀው።በግድ እንዲይዝ ልትሞት ትንሽ የቀራት አይጥም ብትመጣለት ሲጫወትባት ታመልጠውና አከኪ ዘራፍ ማለት ይጀምራል እንጂ ተዘዋውሮ አድኖ መያዝን አልፈጠረበትም።አይጥ ከመያዝ ይልቅ ዛፍ ላይ ያሉትን ወፎች ተንጋጦ በማየት ሲቋምጥ መዋልን ይመርጣል። እንዲያውም አንድ ሁለት ጊዜ እርግብ ይዞ ጉድ አሰኝቶናል።

ጋሽ መስፍን ግን «ሰላማዊው ነብሮ» ነበር የሚለው።ለነብሮ አንድ ሌላ ጠላት መጥቶበት ቃሊቲ ታግዘው ነበር በኋላ ግን ሰለቻትና ተወችው።አዲስ አበባው ዓለም በቃኝ ያደገና ሄርሜላ የሚባል ድመት ነው። አከባቢውን የግሉ ለማድረግና ሁሉንም ለማስገበር ያቀደ ቢሆንም ከነብሮ በቀር ገባሪ አላገኘም።ቃሊቲ የማትሞከር ሆነችበት። ነብሮ ገና ድምጹን ሲሰማ መግቢያ ነው የሚያጣው።አንድ ቀን ሁላችንም ባለንበት ነብሮ በሜዳው ላይ ይንጎማለላል።ወደ በሩ መሄድ ይወዳልና ወደበሩ በመሄድ ላይ ሳለ ድንገት ሄርሜላ ከየት መጣ ሳይባል ከኋለው ከቸች አለበት፣አላወቀምና ሲጎማለል ድንገት ዘወር ቢል ሄርሜላ።ወዲያው ግቢውን ሁሉ ቅዘን በቅዘን አድሮጎት ቤት ውስጥ ገብቶ ተሸሸገ። አንድ በጣም የሚያዝኑለት እስረኛ ገረሟቸው «ከምንጊዜው ቀጠነለት» ያሉት መተረቻ ሆኖ ነበር። ነብሮ በመኖሩ ብቻ ፍርሃቱን የማያውቁ አይጦች ይሸሻሉ በሚል በቁጥር 1 መኝታ ቤት ያሉት ቦታ

አዘጋጅተውለት ደባል ገብቶ ይኖራል ያው ለምግቡ እኔ ጋ መጥቶ በልቶ ወተቱን ጠጥቶ ለመጨዋቻነት ይወጣል ሲመሽ ወደ 1 ቁጥር ይሄዳል::

ሄርሜላ የነብሮን ፍርሃት በሚገባ ስላወቀበት የሚያድርበት ቤት ሁሉ እየገባ ያንደፋድፈው ነበር::በቁጥር 1 ያሉ ታራሚዎች «ነብሮን ከሄርሜላ ለማዳን» የሚል ፕሮጄክት አውጥተው ሄርሜላ በተገኘ በት ይወገር ብለው ወሰኑ:: ሌላው ቡድን ደሞ ነብሮ በቅምጥል እያደገ ተሞላቆ ራሱን መጠበቅ ባለመቻሉ ደካማ ስላሸነፈው ለምን ሄርሜላ ይወቀሳል መተውና ነብሮ ራሱን እንዲጠብቅ እንዲከላከል ማድረግ ይሻላል አሉ:: ያም ሆነ ይህ ነብሮ ከመልኩ ቀለምና ጋሽ መስፍን ከሰጠው ስላማዊ ነብሮነት ባሻገር ምንም የነብር ጠባይ አልነበረውም::

ከነብሮ ጋር ሁሉም የከረረ ፍቅር ቢኖረውም እንዳረጉት ስለሚሆንና ተኝቶ እያለ አቅፈው አንስተው ሌላ ጋ ወስደው ቢያስተኙት በዚያው ፎርም ይተኛ ል::ለዚህም ሰው ሁሉ ከቦታ ቦታ ማዛወር፤አቀማመጡን ወይም አስተኛኘቱን በመለዋወጥ መተከዣ ያደርጉታልና ይወዱታል::አንዳንድ ጊዜ ጅል ሰውስ ይወደድ የለም::በድመቶቹ አመጋገብ የሚቀኑባቸው ነበሩ:: ደሞ ለድመት አድና ለቃቅማ ትብላ እንጂ የምን ማሞላቀቅ ነው ይሉ ነበር::

ቃሊቲ እያደገች ለአከለ መጠን እየደረሰች ሄዳ አሽኮርማሚም አገኘች::ሲላፉና ለመዳራት መንገድ ሲያስተካክሉ ሁሉም እየጠራኝ ጉድ ሊያደርግህ ነው ቀልድ ተፈጠረ::ወዲያው ያዘች::ጸነሰች::

አንድ ቀን ያንኑ የሚያሽኮረምማትን ጎረምሳ ድመት ተከትላ ወጥታ ጠፋች:: ብትጠራ የለችም ሰአቱ ደርሶ ለቆጠራም ስንገባ የለችም በቃ ጠፋች::በሩ ከተዘጋ በኋላ መጥታ ድምጽ ታሰማለች ብዬ ብጠብቅም ምንም የለም::ሌሊቱ አለፈና ጠዋት እንደወትሮው ለቁርስ ትቀሰቅሰኛለች ብዬ ብጠብቅ የለችም::



ጠዋት ዳቦና ሻይ ለማምጣት የሚወጡትን በየዞኑ እንዲያፈላልጉ ለሌሎች እንዲነግሩልኝ አደረግሁ ይህም ሆኖ እስከ ምሳ ሰአት የለችም:: ነብሮ ብቻ ግቢውን ይዞት ምግብ የሚጋራው የለ ብቻውን ተያያዘው::በመጥፋቷ ምንም ለውጥ አላየንበትም::አንዳንድ ታሳሪዎች « አሁን አንተ እያለህ ቃሊቲ ትጥፋ?» ይሉታል::አንዳንዶች እንዲያውም ፊት ነስተውት ነበር እሱ ደንታም አልሰጠው እንጂ::ሄርሜላ በአካባቢው ብቅ ሲል ብቻ ነው ነብሮ የሚጨነቀው እንጂ ሌላ የሚያስጨንቀው ጉዳይ የለውም::

ቃሊቲ የገባችበት አልታወቀም:: ምናልባት በሚል በየዞኑ ያሉት የዞን ታሳሪ አስተዳደሮች ስለሚተዋወቁ በኛ አስተዳደር በኩል መልእክት ተላላፈ::

በየዞኑ ሁሉ እንዲያፈላልጉልኝ መልእክት ላኩ::እንዲያውም ላገኘልኝ ሰው 50 ብር ወሮታ እከፍላለሁ አልኩና አስነገርኩ::ቀኑን ሙሉ ፍንጭ ቢገኝ ብዬ ብጠብቅ ምንም የለም::መሸ::በሩም ተዘጋ::

በማግስቱ ጠዋት የቁርስ ዳቦና ሻይ የሚያመጡ እስረኞች ወሬ አመጡ::ቃሊቲ፣ በቃሊቲ ዞን ሁለት ታግታለች የሚል::አጋቾቹ 50ው ብር የውነት ከሆነ እንላክት አግኝተናታል ብለዋል ተባለ::ተስማማሁና ወዲያው የስምምነት ቃል ላኩ::እኔ ብስማማም አንዳንድ የዞናችን ሰዎች ባለመስማማታቸው ስብሰባ ተደረገና ከአጋቾች ጋር ስምምነት መግባት አሰያስፈልግም: እንኳን መኖሯ ታወቀ እንጂ እናመጣታለን ተባለ::ዞን ሁለት ሃይለኛ ዞን ነው አሁን ውለታ ብናፈርስ ሌላ ጊዜ አንቀው ሊገሏት ይችላሉ ብዬ ስጋቴን በመግለጼ ደህና እንግዲያው 50 ብር ሳይሆን 20 ብር ይከፈልና ሌላ ጊዜ ቢያግቷት ለእስረኞች አስተዳደር እንደምንናገር አስጠንቅቀን እንስጣቸው ተብሎ በዚሁ ተስማማን ቃሊቲም ወዲያው አንገቷ ላይ ገመድ ታስሮ ተሰጠችን::

ተርባ ነበር::ከተለመደው ውጭ ደረቅ እንጀራም በላች::በርበሬም አልተወችም::ይህ ባሕሪዋ ብዙም

አልቆየም ወደነበረበት ተመለሰ::ቃሊቲም ቀደም ሲል ቋጥራ ነበርና ቀኗ ደርሶ ወለደች:: 5 ወልዳ አራት ተረፉ::አሁን ደሞ ለልጆቿ ማሰብ ጀመርኩ::ከሷ ጋር ለአምስት ድመቶች ማሰብ አስቸጋሪ ሆነ::ሁሉም ያግዝ ይተባበር ጀመር::ልጆቿ ከፍ እንዳሉና ምግብ መብላት ሲጀምሩ ለሚፈልጉ ለመስጠት ተወስነ::

ሁለቱን ትልቋ ልጇ ዮዲት ስትወስድ አንዷን ደሞ ሁለተኛዋ ልጄ ማለዳ ወሰደቻት:: አንዷም ድንገት ሞተች:: ቤተሰብ ቀደም ሲልም አሁንም በየተራ እንዳመቸ ለኛ ምግብ ለድመቶች ሳምባና ሌላም ምግብ ያመጣል:: የአይጡ ችግር ስለተነገራቸው የድምትን ጥቅም ተረድተውታል::አንድንድ ቀን ሳምባ እንዳይገባ ይከለከላል ወይም ምግብ ስለሆነ ቅመሱ ይባልና ሳይገባ ይቀራል::አንድ ቀን ገብቶ ሌላ ቀን የሚከለከለው ወጥ መመርያ ባለመኖሩ እያንዳንዱ የምግብ ፈታሽ የራሱን ሕግ ስለሚያወጣ ነው::ይህንኑ ለአለቆች አቤት ስንልም ለድመት ምግብ ሃላፊነት የለብንም ይባላል::

በጣም የሚገርመው ድመትና አሳ ያላቸው ፍቅር ነው:: አንድ ቀን ነጻነት ደምሴ ከእጮኛው ከተላከለት ሰርዲን አንዱን ለቃሊቲና ለነብሮ ቸራቸውና በሌሉበት ከዳቦና ከሌላ ስጋ ጋር ለማደባለቅ ስንከፍተው እንደጉድ እየጮሁ ቃሊቲም ነብሮም ከቸች አሉ::ዞኑ ተቃጠለ:: ሚያው ሚያው ብቻ አልበቃ አላቸውና መዝለል ጀመሩ ዙርያውን እያሽተቱ ጩኸት በጩኸት::ከዚያን እለት ጀምሮ ነው ድመትና አሳ መዋደዳቸውን የተረዳሁት::አሳ በመጣ ቁጥር ጋሽ መስፍን ድርሻውን እየወሰደ ለድመቶች ያከፋፍላል እኔም እንደዚያው::

ነብሮ በአደባባይ ባዶ ዳቦ አልበላም ቢልም ዞን 1 ቁጥር ቤት ከገባና በር ከተዘጋ እራት ሲበሉ ዳቦውንም እንጀራውንም ይጠርጋል::ቃሊቲ ግን አታደርገውም:: ነብሮ አንዳንድ ጊዜ ለማስመሰል ከቃሊቲ ጋር የመዳራት ሁኔታ ያሳያል እንጂ ለተቃራኒ ጾታ እጅግም ነው: ያወቀለት የለም እንጂ ችግር ሳይኖርበት አይቀርም::



ቃሊቲ እንደገና አርግዛ ወለደች::አሁንም አራት ወለደች ሶስቱ አደጉላት::አንድ ቀርታ ሁለቱ እንዲስጡ ሆኖ አንዱን ለአቶ ገብረጻድቅ ቤተሰብ ሌላዋን ደሞ ለአቶ ስለሺ አንዳርጌ ቤተሰብ ተሰጥታ አንደኛዋ ለግቢው ሆነች::የሁለቱም ቤተሰብ ድመቶቹን ከኛ ጋ ወስደው ሊወጡ ሲሉ አይወጠም ተብሎ ተወሰደባቸው:: በጣም የሚገርም ነው:: ቀደም ብለን ይህንኑ በመፍራት ለሃላፊዎች ነግረን ችግር የለም ተብለን ነው የተነጠቅነው:: በሚቀጥለው ሳምንት ነው መነጠቃቸውን የሰማነውና አቤቱታ አቀረብን ለጊዜው አይደረግም ይጣራል ተባልንና ታለፈ:: በተደጋጋሚ መውጣት አይችሉም ከተባለ ይመለሱልኝ ብዬ ብጠይቅ ማን እንደወሰዳቸው እያጣራን ነው ተባለ:: ቆይቼ ነገሩን ባነሳውም መልስ አላገኘሁም እንዲያውም «አሁን ለድመት ጊዜ አጥፍተን ምርመራ ልናካሂድ ነው?» የሚል የለበጣ መልስ ተሰጠኝ::

የተከናወነው ህገወጥ ዘረፋ ነው:: የታሳሪዎቹን ንብረት አለምንም መመርያ ዘረፋ::ቢጠይቁን የምንሰጣቸውን ለምን በጉልበት መውሰድን እንደመረጡ አልገባኝም:: ማን አለብኝ የማለት ይመስለኛል::

አዲሷ የቃሊቲ ልጅ ሚጢ ተብላ የሁሉም ንብረት ሆነች::በተለይ ደ/ር ብርሃኑ ልዩ እንክብካቤ ነበር የሚያደርግላት::ይጨነቅላታል::በዚህም ለነብሮ ጋሽ መስፍን፡ ለሚጢ ደ/ር ብርሃኑ ለቃሊቲ እኔ:የምግብ ሃለፊዎች ሆንን::ሌላው ጣጣ ግን ከኔ ላይ አልወረደም::

ሚጢ እየደገች ሄዳ ያለእድሜዋ ወለደች 5:: አምስቱም ከአንድ ሳምንት እድሜ አላለፉም ሞቱ:: ገና ተጫውታ ሳትጠግብ ወልዳ ልጆቿን መጫወቻ አድርጋ ገደለቻቸው::ወዲያው ደሞ ቃሊቲ ለሶስተኛ ጊዜ አረገዘችና አንድ የአይን ችግር ያለበት ሰው ረገጣትና ታማ ምግብ አልበላ ብላ ብዙ ቀን ታማ አምፒሲሊንም ቢሰጣት ታማ እያለች ጠፋች::ብትፈለግ ብትፈለግ የለችም::አሁን የጠፋቸው አንድ ቦታ ታማ ወድቃ ሊሆን ይችላል ተብሎ በየአጋጣሚው የሚወጣ ሁሉ በየጥሻው ቢያፈላልግም አልተገኘችም::ከአንድ ሳምንት

በኋላ በውጪው መጸዳጃ በኩል ጠረን ተሰምቶ ሲፈለግ ቃሊቲ ሞታ ተገኘች:: በጣም አዘንኩ::ዘመድ የሞተኝ ያህል ነው የተሰማኝ::ለቀልድ ሳይሆን በቁም ነገር ሃዘናቸውን የገጹልኝ ነበሩ::

ነብሮና ሚጢ ግቢውን ያዙት::ሚጢ በአይጥ አደን በኩል እንደናቷ ነች አያመልጣትም:: እሷንም እየተዋሰ ይወስዷታል::እንዲህ እንዲህ እያልን ድመቶችም አርብተን አይጥም ተከላክለን እስሩንም ታስረን:በቃሊቲ ከረምን::በመጨረሻው ቃሊቲን ለቀን ስንወጣ ድመቶቼን ይገፍ ለመውጣት ብፈልግም ሳይቻል ቀረ:: አሁንም በሰው አስጠይቃለሁ ደህና ናቸው አሉ:: እነሱም ችግሩን ያወቁት ይመስላል ያገኙትን እየበሉ ጠባያቸውን አሳምረው አገልግሎት እየሰጡ ኑሮ ቀጥለዋል::ፎቶግራፋቸው እንኳን እንዳይኖረኝ ቃሊቲ እስር ቤት ካሜራ አይገባም::እስቲ አሁንም ተስፋ ሳልቆርጥ እየሞከርኩ ነው::

## መደምደሚያ

በመጨረሻም በብሔራዊ ሎተሪ አዳራሽ በተገኘ ንበት ዕለት ካደረግሁት ንግግር በአጭሩ ላስነብባችሁና እንሰነባበት::

ወገኖቼ

በቅድሚያ እንኩዋን ደህና መጣችሁ እላለሁ

ወደ ፕሮገራማችን ለመግበታ እንድንችል ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት በሃገራችን መምጣት ሲሉ የማይተካ ውድ ሕይወታቸውን ላሰለፉት ሰማዕታት የአንድ ደቂቃ የሕሊና ጸሎት በማድረግ አርበኞቻችንን እንድናስታውስ እጠይቃለሁ::

አመሰግናለሁ::



ውድ ወገኖች

አሁን አዲስ ምዕራፍ ለመክፈት ተነስተናል::አዲሱ ምራፍ ደሞ በአዲስ መንገድ ወደ ዴሞክራሲና ወደ ሰብአዊ መብት መከበር ያመራናል::ይህን ማድረግ የምንችለው ደሞ በአንድ ላይ ቆመን በአንድነት ስናስብ ነው እንጂ በመነጣጠልና በመለያየት አይደለምና አብረን ለመቆም እንዘጋጅ::

ሃገራችን ድሆች ከሚባሉት ሃገሮች ዝቅ ባለው መስመር ላይ የምትገኝ ናት፤ይህ ግን ሊያሳፍረንና ሊያሸማቅቀን አይገባም ማፈርና መሸማቀቅ ያለብን ሃገራችንን ካለችበት የችግር ማጥ ለማውጣት እንደዜጋ ማድረግ የሚገባንን ስንረሳ ወይም ስንሸሽ ብቻ ነው::ሁሉም ሃገሮች በልጽገው አልጀመሩም::ወደ ብልጽግና ለመሄድ ግን ቆርጠው በመነሳትና የሚያስተዳድራቸው መንግሥታቸውም ሕዝብ የሚለውን የሚሰማ ከሕዝብ ጋር የሚመካከር በሃገርና በሕዝብ አንድነት የሚያምን ሕዝብን ለማስተዳደር እንጂ ለመግዛት ያልቆመ፤ዴሞክራሲያዊና የሕዝቡን ሰብአዊ መብት ያከበረ ተጠያቂነትን የማይፈራ መንግሥት ስለነበራቸው አደጉ በለጸጉ::እኛም የሚያስፈልገን ያ ነው::አሁንም ለማምጣት የተነሳነው ያንን ነው::

የምንፈልገውን ነገር ቁጭ ብለን በማውራትና በማማረር ማግኘት አንችልም:: መጠየቅ፤ማስፈጸም፤ ለምን ማለት፤ ካልሆነም እምቢ ስንባል፤ እኛም እምቢ ማለት መቻል አለብን:: ያንን እስካልለመድን ድረስ የምንፈልገውን የሚሰጠን አናገኝም::

ከፍርሃታችን መላቀቅ አለብን::መሪዎቻችንን መፍራት ማቆም አለብን መፍራት ያለብን እነሱም መፍራት ያለባቸው ሕግና ደንብን ከዚያም አልፎ ሕዝብን ነው የተገላቢጦሽ አድርገን ሕዝብ ፈሪ መንግሥት አስፈራሪ እንዲሆን መፍቀድ የለብንም::የኛ ጠላታችን እስከዛሬ ቀፍድዶ ይዞ ተገዢዎች ያደረገን ፍርሃታችን ነው::ጫንቃችን ብዙ መሸከም በመልመዱ

ነው::አሁን አሁንማ ከአቅማችን በላይ የሆነውን ሊያሸክሙን ሲከጅላቸውም አንችልም ከማለት ይልቅ የኛ የሸክም አቅም አልበቃ ሲለን ጉልበት ተበድረን መሸከምን እየመረጥን ነው::

ፍርሃት የትም አያደርሰንም::እኛ ግን ለፍርሃታችን ገደብ እያጣንለት ነው::አሁን አሁንማ ጎረቤቶቻችንን እንፈራለን፤ቤተሰባችንን እንፈራለን፤ቀን እንፈራለን ማታ እንፈራልን እራሳችንንም መፍራት ጀምረናል::ጥላችን ከኋላ ሲሆን ፊታችንን አዙረን መሄድ ጀምረናል ከፍርሃታችን የተነሳ::መሪዎቻችን ደሞ በፊራን ቁጥር ይበልጥ እንድንፈራ ያደርጉናል::እነሱም እኮ የኛው ሰዎች ናቸው፤እነሱም እኮ ፈሪዎች ነበሩ ብቻ እኛ ከነሱ የባሰን ፈሪዎች መሆናችንን አይተው ሲያረጋግጡ እነሱ ጀግኖች ሆኑ:: የኛ ፍርሃት አጀገናቸው::የነሱ መጀገን ደሞ እኛን የፈሪ ፈሪ አደረገን::ይህ ፍርሃት መብቃት አለበት::ማስፈራራቱ የሚቆመው እኛ መፍራት ስናቆም ነው::ገዢነቱ በቅቶ አስተዳዳሪነት ቦታውን መረከብ አለበት ያን ማድረግ የምንችለው ደሞ እኛ ነንና ከፍርሃት ጓዳችን ወጥተን ሕገመንግሥቱ በሚፈቅድልን መሰረት መብታችንን እናስከብር::በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ለማምጣት እንጣር:: ወቅቱ አሁን ነው::ማንም ምንም ቢለን ሰላማዊ መንገድ ይዘናልና የሚጥለን አይኖርም::መሪዎቻችንም እኛም ለሕገመንግሥቱ ተገዢ ሆነን ይህን ከፊታችን ያለውን ምርጫ ለነጻነት ለዴሞክራሲ ለሰብአዊ መብት ተግባራዊ ማድረጊያነት ለተጠያቂነት እውነታ እንጠቀምበት::

ሕዝብ የበላይ ነው ብለን እናምናለን::ሕዝብ ደሞ የበላይነቱን ማወቅ አለበት::ያንን ካወቀ ፍርሃት አይጠጋውም::ምርጫ የሕዝብ መብት ነው::በምርጫ ሥልጣን ይያዛል ሥልጣን ይለቀቃል::ከእንግዲህ በመሣርያ ወደሥልጣን መውጣት በሃገራችን ማብቃት አለበት::በሰለጠነ ፖለቲካ እየተመራን ሰላማዊ ለውጥ ለማምጣት ተነስተናልና አብራችሁን ቁሙ::

ወገኖቼ



የግድ እኛን ምረጡ ማለት ዴሞክራሲያዊ አካሄድ አይደለምና ያንን አናደርግም አንልምም:: እኛ የምንለው በፍርሃት ማንንም አትምረጡ፤ይጠቅመናል ያገለግለናል ይመራናል ለሃገራችን እድገት ለሕዝባችን ብልጽግና ያመጣልናል ብላችሁ ያመናችሁትን ብቻ ምረጡ ነው የምንለው::

መምረጥና መመረጥ በሕገ መንግሥቱ ላይ የሰፈረ መብት ነው::ሰላማዊ ምርጫ ማካሄድ በሕገመንግሥቱ ላይ ያለ መብት ነው::ሰላማዊ ስንል በሰለጠነ ፖለቲካ ያለጦር መሣርያ ያለ ጉልበት የሚከናወን ዘመናዊ ፖለቲካ ማለታችን ነው::እኛ ያለን ጉልበት የሕዝብ ፍቅር ነው ብለን፤የሕዝብ አመኔታ ነው ብለን፤እናምናለን ሁሉም መከተል ያለበት ይህን እውነታ ነው::ከዚህ ሲወጣ ብቻ ነው ሕገመንግሥቱን ማፍረስ የሚመጣው::

ክቡራትና ክቡራን

ሃገራችን እየሸሹ የሚጠፉባት ሃገር ከመሆን በፍቅርና በመታማመን የምንሰባሰብባት ልትሆን ይገባል::የወጣው የሰው ሃይልና እውቀት ውጪ ያለው የወገን ገንዘብ ወደሃገር ገብቶ ያለአንዳች መጠራጠርና መፍራት ባስተማማኝ ሁኔታ ለሃገርና ለወገን መዋል አለበት::ያንን ለማድረግ ነው የተነሳነው::ኢትዮጵያችንን ስንጠራ ደረታችን ነፍተን ሳንሸማቀቅ ኮርተን አንገታችንን ቀና አድርገን የምንሔድበትን ሁኔታ ማስተንንከልና ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን::የሚያቅተን ነገር የለም:: አብረን ለሃገር ልማት ዕድገት ብልጽግና አንድነት እንጣር::በመበታተን በመከፋፈል የምናገኘው ቢኖር ጥፋት ፤ውድቀት፤ውድመት ብቻ ነው::አንድ ላይ ቆመን በአንድነት እያሰብን ሳንከፋፈል በመከባበርና በማቻቻል ለልማት ብልጽግና ዕድገት እንነሳ::ዛሬ የምንጥለው የዴሞክራሲ የሰብአዊ መብት የተጠያቂነት መሰረት ነገ የሚተካን ትውልድ ተደላድሎ የሚኖርበት ይሆናል::

በጊዜያዊ ጥቅም፤በመታለል፤መብትን ጠቅልሎ ጥሎ ለሆድ ማደር፤ለእኔነት መገዛት፤ማብቃት አለበት።በዴሞክራሲ በሰብአዊ መብት በተጠያቂነት ተጠቃሚ የሚሆነው መላው ሕዝብ እንጂ ጥቂት የተመቻቸው አይፈጠሩም።ትግላችን ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ነው።

ምናልባት አንዳንድ በጊዜያዊ ጥቅም የበለጠ እንጠቀማለን የሚሉ ይኖራሉ፤ አሉ።ትግላችን እነሱንም ከዚህ አስተሳሰባቸው አውጥተን ወደሰበአዊነታቸው እንዲመለሱና እንደሰው ማሰብ እንዲጀምሩ ለማድረግ ነው።በዚህ ከማንም ጋር መጣላት የለብንም። እያንዳንዳችን በምርጫችን መጓዝ መብታችን ነው።ጥሩ የማይስማማው መጥፎን መያዝም መብቱ ነውና።እኛ ግን ሕዝብ ጥሩውን ሊይዝ ይገባል ለዚያ መታገል አለብን ብለን ነው የተነሳነውና አብረን ለጥሩ እንቁም።

አመሰግናለሁ።



የቅንጅት የድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ አባላት የሚያኮሩ፤ጠንካሮች፤ከዓላማቸው ዝንፍ የማይሉ አቋማቸው «ለኢትዮጵያ ሃገራችን ለኢትዮጵያዊ ወገናችን» በሚል መርህ ላይ የተተከለ በመሆኑ ቅንጅትንም የሚመለከቱትና የሚያምኑበትም ሁኔታ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው።

ካናዳ ከዳር እስከ ዳር፤ ጥንካሬ፤ የሃገር ፍቅር፤የዓላማ ጽናት፤ብሩህ ራዕይ፤የሚታይባቸው የቅንጅት ደጋፊዎች ያሉበት ሃገር ነው።ሴት ወንዱ፤ትንሽ ትልቁ፤ሁሉም በቅንጅት ላይ የመጣ በዓይናችን የመጣ የሚሉት ፈሊጥ አላቸው። ሲያስቀኑ!! አመራሩ ዴሞክራሲን፤ሰብአዊ መብትን፤ተጠያቂነትን ካሉበት አካባቢ በመማርና የቅንጅትንም መርህ በመቀበል ለተግባራዊነቱ የሚያሳት ታማኝነት አባላቱ በአንድ ረድፍ እንዲሰለፉ አድርጓል።

በካናዳ ቶሮንቶ የዮርክ ዩኒቨርሲቲ የቴያትር ዲፓርትመንት ከቅንጅት ጋር ከባድ ፍቅር ያለው ነው።አንድ ቀን ለቅንጅት ሰጥቶ ተማሪዎቹና የዮርክ አባላት ስለቅንጅት እንዲሰሙ እንዲረዱ ሲያደርግ አንድ ምሽት ደግሞ ለካናዳ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ቢሮ የሚውል የድጋፍ ማሰባሰቢያ እራት አዘጋጅተው በእራቱ ላይ ከፍተኛ ተደማጭነት ያላቸው ካናዳውያን እንዲገኙ በማድረግ እውነታውን አሳውቀዋል።ከኛ ይበልጥ ቅንጅት ሆነው፤ከኛ ልቀው ስለቅንጅት አስረጂና ጠበቃ ሆነው ያመሹትን ፕሮፌሰር ዶን ሩብንና ባለቤታቸውን አይቼ ንግግራቸውን ሰምቼ ወዳጅ ወዳጁ ለሚያደርገው ሕዝባዊ ወገናዊነት አብሮት መቆም ያለበት መሆኑን አሳይተውኛል።

በካናዳ ሰፊ ፕሮግረም ነበር የተዘረጋውና ሰፊ ጊዜ ወስዷል።በዚህ ሰፊ ጊዜ ወቅት ደሞ ሠፊ ልምድና ዕውቀት ከያንዳንዱ አባል አግኝቻለሁና ምስጋናዬ የላቀ ነው።

የካናዳ ተልእኮዬን ከመጨረሴ ቀደም ብሎ በቅንጅት መሃል የተፈጠረውን ችግር ስሰማ ማመን ነበር ያቃተኝ።ቃሊቲ በነበርንበት ወቅት የቀድሞው መኢአድ አባላት ስለ ዶ/ር ታዬ ሲነሳ ያንገሸግሻቸው ነበር።እንዲያውም ቁርሾ አለን ሲሉ «የማያስፈልገውን» የምንልም ነበርን።እነ አባይነህ ሻለቃ ጌታቸውና እነ ማሙሸት አማረ ከመኢአድ ካላወጡ አልሰራም ማለቱን እያነሱ በቁጭት ነበር የሚናገሩትና እንዴት አሁን ከኢንጅነር ኃይሉ ጋር እጅና ጓንት ሆኑ? ብዬ ገርሞኛል።

ካናዳን ለቅቄ የቅንጅትን ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ አመራር አባላትና አባላቱን እንበርታ ብዬ ልጄን አዳምንና ፍቅረኛውን ሰብለን ቶሎ ዳግም አያት አድርጉኝ በማለት ተሰናብቼ ወደ ሎስ አንጀለስ ሌላዋን ልጄን ጸደይ ደበበን ለማየት ሄድኩ።ኤርፖርት የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ አባላትና ልጄ ጸደይ ደበበ

ተቀበሉኝ::ፀደይ ገና ስታየኝ ለቅሶ ጀመራትና እኔንም አስነባችኝ::የሎስ አንጅለስ ኮሚቴ መምጣትህ ካልቀረ ብለው ከድጋፍ ሰጪ አባላትና ደጋፊዎቻችን ጋር ለማስተዋወቅ ሲሉ ፕሮግራም ይዘዋል እኔ ደሞ ከልጄና ከቤተሰቦቻችን ጋር ትንሽ መቆየቴ ስለማይቀር ፕሮግራሙን ተቀብያለሁ::

ውድ የቅንጅት ደጋፊዎች!

ወደ ዝርዝር ጉዳይ ልግባና መነሳት ያለበትን ዋና ዋና ጉዳይ ላንሳ፤ይህን ጉዳይ የማነሳው እንደላእላይ ምክር ቤት አባልነቴ እንደ ሕዝብ ግንኙነትም በስብሰባዎቻችን ላይ የተካሄደውንዕውነታ እንጂ በተባራሪ የሰማሁትን አሉባልታ ወይንም የስሚ ስሚ እንዳልሆነ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ::

እያንዳንዳችን ኢትዮጵያን እንወዳለን ለዚህች ሃገራችንም ፍቅር አለን::ቅንጅት ነን ስንልም የሰላማዊ ትግል ብቸኛና አማራጭ የሌለው ምርኩዛችን መሆኑን አምነን ነው::በሕግ ፍጹም የበላይነት በሰብአዊ መብቶች እና በዴሞክራሲ ላይ ተመስርተን ነው::የወገን መብት መረገጥ የዴሞክራሲያዊ ድምጽ መታፈን ስለሚያንገበግበን ነው የመከራ ቀኖች አልፈው በሰላምና በብልጽግና እንዲተኩ ነው::ለዘመናት በላያችን የተጫነው አምባገነንነት ስለሰለቸንና ስብእናችንን ሁሉ ገፎ የቁም ሙቶች ስላደረገን ነው::ቀድሞ የነበረው አጥፍተህ ጥፋ አጉል ባህል ተወግዶ የብሩህ ዘመን ብርሃን ለማየት ነው የኛም ሆነ፤ ቅንጅት ያልን ኢትዮጵያዊያን ምኞትና ራእይ::

አዲስ ሃሳብ ለመስማት አዲስ ጠቃሚ መንገድ ለማየት ፈቃደኛነት የሌለን በጭፍን ድሮ የያዝነውን መንገድ ብቻ እንከተል በማለት የትም አይደረስም:: ዘመን እየተለወጠ ሲሄድ አመለካከትም የግድ ይለወጣል::ዕድገት ነዋ::የሌሎችን ሃሳብ ለመስማት ፈቃደኛ ካልሆንን እኛንም የሚሰማን አናገኝም::ቀድሞ የቀረውን ልሹም ልሻር፤ከኔ በላይ ላሳር አሁን ዘመንን ሕግ አሽረን አምጥተን በሕዝብ ላይ እንጫን ለማለት የቅንጅትም ሆነ የእባላቱ ፍላጎት አይደለም:: አሁን እየተደረገ ያለው ያ ነውና ከመሠረቱ ልጀምር

በመጀመርያው የላእላይ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ከቀረቡት አጀንዳዎች አሁን እንደምክንያት እየቀረበ ያለው የላእላይ ምክር ቤት አለመሟላት ጉዳይ አንዱ ነበር::ም/ተቀ/ሊቀ መንበር ብርቱካን ሚደቅሳ አጀንዳውን ሲያቀርቡት

« ሳይታሰሩ የቆዩትን የላእላይ ምክር ቤት አባላት አካተን ብንሰበሰብ ምን ችግር አለው?» በማለት ነበር፤ ለዚህም በቅድሚያ ከሊቀመንበራችን ከኢንጅነር ኃይሉ የተሰጠው ምላሽ፤«የማንን ምንነት ባላወቅንበት ሁኔታ ማንንም አሰባስበን እቅዳችንን አሳልፈን



መስጠት ይሆናል» በማለታቸው ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴም ይህንኑ በመደገፍ «ሳይጣራ ማካተቱ ችግር ሊኖረው ስለሚችል ጥንቃቄ ያስፈልጋል» በሚል ድጋፍ በማድረጋቸውና አንዳንድ አባላትም ሁኔታው እስኪጣራ ይቆዩ የሚለውን በመደገፋቸው ሳይካተቱ የቆዩት በዚህ መልኩ ብቻ ነው:: አሁን እውነትን ትቶ አዲስ ታሪክ መፍጠሩ የስብሰባው ቀለ ጉባኤ ሲታይ ማፈር ይመጣልና እውነቱን ይዘን መጓዙ ነው ለሁላችንም የሚጠቅመው:: በዚያው እለት ይህንን የሚያጣራ ኮሚቴ ተሰይሞ ስራውን እንዲሰራ በላእላይ ምክር ቡቱ ሲወሰን፤«እስኪጣራ ግን ቁጭ ብለን አንጠብቅም አጣዳፊ የሆነ ሥራ ስላለን ያንን መቀጠል አለብን» ተብሎ ስብሰባው ሲቀጥል ኢንጅነር ኃይሉ በሥራ አስፈጻሚው ስብሰባ የታቀደውን አካሄድ እራሳቸውም ያመኑበትን ለቤቱ አቀረቡ ይህም

1 «መንግስት እኛ ጋዜጣዊ መግለጫም እንዳንሰጥ ከአባላትና ደጋፊዎቻችን ጋር እንዳንገናኝ እያደረገ ስለሆነ በአስቸካይ ወደ ተለያዩ ክፍለ አለማት በመሄድ ከደጋፊዎቻችን ጋር ስብሰባዎች ማድረግ አለብን

2 ውጪ በምናካሂደው ስብሰባ ላይ በመመስረት የውጭ መገናኛ ብዙሃን ቅንጅት ምን አቀደ? ምን እያደረገ ነው? ለሚለው ጥያቄ በሃገር ውስጥ ያሉ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን ስለሚያዳምጡ ምን እያደረግን እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳልና በአስቸካይ ጉዞው እንዲደረግ ላእላይ ምክር ቤቱ » ይወስን የሚል ነበር::

በዚህ ጉዳይ ላይ በርካታ ሰአት የፈጀ ውይይት ተደርጎ በሊቀ መንበራችን የተነሳው ነጥብ አሳማኝና ትክክልም በመሆኑ ከዚህ ቁጭ ብሎ ፍቃድ በመጠበቅ መንግስትም ዛሬ ነገ እያለ ጊዜ በማጥፋት ከአባሎቻችንና ከደጋፊዎቻችን ሊያለያየን ስለሚጥር በቀረበው ሃሳብ ላይ መወሰኑ አማራጭ የሌለው ሆኖ ተወሰነ::

በእለቱ ስብሰባው ሲጠናቀቅም ኢንጅነር ኃይሉ «በሚቀጥሉት ስብሰባዎች የህክምና ቀጠሮ ስላለኝና ያንንም መከታተል ስለአለብኝ፤እናንተ እየተሰበሰባችሁ የምታሳልፉትን ውሳኔ እቀበላለሁ፤ ሆኖም እንዳውቀው ብታደርጉ የተቀላጠፈ አካሄድ ስለሚሆን እነማን ያሳውቁ የሚለውን ወስነን የዛሬው ስብሰባ ያበቃል» በማለታቸው ጉዳዩ ልክ ባይሆንም በጤንነት ምክንያት የተነሳ ነውና ይሁን በሚል

1. ተ/ም/ሊቀ መንበር ብርቱካን
2. ጸሃፊያችን ሙሉነህ ኢዮኤል
3. ዶ/ር ኃይሉ አርአያ

4. ስለሺ ጠና በየምሽቱ የስብሰባውን ውጤት እንዲያሳውቁ ተወስኖ የእለቱ ስብሰባ ተጠናቀቀ።

እስከዚህ ድረስ የላእላይ ምክር ቤት መሟላት አለመሟላት ጨርሶ አልተነሳም።ደግሞም ሊሟላ የሚችልበት መንገድም የለም፤ ምክንያቱም

- ገሚሱ ከሃገር ወጥቷል
- ሌላው ከሌላ ፓርቲ ጋር ግንባር ፈጥሮ በመንቀሳቀስ ላይ ነው
- ተራፊው ከእንግዲህ በምንም መልኩ ስሜ ከቅንጅት ጋር እንዲነሳ ስለማልፈልግ አትድረሱብኝ ብሎ ወስኗል። እነዚህ በአንድነትሲደመሩ ከእስር የተፈታነው 22 የላእላይ ምክር ቤት አባላት አብላጫ እንሆናለን።ይህም ታምኖበት ነው ወደ ስብሰባ የገባነው፡ይህ ታምኖበት ነው ያልታሰሩት ተጣርተው ከኛ ጋር ይቀላቀሉ የተባለው።

በዚህ ሁኔታ ስብሰባው ለበርካታ ቀናት እየተካሄደ ውጤቱም በየምሽቱ ለሊቀመንበራችን እየደረሰና እሳቸውም እየተስማሙበት ቀጠለ።በስተመጨረሻው ላይ(ቆይቶ ግልፅ እንደወጣው) ከዋሽንግተን በተላከ መልእክት ሳቢያ ችግር ይሰማ ጀመር።

ሁለቱም ኮሚቴዎች እንዲፈርሱ የሚለው ደብዳቤ በሊቀመንበራችን ከተላለፈና አንደኛው መፍረሱን በጸጋ ሲቀበል አንደኛው ግን በጭራሽ የመፍረሱ ነገር እኔን አይመለከተኝም በሚል አቋም በመያዙና ከዋሽንግተንም በሻለቃዎቹ በዮሴፍና አድማሱ በዶክተሮቹ በዘብህና ታዬ ለሊቀመንበራችን የተላከ መልእክት ነገር ማደፍረስ ጀመረ።በየትኛውም የቡድን አወቃቀር ላይ ስምምነት የነበራቸው ኢንጅነር መልእክት ከደረሳቸው በኋላ የአሜሪካ ልኡክ አባላት ይቀየር የሚል ሃሳብ አመጡ።የእለቱን ውሳኔ ይዞ የሄደው ቡድንም ይህ እንደማይሆንና ውሳኔው የላእላይ ምክር ቤቱ እንደሆነ ቢነገራቸውም በፍጹም በማለት «ጉዳዩ ለላእላይ ምክር ቤቱ በድጋሚ ይቅረብልኝ እንዲያውም በነገው ስብሰባ መጥቼ አስረዳለሁ» በሚል ከኮሚነው ጋር ተለያዩ።በበነገታው ስብሰባ ላይ ሊቀመንበራችንን ስለሚመጡ እንጠብቅ ተብሎ እየጠበቅን እያለን ሰአት በማለፉ ይደወልላቸው ተብሎ ሲደወል በመታመሜ መምጠት አልቻልኩምና ቀጥሉ ተብሉ ሃሳባቸው ለምክር ቤቱ ሲቀርብ፤ምክር ቤቱ « ወስነን ወደጨረስነው ጉዳይ ለምን ትመልሱናላችሁ ይህ ያለቀ ስለሆነ አንመለስበትም» ተባለ።ይህ ለሊቀ መንበራችን ሲነገር የተሰጠው መልስ «የአሜሪካው ቡድን ተለውጦ፤ እኔ (ማለት ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል) አባይነህ ብርሃኑ ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ በሚጓዘው ኮሚቴ ውስጥ የማንካተት ከሆነ ጉዞው መተላለፍ አለበት እኔም



ለህክምናዬ ቅድሚያ ስለምሰጥ ወደ አሜሪካ አልሄድም» የሚል አቋም ያዙ።እዚህ ላይ መታየት ያለበት ልኡካኑ ከተለወጡ የህክምናው ጉዳይ ላይነሳ ካልሆነ ግን ሰበብ ሆኖ ሊቀርብ ማለት ይመሳሳል።

እዚህ ላይ እንግዲህ የላእላይ ምክር ቤት ያስለፈውን ውሳኔ የማፍረስ ጅምር መጣ።ይህ ደግሞ ቅንጅት ካለው የመተዳደርያ ደንብ ጋር ጨርሶ የማይጣጣም ነው በማለት ለማስረዳት ቢሞከርም ኢንጅነር ኃይሉ ፍንክች ያባ ቢላ ልጅ አሉ።

ኢንጅነር ጉዞው ይተላለፍ ሚሌንየምን እዚህ አክብረን እንሂድ የሚል ያልነበረ አዲስ ሃሳብ ሲያመጡ «ቀደም ሲል ስብሰባው የሚካሄድ ልኡካኑም የሚሄዱ መሆናቸው ታምኖበት ደብዳቤ በየሃገሩ ላሉ ቻፕተሮች ተጽፎ አስፈላጊው የዝግጅት፤ያዳራሽ ክፍያ ተከፍሎ፤ዝግጅቱ እየተጠናቀቀ ስለሆነ አሁን መለወጡ ችግር አለበት» ቢባሉም አልስማማም አሉ።ምክንያት ያደረጉትም ጤናቸውን እየሆነ መጣና እንዲያውም «ጀርመን ያለው ሃኪሜ አሁን በያዝኩልህ ቀጠሮ ካልመጣህ ሌላ ቀጠሮ በአጭሩ አልሰጥህም ስላለኝ አልሄድም» በማለታቸው በዚህ ምክንያት ከሆነ «ቡድኑ በተያዘለት ፕሮግራም ይሂድ እርስዎም በችግራችን አብረውን ለቆሙት ወገኖቻችን የጽሁፍ መልእክት ያስተላልፉና ህክምናዎን እንደጨረሱ ይምጡልን» ቢባሉም «ብመጣም ከናንተ ጋር አልቀላቀልም» በማለት ወሰኑ።ይህ ለላእላይ ምክር ቤት ሲቀርብ ላእላይ ምክር ቤቱ ታጋሽ በመሆንና የቅንጅትን አንድነት ቅድሚያ በመስጠት ይበጃል ባለው መሰረት አንድ ተጨማሪ ሰው በማድረግ አቶ ክፍሌ ጥግነህ አብረው ሂደው ለማስረዳትና ሃሳባቸውን ለማስለወጥ እንዲሞክሩ ተወስኖ ሄደው አነጋገረው ይዘው የመጡት መልስ ግን እጅጉን የሚያሳዝን ሆነ።

ኢንጅነር የሰጡት መልስ «አላደርገውም ደሞ እኔ በሌለሁበት አሜሪከ ያለውን ችግር አትፈቱትም» የሚል ሆነ። ይህ ለላእላይ ምክር ቤቱ በቀረበ እለት ተጨማሪ ኢንፎርሜሽን ተብሎ በአቶ አባይነህ የተነገረው «የልኡኩ አባላት ወደ አሜሪካ ቢሄዱ በገማ እንቁላልና በበሰበሰ ቲማቲም የሚደበደብ መሆኑ» ተነገረ።

ይህን መሰረት የሌለው ሪፖርት ወደ ጎን ተትቶ ልኡካኑ ወደ የተመደቡበት ሃገራት እንዲሄዱ መመርያ ተሰጠ።በዚሁ እለት ቤተሰቦቻቸው ስለሞቱባቸው ደጋፊዎቻችን ጉዳይ ቀደም ሲል ተነስቶ አሁን ሄደን ብናነጋግራቸው በአል ከመሆኑም ከብዛተቸውም ለማሰባሰብ ከማስቸገሩም የተነሳ ችግር ስላለው ጊዜም በቂ ስለሌለ አንድ ዘላቂ ገቢ የሚያገኙበትን ጥናት እንዲያጠና የተመደበው ኮሚቴ ሪፖርት አቀረበ።

- የዚህ ኮሚቴ አባላት

- ብርቱካን ሚዴቅሳ
- ሙሉነህ ኢዮኤል
- ደበበ እሸቱ ነበርን የጥናቱንም ውጤት በተመለከተ

«ዘላቂ ገቢ በሚያስገኝ መልኩ ቀርጸን ከጉዞ መልስ ተግባራዊ እንዲሆን» በአቶ አባይነህ ሃሳብ ቀርቦ በዚሁ ተወስነ:: ጨርሶ ወደ አሜሪካ አልመጣም ያሉት ሊቀመንበራችን አስቀድመው በቤታቸው ባካሄዱት የሚስጥር ስብሰባ የመኢአድን የሥራ አስፈጻሚ አባላት የነበሩትን ግን በአሜሪካው ጉዞ የተካተቱትን ኢንጅነር ግዛቸውን አቶ ብሩክ ከበደን ከከሰመው መኢአድ አስወጥተው ሌሎች ተተኪዎች መረጥኩ ያሉት:: አስቀድሞ የዚህ ችግር ፈጣሪ የሆኑት ሻለቃ አድማሱ ቅድመ አፍራሽ ተግባር የነበራቸውና እምነት ሊጣልባቸው የማይችሉ መሆናቸው ሲነገር የነበር ቢሆንም ማንም ሳያውቅ በሚስጥር በተከናወነ ስምምነት በሊቀመንበራችን ብቸኛ

ውሳኔ በእስር ላይ እያለን ማንንም ሳያማክሩና ለማንም ሳይነግሩ ያውም አብረዋቸው በአንድ ቤት የታሰሩት

1. ዶክተር ያእቆብ ሃይለማርያም
2. ዶክትር ሃይሉ አርአያ
3. ዶክተር በፈቃዱ ደግፌ
4. ኢንጅነር ግዛቸው
5. አቶ ብሩክ
6. አቶ ታምራት ታረቀኝ ሁሉም የላእላይ ምክር ቤት አባላት አብረዋቸው እያሉ ወደ አሜሪካ ለማስታረቅ እንዲመጡ የተወከሉትን በማስቀረት ለማንም ሁኔታውን ሳያሳውቁ ሻለቃ አድማሱንና ዶ/ር በዘብሀን ላኩ::ይህ ደግሞ ከኢንጅነር ኃይሉ በስተቀር ሁሉንም ያሳዘነና አያደርጉትም የተባለ ጉዳይ ነበር::

ሻለቃ አድማሱ ቅሬታና ልዩነት ያሳዩ የነበረው አሁን አይደልም:: ጨርሶ ስብሰባው ከመካሄዱ አስቀድሞ ፓርላማ ለመግባት በነበራቸው ቁርጠኛ አቋም ጥቂት ተመራጮችን ሰብስበው እንግባ የሚል ፔቲሽን ሲያስፈርሙ የነበሩና ሲታወቅባቸው ያፈገፈጉ ቀርጥ አቋም የሌላቸው እንደሆነ የታወቀ ነው:ይህን ሊክዱ አይችሉም::

የነሻለቃ አድማሱን አመጣጥ በተመለከተ በፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ስንገናኝ ማን እንዳደረገው ሲጠየቅ ኢንጅነር እኔ ነኝ ደሞ ልክ ነው አሉ::ከዚሁ ጋር ተያይዞ ስለተካሄደው የኮሚቴ ምርጫም እንደማያውቁና ከየዞኑ የተሰጠውን አስተያየት እንዳልተቀበሉት ምርጫውን እንደሚደገፉት ሲናገሩ የማፍረሻ



ደብዳቤ እንዲጸፉ ቢጠየቁ ያንን ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሁላችንም ባለን መገናኛ ዘዴ ለምናውቃቸው የኛ ውሳኔ ሳይሆን የኢንጅነር ብቸኛ ውሳኔ መሆኑን አሳወቅን::

የዶ/ር ታዬን በኮሚተው መካተት በሰማንበት ወቅት በነበርንበት ዞን ጉዳዩ ተነስቶ በሰፋት ይነገር የነበረው በነአቶ አባይነህ ነበር::ቀደም ሲል ዶ/ሩ መኢአድን እንዲቀላቀሉ ተጠይቀወ በነበረበት ወቅት ከመኢአድ ውስጥ አቶ አባይነህ፤ ሻለቃ ጌታቸው መንግሥቱ፤ አቶ ማሙሽት አማረ ናለወጡ በስተቀር አላደርገውም ያሉ ናቸውና ጨርሶ በኮሚቴው ውስጥ እንዲካተቱ ኢንጅነር ኃይሉ ይህን መመርያ አይሰጡም ይባል ነበር:: ዶ/ር በነአባይነህ ብርሃኑ ይወገዙ ይከሰሱና ይወቀሱ ነበር::ያን አባባል ምን በላው?

ቅንጅት ዴሞክራሲያው አካሄድ፤ የሰብአዊ መብት መከበር፤ ተጠያቂነት፤ የሰለጠነ ፖለቲካ፤ሰላማዊ ትግል፤ ሲልና በወረቀት ላይ ስናየው ሁላችንም ይሁን ብለን ነበር::በአንዳንድ አጋጣሚ ግን ተግባራዊ መሆን ሲጀምር፤ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሱት አይነት «የኔ ሃሳብ ብቻ» ተቀባይነት ሲያጣ፤ ሊቀ መንበራችን ያሉት በአብላጫ ድምጽ በዴሞክራሲያዊ ውይይት ውድቅ ሲሆን አንዳንዶቻችን ነግ በኔ በሚል ፈራን::ከወጣንበት መሰላል መውረድን እንደሞት ጠላነው::ድምጻችን ያለምንም ተቃውሞ ገና ስንተነፍሰው ተቀባይነት ማግኘት መቅረቱ ሲታየን ያንን ይሁን ያልነውን ዴሞክራሲ እንደጦር መፍራት ጀመርን::

ሥልጣን የሚሰጥ ሳይሆን በአምቻ ጋባቻ የሚገኝ ሳይሆን በሕዝብ ፍቃደኝነትና ድምጽ የሚገኝ፤ ተመልሶም የሚወሰድ መሆኑን ስንገነዘብ ዴሞክራሲ ማለት ይህ ከሆነ:የሠለጠነ ዴሞክራሲ ማለት ትርጉሙ ይህ ከሆነ፤ «ከማላውቀው መልአክ የለመድኩት ሰይጣን ይሻለኛል» በማለት ወደ ቀድሞው ወደከሰመው ቤታችን መመለስን መረጥን አሉ በተግባራቸው:: አሁንም እያየን ያለነው ይህንኑ ነው::

በፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የሚያዝ ስልጣንም ሆነ ወይም ሃገራዊ ስልጣን፤የአንድ ግለሰብ ወይም የአንድ ቀድሞ ስልጣን መያዝ የቻለ ቡድን እርስተ-ጉልት እንዳልሆነ በመረዳት፣ ቅንጅትን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ነጻ እና ዴሞክራሲያዊ ድርጅት አድርጎ ለማቆም የሚደረገው ጥረት የሩቅ እና የቅርብ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ባህሎቻችንን በሚገባ መተቸት ከቻለ ንቃት-ህሊና ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::ስልጣን ከድህነት መውጫ፣ ስልጣን ውሱን ከሆነው ሃገረዊ ሃብት የተወሰነውን መቦጨቂያ፣ ስልጣን መንደላቀቅን፣ ዝናን እና ክብርን መጎናጸፊያ፣ ስልጣን የራስን እና የቤተሰብን ህልውና መከላከያ መሳሪያ ተደርጎ የሚታወቅበት ባህል በሃገራችን ውስጥ ስር የሰደደ መሆኑ ይታወቃል:: ይህ ለዝንተ-አለም ስር የሰደደ ባህል ሁሌም በመሳሪያ ሃይል የስልጣን ባለቤትን የሚያሳድዱ የህብረተሰብ

ክፍሎች እንዲበራከቱ በማድርግ፣ ከስልጣን ውጭ በሰላማዊ ህይወት ወስጥ በሚደረጉ ጥረቶች አማካይነት ሊመጣ የሚችልን የኑሮ መሻሻልም ሆነ የህይወት ዋስትና ብዙ ሰው ማየት እንዳይችል እና እድሉንም እንዳያገኝ አድርጎታል:: አሁን ያንን ፈለግ የተከተለ አንጥፉልኝ ጎዝጉዙና አስቀምጡኝ የሚል አስተሳሰብን ቅንጅትም የቅንጅት ባለቤት

የሆነውም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቀበሉት ሂደት አይደለም::

አሁን እንደሚታየው ከሆነ የአሜሪካ ልኡክ የሚከሰስ የሚወቀሰውም እዚህ አሜሪካ ባለው የኢንጅነር ኃይሉ ስብስብ እንጂ በሊቀመንበራችን ኢንጅነር ኃይሉ ነው ብዬ ማመን ይቸግረኛል:: ቅንጅት ሰደት ላይ አይደለም አሳይለምም አልጠየቀም ስለዚህም ቤቱ ሃገሩ ነውና ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል እንደሊቀመንበር መጠየቅ፤መጠየቅም ካለባቸው ወደ ሃገር ገብተው በስልጣን ወንበራቸው ተቀምጠው ጉዳያቸውን ለላእላይ ምክር ቤቱ አቅርበው በሚሰጠው ውሳኔ እንጂ መተዳደርያ ደንባችን ሊቀ መንበሩ እንዳሻቸው ይፈልጣሉ ይቆርጣሉ አይልም::እኛ ደሞ ከቅንጅት ደንባችን ውጪ ንቅንቅ የምንል አይደለንም::ከማንም በላይ ቅንጅት ነው::ከምንም በፊት ቅንጅት ነው::ስለዚህም ለቅንጅት መተዳደርያ ደንብ መገዛትና ደንቡንም ማክበር የሁላችንም ግዴታ ነው በቅንጅት የመታቀፍ እድል የሚወሰነው በዛ እንጂ በግለሰብም በቡድንም አይደለም::

የቅንጅትን መተዳደርያ ደንብ ተግባራዊ ማድረግ ሲጀመር ማኩረፍ የፊውዳል ባህርይ ነው:: ቅንጅት ደግሞ ለፊውዳላዊው አስተሳሰብም ሆነ ለፊውዳል ተሚጋቾች ቦታ ስለሌለው በሰለጠነ ፖለቲካ በሰላማዊ መንገድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ራዕይ ተግባራዊ ያደርጋል::

> የህዝብን ድምጽ ማስከበር ለድርድር የማይቀርብ ግብ ነው::ሂደቱ ፍጹም ሰላማዊ በሆነ ስልት ነው:: ከዚህ ውጪ የማይሞከር ሕልም ነው::ማድረግ የማይቻለውን ማድረግ የሚቻለው በሕልምና ቅዠት ብቻ ነው ቅንጅት ደግሞ ቅዠትም የለበት ካለመም የሚተገበር ራዕይ ብቻ ነው::

ሕዝብን እየናቀ ለሕዝብ ቆሜያለሁ: ሃገርን ለጥፋት እያስማሙ ሃገሬን እወዳለሁ ምን ይሉት ቋንቋ ነው? እያንዳንዱ የቅንጅት አባልም ሆነ አመራር የሕዝብ የበላይነትን አምኖና ተቀብሎ ለሕዝብ ፍላጎትና ስሜት እንዲሁም ለራዕዩ ተግባራዊነት ተገዢ ለመሆን ቃል ገብቷል:: የቅንጅትን መተዳደርያ ደንብና ማኒፌስቶ ሲቀበል ያንን በተግባር ሊተረጉምና ለሱም ተገዢ ሊሆን



ቃል ገብቶ ነው:: ያውም የማይታጠፍ ቃል:: ሕዝብን ከእኔ አውቅልሃለሁ የሞኝ ቋንቋ አላቆ እራሱ ለራሱ የሚያውቅ መሆኑን አምኖና ተቀብሎ ነው አባልም የሆነው:ወደ አመራርነትም የወጣው::ያን ሲያጥፍ ነገር ተበላሸ ማለት ያን ጊዜ ነው::

ለመምረጥ ሲል:ለቅንጅት ሲል:የተጎሳቆለልንን: የተንከራተተልንን: የተወገዘልንን:

የተፈናቀለልንን የሞተልንን ክቡር የሆነውንና በቃሉ የጸናውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ነውመናቅ የተጀመረው:: በመተዳደርያ ደንቡ ላይ የሌለውን ጨርሶ ያልተባለውን ተብሏል ብሎ ሕዝብን ለማታለል መሞከር ምን መሆን ነው? ጤንነት?

ጨርሶ በመተዳደርያ ደንቡ ላይ የሌለ አንቀጹ ያላለውን አለ ብሎ የማይሆነውን ሁን ብሎ ድፍረት ማሳየት ለውርደት ነው እንጂ ሌላ ትርጉም ሊኖረው ጨርሶ አይችልም::

- እንግዲህ ለሕዝብ ማን ቀጠፈ? ለህዝብ ማን ዋሸ?
- ማን በመተዳደርያ ደንቡ ላይ የሌለውን አለ ብሎ ለፈፈ?
- ማን ሕዝብን አታውቅም መሃይም ነህ አታነብም አለ?

በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ መተዳደርያ ደንብ ላይ በዘር በብሔር በቅርበት በመተዋወቅ በመደጋገፍ ሥልጣን ይተላለፋል የሚል አንቀጽ ጨርሶ የለም::

ከሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ መሃል አብላጫው ቁጥር በአንድ ጎን ሆኖ ከላእላይ ምክር ቤቱ የተሰጠውን የሥራ ሃላፊነት በመወጣት ላይ ሳለ ድንገት በተፈጠረ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ሰበብ ለብቻ ተገንጥሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ሕዝብን መናቅ ነው::የሕዝብን አደራ ማጣመም ነው::ሕዝብን የሚያስቀድም መሪ ለሃገር ከበሬታ ያለውና ራእዩ በሀገር ላይ የተመሰረተ መሪ ምንም ስህተት ቢሰራ ያንን በመመለስና በማስተካከል ሥራውን ያከናውናል እንጂ በተልካሻ ምክንያት ያውም አየር ማረፊያ መጥተው አልተቀበሉኝም በሚል ሰበብ የህዝብን ራእይ መግደል ዴሞክራሲያዊ ስርአት እገነባለሁ ብሎ በተነሳ አካል ጨርሶ ታይቶ የማይታወቅ አሳፋሪ ተግባር ነው::

የኢንጅነር ኃይሉ አንጃ አሜሪካ ከገባበት እለት አንስቶ ልክ አዲስ አበባ እንደተደረገው ሁሉ ተሰመነ:«እባክህ በእልህ ሂደቱን አታበላሸ» ተብሎ አማላጅ ተላከበት:የሕዝብን ተስፋና ራእይ የሚያደበዝዝ ሁኔታ አይፈጸም ተባለ:ጠፋ የሚባል ጉዳይ ካለ ቁጭ ብለን በሰለጠነ ውይይት እንነጋገር ቢባልም አሻፈረኝ ያባ ቢላ ልጅ ተባለ ሕዝብን ግራ እንዳናጋባ ለጠላትም መሳቂያ መሳለቂያ

እንዳንሆን በጠረጴዛ ዙርያ ችግራችንን እንፍታ ተብሎ በሃገር ባሕል ልማድ መሰረት ሽማግሌ ቢጠይቅም ር ፈጽሞ ተባለ።

- ኢንጅነር ፍቅርን በጥላቻ
- አንድነትን በመበታተን
- ሰላምን በግጭት
- ክበሬታን በንቀት

ለሰላም ተብሎ የተሰነዘረ ልመናን እንደፍርሃት በመቁጠር የተደረገውን የሰላም ጥሪት ሁሉ ካለኔ ያወቀ የበቃ ላሳር ባሉ ደጋፊዎች ከንቱ መንገድ በመመራት ይሄው ለዚህ ደረሰ።ያን ጊዜ ጀርመን ነው የምሄደው የሚል ድንገተኛ ውሳኔ ሲያመጣ ተለመነ። አሜሪካም ብመጣ ከናንተ አልቀላቀልም ሲል ተለመነ። የጽሁፍ መልእክት አልክም ሲል ተለመነ።ሁሉን ነገር እምቢ ሲል መለመኑ ችግሩን አባባሰው።ከእንግዲህ ልመናም የለ ሽምግልናም በቃው ከእንግዲህ የቅንጅት ላንድነትና ዴሞክራሲ ሥራ አስፈጻሚ የሚወስደውን እርምጃ ተግባራዊ ማድረግ እንጂ ግራ ለማጋባት ወደ ሚጠራ ስብሰባ የሚሄድ አይኖርም።አሁን ያቀዱት ሌላ የጥፋት ተልእኮ ነው።ያሁኑን ኮሚቴ የሚሉትን እነ ዶ/ርና ሻለቃ ያሉበትን አፈረስን ብለው ሌላ ኮሚቴ ያቋቋሙና አምባገነን መንግሥታት ወይም መሪዎች እንደሚያደርጉት ካባቸውን የለወጡ ለመምሰል ዴሞክራቲክ ቅንጅትን ፈጠርን ሊሉ ነው።ዴሞክራሲ የሚለው ቃል ብቻውን ቢደረደር ሥርአቱን አያመጣም ያንን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማምጣት ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል።ለደንብና ለሕግ ተገዢ መሆን ሳይችሉ ዴሞክራቲክ መሆን ደግሞ ከንቱ ድካም ነው።

ኢንጅነር ኃይሉን ለማነጋገር ቀጠሮ ይዘው ደክመን ሳይሉ ከላስ ቬጋስ ድረስ ሚኒያፖሊስ በመብረር የመጡትን የልኡክ አባላት የገጠማቸው ችግር ውጣ ውረድ ልግባ አትገባም በጣም የሚያሳፍር ነበር።ልኡካኑ ሲመጡ 3 ሆነው ነው።ኢንጅነር ቤት ሲደርሱ የሚያነጋገራቸውም በወጉ አሳገኙም ኢንጅነርም የሉም ተባሉ።በስንት ደጅ ጥናትና መጉላላት ለጥቂት ደቂቃ ሊያነጋግሯቸው ፈቀዱና ሊገቡ ሲሉ ከ3ቱ ሁለቱ ብቻ ናቸው የሚገቡት ተባሉ።አንዱ አይገቡም የተባሉት የቀድሞው መኢአድ የሥራ አስፈጻሚ አባል የነበሩት አቶ ብሩክ ከበደ ናቸው።ሌሎቹም እሳቸው ካልገቡ እኛም አንገባም በማለታቸው በስንት ልምምጥ ተፈቀደና ገቡ።ተ/ም/ሊቀ መንበር ብርቱካን ሚዴቅሳ አበባ ተሸክማ ነው የገባቸው። ያላትን አክብሮት ለመግለጽ መልካም ምኞታቸውንም በአበባ ጉንጉን ለማሳየት። የጠበቃቸው ግን ሰላምታ በሃገር ልምድና ባህል መሰረት ከአንገት በላይም ቢሆን መስተንግዶ አልነበረም ይልቅስ ምሬት ባለው አነጋገር የማይሆን የማይሆን ቃላት አወረዱባቸው ያውም እንግዶች ሆነው በሄዱበት ቤት።ያን ሁሉ ችለው ልመናቸውን ቢቀጥሉም በቃ አሁን የህክምና ሰአት



ነው በቃ ብለው ውሃ ጠጡ ሳይባሉ ተባረሩ።ቢያንስ 22 ወራት አንድ ላይ በአንድ ጉዳይ አብረው ታስረው ነበር።ሌላው ቢቀር የኢትዮጵያዊነታችን መገለጫ መስተንግዶ ነበር።ሲጓዙ ውለው በደከመ ጉልበት ተባረሩ። ይህ ደሞ ደምበኛ የፊውዳል ባህሪ ነው። ድሮ ፊውዳሎች ሲያኮርፉ ግብር የሚጠሩትን ይተዉታል፤ ሰላም የሚሉትን ያርቁታል፤ በውይይት ችግርን መፍታት ብሎ ነገር አያውቁማ።አኩርፈው ከስልጣን ማውረድ ማሰር መግረፍ ሲብስም መግደል ነው ባህሪያቸው፡ያን ደሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ ተፍቶታልና ተመልሶ ወደዚያ አይገባም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእንግዲህ የሚያውቀውና የሚመራበትም የሰለጠነ ፖለቲካ ብቻ ነው።ሰላማዊ የሰለጠነ ፖለቲካ በቃ። ከዚያ ውጪ ሌላ የማይሞከር ነው።የሕዝብ ራእይ የሕዝብ ፍላጎት በማንም ጉልበትና ጫና ለድርድር አይቀርብም።

ለቆምንለት ለደከምንለት ለተንገላታንለት የዴሞክራሲ ስርአት የሰብአዊ መብት መከበር ለተጠያቂነት መከበር ከመቆምና በሰላም ከመታገል ውጪ ዝንፍ የማንል መሆናችንን ልናረጋግጥ እወዳለሁ።

ቅንጅት የሰለጠነ ፖለቲካ ያራምዳል ስንልም በሃገራችን ላይ እስከዛሬ ሲካሄድ የነበረው የጦር ሰበቃ እንዲያበቃና በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ለማምጣት መታገል ማለት ነው።ቅንጅት በመሳርያ ትግል የሚያምኑትንም ጭምር ወደ ሰላማዊ ትግል እንዲመለሱ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል።አርጉ አታድርጉ ለማለት ሳይሆን በሃገራችን እስከዛሬ ሲደረግ በነበረው የጦር መማዘዝ ትግል የበርካታ ኢትዮጵያዊያን ሕይወት ጠፍቷል አሁን እንደገና ወደዚያ መግባቱ የባሰ እልቂት ማምጣት ነውና እገሌ ተገሌ ሳይባል ሁሉም በሰላማዊ መንገድ በሰለጠነ ፖለቲካ ለለውጥ መታገልን እንዲመርጥ ቅንጅት ለማግባባት ይጥራል።

### ቅንጅት ፍቅር-ሰላም-አንድነት-ሃይል-ብልጽግና ነው

እያልን ከዚያ ወደተለየ ስልት አንገባም።ሁሉም አካል ተቃዋሚም ገዢውም ፓርቲ የሰለጠነ ፖለቲካን አካሄድ በመቀበል በሩን ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን ክፍት በማድረግ በሰላማዊ መንገድ ትግልን ማካሄድ እንደዋነኛ አማራጭ ሊታይ ይገባል።

ፖለቲካ መከራረፊያ መጣያ መሰዳደቢያ የእሰጥ አገባ መድረክ የሃሰት ስም መለጠፊያ የአሉባልታ ማካሄጃ ሊሆን አይገባም።ፖለቲን የሚፈራ የሚሸሽም ሊሆን አይገባውም።በኛ ሀገር ሆነና ነው እንጂ በሰለጠነው ዓለምማ ፖለቲካ ምን ማለት እንደሆን የፖለቲካ ልዩነት ምን እንደሚመስል እያየነው ነው። በጣም የሚያሳዝነው ግን በነጻ የሰለጠነ ዓለም ውስጥ ተቀምጠን የሃገሩን

ባህል ከማወቅና ጥሩውን ከመያዝ ይልቅ መጥፎ ባህላችንን ማራገቡን መርጠናል።በስድብ ለውጥ ለማምጣት በስድብ እውነትን ለማሸነፍ በስድብ ታማኝነትን ለማግኘት በስድብ ንጹህ ሆኖ መታየትን እንሞክራለን።እውነቱ ግን በስድብ የሚገኝ አንዳች ነገር የለም። ሰዳቢ ለመሆን ደጋግሜ እንዳልኩት ባለጌ መሆን ብቻ ነው የሚያስፈልገው።በውሸት ተሸፋፍኖ ከሃቁ ለመቅደም የሚደረግ ሩጫ ጨርሶ አያዋጣም።ሕዝብን እናከብራለን ካልን እውነቱን በጉያችን ሸጉጠን በማፈን ሃሰቱን ብቻ ማነብነቡ ለሕዝብ ክብሬታ ሳይሆን ንቀት ነው።ምናልባት ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል በሚለው ጠባብ መንገድ ለመሄድ ታስቦ እንደሆነ በአሁኑ ዘመን አይሰራም።

- ጥላቻን ትተን ፍቅርን
- ሃሰት አርቀን አውነትን
- መለያየትን ትተን አንድነትን
- ጀብደኝነትን ትተን ቀናነትን
- ማንአለብኝ ባይነትን ትተን ሕዝባዊነትን
- እኔነትን ትተን እኛነትን
- መግዛትን ትተን ማገልገልን
- ግብታዊነትን ትተን ለሕግና ለደንብ መገዛትን ተግባራዊ ለማድረግ ብቃቱ ሊኖረን ይገባል።

ይህን ለማድረግ ብቃቱ እስከሌለን ድረስ ሕዝብን እንወክላለን ለማለጽ መሞከር ከንቱ ጩኸት ነው። ኢንጅነርና አጃቢው ጦር የተጠየቁት ነገር ቢኖር የቅንጅት ላንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ደንብ ይከበር፡ይጠበቅ ነው።ደንቡ የሚለው ተግባራዊ ይሁን ነው፡ለደንቡ ሁላችንም ተገዢ እንሁን ነው።ይህን መጠየቅ ምን የሚያስቆጣና የሚያስኮርፍ ነገር አለበት?መነጋገርም ያለብን ስለ ድርጅታችን ስለ ቅንጅት እንጂ ከዚያ ውጪ የሚያነጋግረን ግላዊ ጉዳይ ጨርሶ ሊኖር አይገባም።የማንም ስም ሲነሳ ከድርጅቱ ጉዳይ ጋር በተያያዘ እንጂ በአሉባልታ ላይ በተመሰረተ ያልተስተካከለና መሰረት የሌለው ውንጀላ ከትዝብት ውጪ ለምንም አይበጅም።ማእከል ማድረግ ያለብን የቅንጅትን ደንብና ሕግ መከበርና አለመከበርን ነው እንጂ አሉባልታው እንካን ለሰሚ ለተናጋሪውም ጠቀሜታ የለውምና በዚያ ጊዜ ማጥፋት ጨርሶ አያስፈልገንም።

ቅንጅት አንድ ጊዜ በሕዝብ ውስጥ የገባ ተስፋና የወደፊት ራዕይ በመሆኑ በተራ ወሬ የሚፈታ ድርጅት አባላቱም ለተራ ወሬ የሚገዙ አይደሉም።የቅንጅትን ካምፕ በማተራመስ ቅድሚያ የሚሰጠውን ጉዳይ እንድንረሳና ወደ ትናንሽ ጉዳይ እንድናተኩር ለማድረግ ነበር ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ።ቶሎ ነቅተን ሁለቱንም እንደየሚዛናቸው ለማስኬድ ባንነቃ ኖሮ አሁን ያለንበት ሁኔታ ሁሉ ተለውጦ ቅንጅትም በማይሆን ሰዎች እጅ ወድቆ መተራረቢያ ሆነን



እንቀር ነበር።ለተንኮሉ ቶሎ ነቅተን መፍትሄ በማግኘት በሃገር ውስጥ ሊደረግ የሚገባውን በአንድ በኩል እዚህና አካባቢው የሚነዛውንም መርዝ በሌላ ጎን በመታገል ከመፈረናከስ ድነናል።አሁን ቅንጅትን ለቆ የሚወጣ ወይም የሚወጡ ናሉ ግለሰቦች እንጂ ድርጅቶች አይሆኑም ከዚህ በፊትም ታይቷል።ግለሰቦች ደግሞ ቢወጡ ተጎዱ እንጂ መከታ አጡ እንጂ ክብራቸውን እራሳቸው ገፈፉ እንጂ ቅንጅት ያው ቅንጅት ሆኖ ይቀጥላል።ለሕዝብ ብልጽግና ነጻነት ለሃገር እድገት አንድነት ሁላችንም ለዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት መከበር በጽናት እንቁም።ለድርጅታችን ደንብና ሕግ መከበር ዘብ የመቆም ድርጅታዊ ግዴታችን ነውና ማንም ሊያፈርሰው ሊጥሰው እንደማይችል ቃል እንግባ!

አሁን የምናየው የጥላቻ ፖለቲካ ነው ጥላቻው መሰረት ያደረገው ደሞ በግለሰቦች ላይ ነው።ድርጅቱን አንጠላውም ግን አዲስና የሰለጠነ ፖለቲካ የሚያራምዱትን ግን እንጠላለን ነው አዝማሚያው።ግለሰቦችን በተለያየ ወንጀል በመኮነን እራሳቸውን ፍጹምና ሃቀኛ በማድረግ ይደስኩራሉ።በጠረጴዛ ዙርያ ወይም በሕዝብ ፊት ቁጭ ብለው እውነቱን ፍርጥርጥ አድርገው በማውጣት በአደባባይ መነጋገርን ይሸሹታል።በጥላቻ ላይ የተመሰረተ አካሄድ ነው የሚመርጡት፡የጥላቻቸው ምክንያት የመንግስት ስልጣን በአንድ መልኩ ወይንም በሌላ ለ«ኛ ይገባናል» ብለው ከልባቸው የሚያምኑ ግን በምንም አይነት አገሪቱን ወደ «እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ህዝቡንም ወደ ነፃነት ለመውሰድ አላማውም ፍላጎቱም የሌላቸው፡ከኖሩበት የበላይነት፡የግዛት አስተሳሰብ እልፍ ብለው በዴሞክራሲያዊ ሥርአት ጨርሶ የማያምኑ ናቸው።ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወይም የሰለጠነ ፖለቲካ ለኢትዮጵያ ገና ጊዜው አይደለም ብለው አሁንም በእናውቅልሃለን ዘመን ያሉ ናቸው።ይህ ደሞ የቅንጅት የአባላቱና የደጋፊዎቹም አመለካከትና እምነት አይደለም።

በዚህም መልካሙን ሁሉ እየተመኘሁ ልሰናበት።